
ስደትና ፍልሰት — የታሪካችን ሾተላይ“
ገጽ 10

መነሻውን ዕውቀትና ልምድ ያደረገው አሚጎስ
ገጽ 13

ያሳለፈ ትናንት ...
ገጽ 16

ኢፕድ
# አዲስ ዘመን
83ኛ ዓመት ቁጥር 054 ጥቅምት 24 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ቅዳሜ
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



# የቼክ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

## ፒትር ፊያላ ለይፋዊ የሥራ ጉብኝት አዲስ አበባ ገቡ

ገጽ 4






## ”የሰብዓዊ ድጋፍን በራስ አቅም መሸፈን የሉዓላዊነትና የክብር ጉዳይ ነው”

- አቶ ደመቀ መኮንን
ጠቅላይ ሚኒስትርና
የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር

ገጽ 4

## መንግሥት ከስድስት ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ብር በላይ የነዳጅ ድጎማ አድርጓል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በ2016 የመጀመሪያው የሩብ ዓመት በታለመለት የነዳጅ ድጎማ መንግሥት ከስድስት ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ብር በላይ ድጎማ ማድረጉን የትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር አስታወቀ።

በትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር ብሔራዊ የታለመለት ነዳጅ ድጎማ ፕሮጀክት አስተባባሪ አቶ ሰልማን መሀመድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤

መንግሥት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ተስፋ የተጣለበት የሩዝ ልማት

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

የአንድን ሀገር እድገት ለማፋጠን የምግብ ዋስትናን የማረጋገጥ ጉዳይ ቀዳሚ አጀንዳ ነው፡፡ በምግብ ራሳቸውን የቻሉ ሀገራት በቴክኖሎጂው፣ በፖለቲካውና በኢኮኖሚው ዘርፍ የበላይ ከመሆናቸው በላይ ልዕለ ኃያልነት አጎናጽፏቸዋል፡፡

የዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ለማጠናከር፣ በቀጣናው ተሰሚነትን ለማሳደግ፣ የአካባቢውን ጂኦ ፖለቲካ በሚፈለገው መልኩ ለመቀመርና የላቀ ተጠቃሚ ለመሆን የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡

ኢትዮጵያ በቅርብ ጊዜ የምግብ ዋስትናዋን ለማረጋገጥ

ተስፋ የተጣለበት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት
Ethiopian Meteorology Institute
ETHIOPIA

# ኢንስቲትዩቱ
## በመጪዎቹ 10 ቀናት የደረሱ ሰብሎች መሰብሰብ እንደሚገባ አሳሰበ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በመካከለኛው፣ በምሥራቅና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ሊኖር ስለሚችል በመጪዎቹ 10 ቀናት የደረሱ ሰብሎች መሰብሰብ እንደሚገባ የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት አሳሰበ።

ኢንስቲትዩቱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በላከው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ በመካከለኛው፣ በምስራቅ እና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል ይጠበቃል። ይህም ሁኔታ በደረሱ ሰበሎች ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል በመሆኑ የሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊውን ጥንቃቄና ዝግጅት በማድረግ የደረሱ ሰብሎችን የመሰብሰብ ተግባር ማከናወን ይኖርባቸዋል።

በምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚኖረው እርጥበት በተለያየ ምክንያት ዘግይተው ለተዘሩና የእድገት ጊዜያቸውን ላልጨረሱ የመኸር ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የተሟላ እድገት የሚያስፈልጋቸውን የውሃ አቅርቦት ከማሟላት አንፃር አዎንታዊ ሚና እንደሚኖረውም በመግለጫው አመልክቷል።

በደቡብ ምዕራብና በደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተስፋፋና ሰፊ ቦታዎችን የሚያካትት ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን የሚኖረው ዝናብ ውሃ አጠር በሆኑ አካባቢዎች የሚገኘውን የዝናብ ውሃ ለማቆርና ለመያዝ መልካም አጋጣሚን ይፈጥራል።

ነገር ግን በተዳፋትና ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ላይ የአፈር መሸርሸርና በእርሻ ማሳዎች ላይ የውሃ መተኛት ሊያግጥም እንደሚችል መግለጫው ጠቁሞ፤ አርሶ አደሮችና የሚመለከታቸው አካላት ከወዲሁ በግብርና ባለሙያዎች በመደገፍ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚያስፈልግ መግለጫው አሳስቧል።

በሚቀጥሉት አስር ቀናት የበጋ ወቅት እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑት የባሮ አኮቦ፣ ገናሌ ዳዋ፣ በመካከለኛውና በታችኛው ኦሞ፣ ጊቤ፣ ዋቢሸበሌ የታችኛው ስምጥ ሸለቆ እና አጋዴን፣ ተፋሰሶች ላይ የተለያየ መጠን ያለው እርጥበት እንደሚያገኙ ይጠበቃል ነው ያለው መግለጫው።

ይህም ሁኔታ የተፋሰሶችን የገጸ ምድርም ሆነ የከርሰ ምድር የውሃ ሀብት ከማበልጸግ አንጻርም ሆነ በተለያየ ዘዴ ለሚከናወኑ የውሃ ማሰባሰብ ተግባራት አዎንታዊ ሚና እንደሚኖረው መግለጫው አንስቶ፤ የበጋ እርጥበት ተጠቃሚ ባልሆኑት ተፋሰሶች ላይ የሚጠበቀው እርጥበት የተሻለ የውሃ ሀብት በግድቦችና በውሃ አካላት ላይ እንዲኖር አስተዋጽኦ ያደርጋል ብሏል።

በሁለተኛው አስር ቀናትም ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በደቡባዊው አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች በመነሳት ሰፊ ቦታዎችን የሚያካትትና ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ ይላል መግለጫው።

በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብና ደቡብ ምስራቅ አካባቢዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር ትንበያዎች የሚያመላክቱ መሆኑን ገልጾ፤ ይህም ሁኔታ ለአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለአረንጓዴ እፅዋት ልምላሜ ሽፋን መሻሻል፣ ሰው ሰራሽም ሆነ የተፈጥሮ ምንጮችን ከማጎልበት እና የውሃ አቅርቦትን ከማረጋገጥ አንፃር አዎንታዊ እንደሚኖረው በመግለጫው አስታውቋል።

# በአፍሪካ በእውቀትና ክህሎት የላቀ ዘመናዊ ሠራዊት ለመገንባት እየሠራን ነው

**ታደሠ ብናልፈው**



ፎቶ፡- ዳኜ አበራ

ሆለታ፡- በቴክኒክ ሙያ የላቀ ከአፍሪካ ጠንካራና ዘመናዊ የመከላከያ ሠራዊት ለመገንባት እየሠራን ነው ሲሉ የመከላከያ ትምህርትና ሥልጠና ዋና መምሪያ ኃላፊ ሌተናል ጀኔራል ይመር መኮንን ገለጹ።

በሜጀር ጀኔራል ሙሉጌታ ቡሊ ፖሊ-ቴክኒክ ኮሌጅ "በቴክኒክ ሙያ የላቀ ብቃትና ክህሎት ያላቸው ፕሮፌሽናል ወታደር ሙያተኞችን ለማፍራት እንተጋለን" በሚል መሪ ሃሳብ ትናንት የፓናል ውይይት ተካሂዷል።

በውይይቱ ላይ የመከላከያ ትምህርትና ሥልጠና ዋና መምሪያ ኃላፊ ሌተናል ጀኔራል ይመር መኮንን እንዳሉት፤ በቴክኒክ ሙያ የላቀ ከአፍሪካ ጠንካራና ዘመናዊ የመከላከያ ሠራዊት ለመገንባት እየሠራን ነው። በዚህ ረገድ የሜጀር ጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የመከላከያን አቅም ለማሳደግ በሚደረገው ጥረት ውጤታማ ነው።

ኮሌጁ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ የሀገሪቱን የመከላከያ ኃይል አቅም በመገንባት ረገድ ብቁ ሙያተኞችን በማፍራት ከፍተኛ ድርሻ መወጣቱን ሌተናል ጀኔራል ይመር ተናግረዋል።

እንደ ሌተናል ጄኔራል ይመር ገለጻ፤ በፓናል ውይይቱ በቂ ግብዓት መሰብሰብ ተችሏል። ይህም ሃሳቦችን በማደራጀት የላቀ ሥራ ለመሥራት ጠቀሜታው የጎላ ነው።

የሜጀር ጀነራል ሙሉጌታ ቡሊ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የሁሉም የመከላከያ ክፍሎች እንደሆነ የጠቆሙት ሌተናል ጄኔራል ይመር፤ ኮሌጁ በአደረጃጀት ሆነ በማስተማር ልምዱ ስኬታማነትና ወደር የሌለው እንደሆነም አብራርተዋል።

የመከላከያ ሠራዊት የሰው ሀብት መምሪያ ኃላፊ ሌተናል ጀነራል ሀጫሉ ሸለመው በበኩላቸው፤ በኮሌጁ እየተሰጠ ያለውን የሙያ ሥልጠና የሠራዊቱን መሠረታዊ ችግሮችን የሚፈታ ነው ብለዋል።

በሜጀር ጀነራል ሙሉጌታ ቡሊ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ በሳይንስ፣ በቴክኒክና ሙያ እንዲሁም በቴክኖሎጂ የዳበረ የሰው ኃይል በማፍራት የሠራዊቱን ቴክኒካዊ ችግሮች እየፈታ መሆኑን ገልጸዋል።


የሜጀር ጀኔራል ሙሉጌታ ቡሊ ፖሊ-ቴክኒክ ኮሌጅ አዛዥ ብርጋደል ጄኔራል አበበ ዋቅሹማ በበኩላቸው በእውቀትና ክህሎት የላቀ ሙያ ያላቸውን ወታደሮች እያፈራን ነው ብለዋል።

በቀጣይም ኮሌጁ የላቀ ክህሎትና ብቃት ያላቸው ወታደሮችን በማፍራት በ2030 በሀገር ውስጥ እና በአፍሪካ ተወዳዳሪና ተመራጭ ተቋም ለመሆን ራዕይ ሰንቆ እየሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

የሜጀር ጀኔራል ሙሉጌታ ቡሊ ኮሌጅ በ1953 ዓ.ም ከተቋቋመ ጀምሮ የሠራዊቱን የውጊያ አቅሞች የሚያጠናክሩ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና በመስጠት ላይ መሆኑ ይታወቃል።

# ኢትዮጵያና ኮሪያ ትብብራቸውን ለማጠናከር ትኩረት እንደሚሰጡ ገለጹ

**ዘላለም ግዛው**



አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ እና ኮሪያ በጤና ዘርፍ፣ በኢንዱስትሪ፣ በስፖርት እና በሰው ሀብት ልማት ያላቸውን ሁሉን አቀፍ ትብብር በማጠናከር ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር ትኩረት እንደሚሰጡ የሁለቱ ምክር ቤቶች አባላት ገለጹ።

በ ቼልሶ አን (ዶ/ር) የተመራ የኮሪያ ምክር ቤት አባላት እና በጎ አድራጎት ድርጅቶችን ያካተተ የልኡካን ቡድን ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የውጭ ግንኙነትና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ዲማ ነገዎ (ዶ/ር) እና ከጤና፣ ማህበራዊ ልማት ባህል ስፖርት ምክትል ሰብሳቢ ከይረዲን ተዘራ (ዶ/ር) ጋር ተወያይቷል።

የልኡካን ቡድኑ በጤና ዘርፍ በኢትዮጵያ እየተደረገ ያለውን ትብብር በመመልከት ተጨማሪ ድጋፍና ትብብር ለማድረግ የሚያስችል ውሳኔ ለመወሰን ነው ጉብኝት ያደረገው።

ዲማ ነገዎ (ዶ/ር) የሁለቱ ሀገራት ትብብር 60 ዓመት እንደሞላው አንስተዋል። ረጅም ታሪክ ባስቆጠረው ወዳጅነት የኢትዮጵያ ወታደሮች ከ 70 ዓመት በፊት ኮሪያ ዘምተው የድል ታሪክ ማስመዝገባቸውን አስታውሰዋል።

የቆየ ግንኙነቱ በሕዝብ ለህዝብ ግንኙነት ሊጠናከር እንደሚገባው እና ሁለቱ ምክር ቤቶች የልምድ ልውውጥ ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው ጠቁመዋል።

ሕግ በማውጣት፣ አስፈጻሚውን አካል በመከታተል እና በመቆጣጠር የኮሪያን ልምድ በመቅሰም የበለጠ ትብብር እና የልምድ ልውውጥ ማድረግ እንደሚያስፈልግም ተስማምተዋል።

ኮሪያ በእኤአ 2030 በኮሪያ ቡሳን ከተማ ለምታዘጋጀው ዓለም አቀፍ ኤክስፖ የኢትዮጵያ ድጋፍ እንደማይለይም ቃል ገብተዋል።

ከይረዲን ተዘራ (ዶ/ር) የሁለቱ ሀገራት ግንኙነት የኮሪያ ዘማቾች መታሰቢያ ሙዚየም እስከመገንባት የደረሰ መሆኑን ተናግረዋል።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ ጤና፣ ማህበራዊ ልማት፣ ባህልና ስፖርት ከኮሪያ ልምድ ለመቅሰም ፍላጎት አለ። እስካሁን በጤና ዘርፍ ባለሙያዎችን ከማሠልጠን አንስቶ በዘርፉ የተደረገው ድጋፍ መንግሥት በሀገር አቀፍ ደረጃ የጤና ሽፋንን ለማዳረስ የተቀመጠውን እቅድ እንደሚያግዝ ገልጸዋል።

በህክምና መሣሪያዎች፣ በመድሃኒት አቅርቦት ደረጃቸውን በጠበቀ መልኩ የጤና አገልግሎት ለማዳረስ ቀሪ ተግባራት መኖራቸውን ቋሚ ኮሚቴው በክትትሉ መታዘቡን አንስተዋል።

ከሀገራዊ ፍላጎቱ አንጻር የመድሃኒት ምርት ስምንት በመቶ ብቻ እንደሚያሳካ በመጠቆምም፤ የኮሪያ ባለሀብቶች ባሉ ትላልቅ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው ቢያለሙ ተጠቅመው ሀገራዊ አቅምን ማሳደግ እንደሚችሉም ነው የጠቀሱት። በሥራ፣ በቴክኖሎጂ፣ በጊዜ አጠቃቀም የባህል ለውጥ ላይ ተሞክሮ ለመቅሰምም ተነጋግረናል ብለዋል።

የልኡካን ቡድኑ አባላት ኢትዮጵያ የሚገባትን ያህል ታድጋለች በሂደቱም የኮሪያ ድጋፍ አይለይም ብለዋል።

በጤና ዘርፍ የሚገኙ የኮሪያ ባለሀብቶች በኢትዮጵያ ተሰማርተው የጤና ዘርፉን እንዲደግፉ ግፊት እንደሚደረግም ነው የጠቀሱት።

የልኡካን ቡድኑን የመሩት ዶ/ር ቼልሶ አን፤ ኮሪያ ኢትዮጵያን፣ የኮሪያ ዘማቾችንና ቤተሰቦቻቸውን ውለታ እንደማትዘነጋም ነው በውይይቱ ያነሱት።

ኮሪያ ዓለም አቀፍ ድጋፍን የደረሰችበትን እድገት ባማከለ መንገድ አራት እጥፍ በማሳደግ በዓመት ወደ 100 ሚሊዮን ዶላር እንዲያድግ መደረጉን አንስተዋል። በኮሪያ መንግሥት በማደግ ላይ ላሉ ሀገራት የሚሰጥ ድጋፍንም ከሚቀጥለው ዓመት አንስቶ አርባ በመቶ ለማሳደግ ስምምነት ላይ ተደርሷል ብለዋል።

ከዚህ ድጋፍም ከአፍሪካ ማዕከል በደንብ የምትጠቀመው ኢትዮጵያ ናት። ጉብኝታችን የእስካሁን ትግበራን ተመልክተን ለቀሪው የበጀት ውሳኔ ለማድረግ እንዲረዳን ነው የመጣነው። በጤና ዘርፍ የንብረት አመዘጋብ ሥርዓትን ለመተግበር ከጤና ሚኒስቴር አመራሮች ጋር በነበረን ውይይት ተስማምተናል ብለዋል።






# በኦሮሚያ በመኸር ወቅት የለማውን የስንዴ ምርት መሰብሰብ ተጀመረ

ማርቆስ በላይ

አሳሳ፡- በ2015/16 የምርት ዘመን የመኸር ወቅት የለማውን የስንዴ ምርት የመሰብሰብ ሥራ መጀመሩን የኦሮሚያ ክልል አስታወቀ።

በኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ የተመራ ልዑክ በክላስተር የለማ የመኸር ስንዴ ምርት የመሰብሰብ ዘመቻን በምዕራብ አርሲ ዞን ገደብ አሳሳ ወረዳ ትናንት አስጀምሯል።

በወቅቱ አቶ ሽመልስ አብዲሳ እንደገለጹት፤ ፤ በክልሉ በ2015/2016 የመኸር ወቅት ከለማው ስንዴ ከ81 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ይጠበቃል።

በ2015/2016 የመኸር ወቅት በተሠራው ሥራ ሁለት ነጥብ አራት ሚሊዮን ሔክታር መሬት ስንዴ መልማቱን አመልክተው፤ ከዚህም ከፍተኛ ምርት ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል ብለዋል።

በክልሉ ሰባት ሺህ ሔክታር መሬት የተጀመረውን የበጋ መስኖ የስንዴ ልማት፤ በአሁኑ ጊዜ ወደ ሁለት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሔክታር መሬት ለማስፋት ተግባራዊ ሥራ መጀመሩን ገልጸዋል።

በአጠቃላይ በ2015/16 የምርት ዘመን በመኸርና በበጋ የመስኖ የስንዴ ምርት አምስት ሚሊዮን ሔክታር መሬት በማልማት 180 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት ታቅዶ እየተሠራ መሆኑን አስታውቀዋል።

በስንዴ ልማት ላይ በተሠራው ሥራ ከውጭ የሚገባውን ምርት በሀገር ውስጥ መተካት መቻሉን አውስተው፤ የስንዴን ምርት ወደ ውጭ ሀገራት መላክ መጀመሩን አስታውቀዋል።

በክልሉ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በትራክተር ማረስና በመስመር መዝራት ላይ ያለውን ተሞክሮ ማስፋት እንደሚገባ በመግለጽ፤ ምርጥ ዘርን ጨምሮ ማዳበሪያ መጠቀምና ምርት ሲደርስ በኮምባይነር መሰብሰብ እንደሚገባ አመላክተዋል።

እንደ ክልል በግብርናው ዘርፍ 28 ኢኒሼቲቮች ታቅደው ወደ ሥራ ተገብቷል ያሉት አቶ ሽመልስ፤ ከተጀመሩት ኢኒሼቲቮች መካከል የስንዴ ልማት አንዱ ነው ብለዋል።

የተዘጋጁት ኢኒሼቲቮች የክልሉን አየር ንብረት መሠረት ያደረጉ መሆናቸውን ተናግረው፤ ባለፉት ዓመታት በሁሉም የልማት ሥራዎች ተጨባጭ ውጤት መገኘቱን አስገንዝበዋል።

የተጀመሩት ኢኒሼቲቮችን በማስቀጠል አርሶአደሩን በስፋት ሜካናይዜሽንን ጥቅም ላይ እንዲያውል እየተሠራ ይገኛል ያሉት አቶ ሽመልስ፤ የምርት አሰባሰብ ሥራው በኮምባይነር እንዲከናወን ሰፊ ዝግጅት መደረጉንም ተናግረዋል።

በምርት መሰብሰብ ማስጀመሪያ መርሃግብሩ ላይ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳን፣ በብልጽግና ፓርቲ የኦሮሚያ ክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ፍቃዱ ተሰማን እንዲሁም የተለያዩ የፌዴራልና የክልሉ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ተገኝተዋል።

# የድሬዳዋ ነጻ የንግድ ቀጣና በሩብ ዓመቱ አምስት ሚሊዮን ዶላር ገቢ አግኝቷል

ሞገስ ጸጋዬ

ድሬዳዋ፡- የድሬዳዋ ነጻ የንግድ ቀጣና በመጀመሪያው ሩብ ዓመት አምስት ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ማግኘቱን አስታወቀ።

የድሬዳዋ ነጻ የንግድ ቀጣና ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ካሚል ኢብራሂም እንደገለጹት፤ በነጻ የንግድ ቀጣናው ውስጥ ገብተው ሥራ የጀመሩ ባለሀብቶች የተለያዩ ተኪና ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶች እያመረቱ ይገኛሉ። በዘንድሮ በጀት ዓመት በመጀመሪያው ሩብ ዓመት ብቻ የድሬዳዋ ነጻ የንግድ ቀጣና ውስጥ ተመርተው ለውጭ ገበያ ከቀረቡ ምርቶች አምስት ሚሊዮን ዶላር ገቢ ማግኘት ተችሏል።

ነጻ የንግድ ቀጣናው በሶስት ዘርፎች አተኩሮ የሚሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ እነዚህም የአምራች፣ የንግድና የሎጂስቲክ ዘርፎች መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

በአሁኑ ጊዜ የአምራች ዘርፍ ወደ ሥራ ገብቷል ያሉት አቶ ካሚል፣ በዚህ ዘርፍ ብቻ ካሉ 15 የማምረቻ ሼዶች ውስጥ 10 ሼዶች በባለሀብቶች መያዛቸውን ተናግረዋል። ነጻ የንግድ ቀጣናውን በሙሉ አቅሙ ወደ ሥራ ለማስገባት ጥረቶች እየተደረጉ መሆኑን ጠቁመዋል።

እንደ ስራ አሥኪያጁ ገለጻ፤ በነጻ ንግድ ቀጣና ውስጥ ያሉ ባለሀብቶች በተለያዩ የአምራች ዘርፎች ላይ ተሰማርተው ተኪ ምርቶችን እያመረቱ ነው። በአምራች ዘርፉ ተኪ ምርቶችን ከማምረት ጎን ለጎንም ለውጭ ገበያ




የሚቀርቡ ምርቶችን በማምረት ለሀገር ኢኮኖሚ ዕድገት ትልቅ ሚና እየተጫወተ ነው።

የድሬዳዋ ነጻ የንግድ ቀጣና በ2014 ዓ.ም ወደ ሥራ መግባቱን የጠቀሱት ሥራ አስኪያጁ፣ ባሳለፍነው አንድ ዓመት የተለያዩ መተዳደሪያ ደንቦችን ማዘጋጀት መቻሉን አመልክተዋል።

የነጻ ንግድ ቀጣናውን ውጤታማነት ለማሳደግ ከተለያዩ ሀገራት ተሞክሮዎችን በመውሰድ ተቀምረው ተግባራዊ በመደረግ ላይ መሆናቸውን ጠቁመው፤ ለነጻ የንግድ ቀጣና የሚሆኑ መሠረተ ልማቶችን መዘርጋት እንደ ዋና ሥራ ተይዞ ሲሠራ መቆየቱን አስረድተዋል።

ነጻ የንግድ ቀጣናው እ. ኤ. አ ከ2016 ጀምሮ በኢንዱስትሪ ፓርክነትና ከአንድ ዓመት በፊት ጀምሮ ደግሞ በነጻ የንግድ ቀጣናነት እየሠራ የሚገኝ መሆኑን አንስተው፤ እስካሁን ድረስም ከሁለት ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ ማስገኘት መቻሉን ተገልጿል።

# ሀገራዊ ምክክርና የሽግግር ፍትህ በኢትዮጵያ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ

መዓዛ ማሞ

አዲስ አበባ፡- ሀገራዊ ምክክርና የሽግግር ፍትህ በኢትዮጵያ የሚታዩ ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት ቁልፍ ሚና እንደሚጫወቱ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ገለጸ።

75ኛውን የሰብዓዊ መብቶች ቀን በማስመልከት ትናንት ሀገር ሀቀፍ ጉባዔ ተካሂዷል።

75ኛውን የሰብዓዊ መብቶች ቀን በማስመልከት በተካሄደው ጉባዔ ላይ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ዶክተር ዳንኤል በቀለ እንዳሉት፤ አሁን ላይ በኢትዮጵያ እየታዩ ያሉ ግጭቶችን በዘላቂነት ለመፍታት ሀገራዊ ምክክርና የሽግግር ፍትህ ወሳኝ ሚና አላቸው። እውነትን በመፈለግና የሀገራዊ መግባባትን በመፍጠር በኢትዮጵያ ያሉትን ችግሮች ይፈታሉ ተብሎ ይጠበቃል።

የኢትዮጳያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን በችግር ውስጥ ያሉ ዜጎች እፎታ እንዲያገኙ ግጭቶች በሰላማዊ መንገድ በውይይት መፈታት አለባቸው ብሎ እንደሚያምን ገልጸው፤ ሁሉም ወገን ለዚህ ውይይት በሩን ክፍት ሊያደርግ ይገባል ብለዋል።

በተለይ ሀገራዊ ምክክሩና የሽግግር ፍትህ ሥራዎች ስኬታማ እንዲሆኑና ችግሮች እንዲፈቱ ሁሉም ወገን የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣም ጠይቀዋል።

ኢትዮጵያ ለሰብዓዊ መብቶች ጥበቃ የጀርባ አጥንት የሆነውን አለምአቀፉን የሰብዓዊ መብቶች ስምምነት (UDHR) ቀድመው ከፈረሙ ሶስት ሀገራት አንዷ መሆኗን ዋና ኮሚሽነሩ ተናግረዋል።

75ኛውን የሰብዓዊ መብቶች የምስረታ ቀን በማስመልከት ትናንት የተካሄደውን አገራዊ ጉባዔ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን እና የተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብቶች ቢሮ በትብብር የተዘጋጀ እንደሆነ ታውቋል። ቀኑ በመጪው ታህሳስ 1 እና 2 በጄኔቫ እንደሚከበር ተጠቁሟል።

በመድረኩ የተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብቶች የምስራቅ አፍሪካ ቢሮ ከፍተኛ ኮሚሽነር የሆኑት ሚስተር ማርሴል ከሊሜንት በተወካያቸው አማካኝነት መልእክት አስተላልፈዋል። በመልዕክታቸውም ኢትዮጵያ ለምታካሂደው የሽግግር ፍትህ ድጋፍ እንደሚያደርጉ ገልጸዋል።

በመድረኩ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን፣ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ባለሥልጣንና የመገናኛ ተቋማት ሕብረት ስለተቋማቸው ጽሁፍ ያቀረቡ ሲሆን አሁን ላይ ያለው የሰብዓዊ መብት ሁኔታም በጽሁፋቸው ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል።

በጉባዔው የፍትህ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ አለማየሁ አግደው፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት አበባ እምቢአለ፣ የኢትዮጵያ የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ዋና እንባ ጠባቂ ዶክተር እንዳለ ኃይሌ ፣ የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርኣያ እንዲሁም የዓለምአቀፍ ድርጅቶች ተወካዮችና አምባሳደሮች ተገኝተዋል።

ዜና

# የቼክ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር ፒትር ፊያላ ለይፋዊ የሥራ ጉብኝት አዲስ አበባ ገቡ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ለሁለት ቀናት የሥራ ጉብኝት ወደ ኢትዮጵያ የመጡትን የቼክ ሪፐብሊኩን ጠቅላይ ሚኒስትር ፒትር ፊያላን ትናንት ማምሻውን በቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ተቀብለዋቸዋል፡፡

የቼክ ሪፐብሊኩ ጠቅላይ ሚኒስትር ፒትር ፊያላ ለሁለት ቀናት ለይፋዊ የሥራ ጉብኝት ትናንት አዲስ አበባ መግባታቸውን የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት መረጃ ያመለክታል።

የቼክ ሪፐብሊኩ ጠቅላይ ሚኒስትር ፒትር ፊያላ በአምስት ሀገራት ጉብኝት የሚያደርጉ ሲሆን የመጀመሪያ ጉብኝታቸውን ከኢትዮጵያ ጀምረዋል። ከኢትዮጵያ በመቀጠል በኬንያ፣ በናይጄሪያ፣ በጋና እና በኮትዲቫር ጉብኝ እንደሚያደርጉ ይጠበቃል።

ሁለቱ ሀገራት በልማት ትብብሮች፣ በጤና፣ በማዕድንና በሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ ያላቸውን ትብብር ለማጠናከር እንደሚወያዩ ይጠበቃል። እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ 1947 ኢትዮጵያና የቼክ ሪፐብሊክ የዲፕሎማሲ ግንኙነት መጀመራቸው ይታወቃል።

ቼክ ሪፐብሊክ በዓለም አቀፍ ደረጃ በታሪካዊ እና ባህላዊ ቅርስዎቿ፣ በቢራ ፋብሪካዋ፣ በፊልም ኢንዱስትሪ፣ በጠንካራ የአውቶሞቲቭ ዘርፍ እና በአርኪቴክቸር ትታወቃለች።

ኢትዮጵያና ቼክ ለበርካታ ዓመታት የዘለቀ ታሪካዊና ፈርጀ ብዙ ግንኙነት ያላቸው ሀገራት ናቸው።

ቼክ በግብርና፣በውሃ፣ በትምህርትና በቴክኖሎጂ ዘርፎች ትልቅ ተሞክሮ ያላት ሲሆን እነዚህን ተሞክሮዎች ለኢትዮጵያ ለማካፈልና ኢንቨስት ለማድረግ ፍላጎት እንዳላት ይፋ አድርጋለች፡፡

ቼክ በጤናው ዘርፍም ከኢትዮጵያ ጠንካራ ግንኙነት ያላት ሲሆን በተለይ በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ወቅት ለኢትዮጵያ የህክምና ቁሳቁሶችን ድጋፍ አድርጋለች።

ቼክ ሪፐብሊክ በአዲሱ የአፍሪካ ፕሮግራሟ ከኢትዮጵያ ጋር ላላት ግንኙነት ትኩረት መስጠቷን ማሳወቋ የሚታወስ ነው።

በ2007 ዓ.ም የቼክ ሪፐብሊክ ምክትል ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት ፔተር ድሩላክ አዲስ አበባ መጥተው ይፋዊ የሥራ ጉብኝት አካሂደዋል። በወቅቱ ሁለቱ ሀገራት በንግድ ፣ በኢንቨስትመንትና ፖለቲካዊ መስክ ያላቸውን ግንኙነት ይበልጥ ማሳደግ እንደሚጠበቅባቸው ተናግረው ነበር።

ፔተር ድሩላክ የኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ የሰላምና የልማት ኢንስቲትዩት ባዘጋጀው ውይይት ላይ ተጋብዘው ስለሀገራቸው ታሪክ ጥናታዊ ጽሁፍ ማቅረባቸው የሚታወስ ነው።

# ተስፋ የተጣለበት...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ከምትሰራቸው የግብርና ልማት ሥራዎች አንዱ ደግሞ የሩዝ ልማት ነው፡፡

በኢትዮጵያ አምስት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ለሩዝ ምርት ተስማሚ መሆኑንና ሶስት ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ሄክታር መሬት ደግሞ በመስኖ ማልማት የሚችል አቅም መኖሩን መረጃዎች ያሳያሉ።

ሶስት ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ሄክታር መሬት ተጨማሪ በመስኖ የማልማት አቅም እንዳላት ጥናቱ ይጠቁማል። ጥናቱ ይህ ቢልም ሀገሪቷ አሁንም በየዓመቱ ለሩዝ ግዢ የሚውል በርካታ የውጭ ምንዛሬ ታወጣለች።

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር መረጃ እንደሚያመለክተው ኢትዮጵያ ከ2012 ዓ.ም መጀመሪያ እስከ ግንቦት 2016 ዓ.ም ብቻ አንድ ሚሊዮን 421 ሺህ 517 ነጥብ አምስት ቶን በላይ ሩዝ ከውጭ አስገብታ 37 ቢሊዮን 473 ሚሊዮን 196 ሺህ ብር በላይ ወጪ አድርጋለች።

ኢትዮጵያ ከሶስት ዓመታት ወዲህ የጀመረችው የሩዝ እርሻ የማስፋፋት ሥራ የሀገሪቱ ምግብ ዋስትና ከማረጋገጥ ጎን ለጎን ለሩዝ ግብይት የሚወጣው የውጭ ምንዛሬ በማስቀረት ኢኮኖሚውን መደገፍ እንደሚችል ትልቅ ተስፋ ተሰጥቶታል።

በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የሰብል ምርምር ዳይሬክተር ታዬ ታደሰ (ዶ/ር)፤ አሁን ላይ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሠራበት ያለው የሩዝ እርሻ ተስፋ ሰጪ እንደሆነ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ሃሳባቸውን ሰጥተዋል።

ከከተሞች መስፋፋትና ከምግብ ለውጥ ጋር ተያይዞ የሩዝ ፍላጎት ጨምሯል የሚሉት ዶክተር ታዬ፤ ከ70 እስከ 80 በመቶ የሚሆነው የሩዝ ፍላጎት ከውጭ የሚገባ በመሆኑ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ የሚፈልግ እንደሆነ ይናገራሉ።

ይህንንም ለመተካት ላለፉት ሶስት ዓመታት በትኩረት እየተሠራ ነው። በተለይ በዚህ ዓመት በሀገር አቀፍ ደረጃ በተወሰኑ አካባቢዎች ይለማ የነበረውን የሩዝ እርሻ ወደ ተለያዩ አካባቢዎች መስፋፋቱን ያስረዳሉ።

ምርት እንዳይባክን ተደርጎ መሰብሰብ ከለተቻለና አርሶ አደሩ መፈልፈያ ማሽን እንዲያገኝ ቢመቻች የተዘራው ሩዝ ትልቅ ተስፋ የሚጣልበት እንደሆነም ይገልጻሉ።

በሩዝ ምርት ተጠቃሚ ለመሆን የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን አሳትፎ የተቀናጀ ሥራ ይፈልጋል የሚሉት ዶክተር ታዬ፤ ለተመረተው ምርት የገበያ ትስስር በመፍጠር አርሶ አደሩን ተጠቃሚ ማድረግ ያስፈልጋል ባይ ናቸው።

በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ በግብርና ኮሌጅ መምህርና የብሉ ኢኮኖሚ ሴንተር ኦፍ ኤክሰለንስ ዳይሬክተር አላዩ ያለው (ረ/ፕ) በበኩላቸው፤ በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ በምግብ እራሷን ለመቻል ሩዝ ቀዳሚ አማራጭ የሰብል ዓይነት ማድረግ ተገቢ እንደሆነ ምክረ- ሃሳባቸውን ይለግሳሉ።

በትንሽ መሬት ብዙ ምርት ማግኘት መቻሉና በተቀናጀ መልኩ ከዓሳ ሀብት ጋር በተመሳሳይ ቦታና ጊዜ የሚመረት በመሆኑ ሩዝን ከሌሎች ሰብሎች ተመራጭ ያደርገዋል ባይ ናቸው።

ሩዝንና ዓሳን ጎን ለጎን እንዲመረቱ ማድረግ የሩዝ ምርታማነት እንዲጨምር እንደሚያደርግ በተለያየ ጊዜ በተደረገ ምርምር ታይቷል ይላሉ።

አብዛኛው የኢትዮጵያ የአየር ሁኔታ እንዲሁም የአፈር አይነት ለሩዝ ምርት ተስማሚ ነው የሚሉት ረዳት ፕሮፌሰሩ፤ በዘርፉ ውጤታማ ለመሆን የመሬት ሀብቱን ማወቅና ለአካባቢው ተስማሚ የሚሆን ዘር መምረጥ ተገቢ እንደሆነ ይመክራሉ።

በመኸር እርሻ የተዘራው የሩዝ ሰብል የተወሰነ ዝናብ የሚፈልግ ቢሆንም አሁን ላይ ያለው የሰብል ሁኔታ ከፍተኛ ምርታማነት እንደሚኖር የሚጠቁም ነው ያሉት ደግሞ የፎገራ ሩዝ ምርምርና ሥልጠና ማዕከል ዳይሬክተር ፍስሃ ወረደ (ዶ/ር) ናቸው።

በኩታ ገጠም የተዘሩ የሩዝ እርሻዎች ተስፋ የሚጣልባቸው ናቸው የሚሉት ዶክተር ፍስሃ፤ የሩዝ እርሻ በብዛት ማስፋፋት ካለው የምግብ ዋስትና ከማረጋገጥ በተጨማሪ የሩዝ ሰብል ሲፈለፈል በሚወጣው ተረፈ ምርት የኃይል አማራጭ መጠቀም መቻሉ ሌላኛው ጠቃሚ ጎኑ እንደሆነ ያስረዳሉ።

ሩዝ በምርታማነት መጨመሩ ለውጭ ገበያ ለማቅረብና በምግብ እራስን የመቻል እንቅስቃሴ እንደሚደግፍም ነው የሚናገሩት።

በኢትዮጵያ አምስት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ለሩዝ ምርት ተስማሚ መሆኑንና ሶስት ነጥብ ዘጠኝ ሄክታር መሬት በመስኖ ማልማት የሚችል አቅም እንዳለ ዶክተር ፍስሃ አስታውቀዋል።

በምርምር ቦታው ከ60 እስከ 70 ኩንታል በሄክታር ይገኛል የሚሉት ዶክተር ታዬ፤ በዘርፉ ያለው እምቅ አቅም መጠቀም ከተቻለ በአጭር ጊዜ ሙሉ በሙሉ ከውጭ የሚገባው ምርት ተክቶ ለውጭ ገበያ ማቅረብ እንደሚቻል ይጠቁማሉ።

እንደ አጠቃላይ የሩዝ ምርትን ማስፋፋትና ውጤታማነቱን ማሳደግ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ እምርታ ለማሳደግ አይነተኛው መንገድ መሆኑ ያመላከቱት ምሁራኑ፤ የሩዝን ዘርፈ ብዙ ጥቅም ለማጎልበት በስፋት ማምረት ላይ አሁንም ትኩረት ሊደረግ እንደሚገባ ሃሳባቸውን ሰጥተዋል።

# "የሰብዓዊ ድጋፍን በራስ አቅም መሸፈን የሉዓላዊነትና የክብር ጉዳይ ነው"

*- አቶ ደመቀ መኮንን*

*ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር*

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የሰብዓዊ ድጋፍን በራስ አቅም መሸፈን የሉዓላዊነትና የክብር ጉዳይ ነው ሲሉ የብሄራዊ አደጋ ስጋት አመራር ምክር ቤት ሰብሳቢ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን ገለጹ።

የሰብዓዊ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች ኢትዮጵያ በራሷ ምላሽ የመስጠት አቅም እንድትፈጥር የተቀናጀ ርብርብ እንደሚያስፈልግ ተጠቁሟል።

ብሔራዊ የአደጋ ሥጋት አመራር ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባውን ትናንት አካሂዷል።

የምክር ቤቱ ሰብሳቢ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን በስብሰባው ላይ በሀገሪቱ ባለፉት የለውጥ ዓመታት እየተተገበሩ የሚገኙ የልማት ሥራዎችን በማጠናከር አደጋዎችን መቋቋም የሚችል ሀገራዊ አቅም በመገንባት ላይ ይገኛልም ብለዋል።

በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ ሰብዓዊ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ዜጎች ሕይወት ሳይጠፋና የከፋ ጉዳት ሳይደርስ የተቀናጀ ፈጣን ምላሽ መስጠት እንደሚገባ አንስተዋል።

በክልሎቹ የሚገኙ ተፈናቃዮችን በሚመለከት አፋጣኝ ድጋፍ የሚሹትን በመለየት ዝርዝር እቅድ አዘጋጅቶ ማስፈጸም ይገባልም ብለዋል።

ለዚህም የሚያጋጥሙ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋዎችን በዘላቂነት በራስ አቅም መቋቋምና ምላሽ መስጠት የሚያስችል ጠንካራ ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል ብለዋል።

በሀገሪቱ ባለፉት የለውጥ ዓመታት እየተተገበሩ የሚገኙ የልማት ሥራዎችን በማጠናከር አደጋዎችን መሸከም የሚችል ሀገራዊ አቅም በመገንባት ላይ መሆኑን ጠቅሰው ለስኬቱ የሁሉም ርብርብ የሚያስፈልግ መሆኑን ገልጸዋል።

በየዘመኑ በርካታ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች ማጋጠማቸውን ጠቅሰው ህዝቡ አደጋዎችን በፅናት በመቋቋም መሻገሩን አስታውሰዋል።

በመሆኑም ይህን ጠንካራ ሀገርና ህዝብ የሚመራው አመራር ጠንካራ ተቋማትን በመገንባት ከተረጂነት ለመላቀቅ በጋራ መስራት ይጠበቅበታል ነው ያሉት።

ክልሎች በየአካባቢያቸው ችግሮች እንዳይከሰቱ ሲከሰቱም በራሳቸው አቅም ምላሽ ለመስጠት በቁርጠኝነት መሥራት እንዳለባቸውም አስገንዝበዋል።

ተፈናቃዮች ተጠልለው በሚገኙበት አካባቢ በተለይም ወጣቶቹ የሥነ-ልቦና ድጋፍ በመስጠት በልማት ሥራ ላይ የበኩላቸውን እንዲያበረክቱ ማድረግ እንደሚገባም ነው ያነሱት።

የብሔራዊ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ዶክተር ሽፈራው ተክለማርያም "ሰብዓዊ ድጋፍ፣ ገመናና ሉዓላዊነት፣ ፈተናዎችና የመውጫ መንገዶች" በሚል ርዕሰ ጉዳይ ላይ የመወያያ ፅሁፍ አቅርበዋል።

በፅሁፋቸውም ኢትዮጵያ ላለፉት በርካታ ዓመታት አደጋ ባጋጠማት ጊዜ ሁሉ በተረጂነት መቆየቷን ጠቅሰው ይህም ሉዓላዊነታቸው ምሉዕ እንዳይሆን አድርጓል ነው ያሉት።

በመሆኑም ክብራችንን ለማስጠበቅና ከተረጂነት ለመላቀቅ የሰብዓዊ ድጋፍ ፍላጎታችንን በራስ አቅም መሸፈን እንደሚገባ ተናግረዋል።

ሰብዓዊ ድጋፍን በራስ አቅም መሸፈን ብሔራዊ አርበኝነትን የሚጠይቅ ተግባር መሆኑንም መገንዘብ አስፈላጊ ነው ብለዋል።

በተለያየ ችግር ርዳታ የሚያስፈልጋቸው ዜጎች ለረጅም ጊዜ ርዳታ ጠባቂ እንዳይሆኑ በአምራችነት ማሳተፍ ተጨማሪ ምርት መፍጠር እና የፋይናንስ አቅርቦትን መሠረት ማስፋት በግብ መቀመጣቸውን ጠቅሰዋል።

ትክክለኛ የተረጂዎችን ቁጥር መለየት፣ ርዳታን ላልተፈለገ ዓላማ የሚያውሉትን ተጠያቂ ማድረግ፣ ተቋማዊ አደረጃጀትን ማሻሻል፣ ቅንጅታዊ አሠራርን ማጠናከርና ከተረጂነት አስተሳሰብ መላቀቅም እንደሚገባ ጠቁመዋል።

በአሁኑ ወቅት የሰብዓዊ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች አፋጣኝ ድጋፍ እየተደረገ እንደሚገኝም ኮሚሽነሩ ተናግረዋል።

በስብሰባው የተሳተፉ ሚኒስትሮች በበኩላቸው እንደ ሀገር የሚያጋጥሙ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋዎችን ሀገሪቱ የመቋቋም እምቅ አቅም ቢኖራትም ወደ ተግባር አለወጥነውም ብለዋል።

ለአብነትም የተሟላ የመስኖ መሠረተ ልማት የተዘረጋለት 1 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ውስጥ እስካሁን የለማው 65 በመቶው ብቻ መሆኑን ያነሱት የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ሚኒስትሯ ኢንጂነር አይሻ መሐመድ ናቸው።

በመሆኑም ቀሪ ያለማውን መሬት በመንግሥት ደረጃ እንዲለማ በማድረግ ሀገራዊ የመጠባበቂያ እህል ክምችትን ማስፋት ተገቢ ይሆናል ነው ያሉት።

የገንዘብ ሚኒስትሩ አህመድ ሽዴ በበኩላቸው፤ ክልሎች የተመደበላቸው የርዳታ በጀት በአግባቡ ማስተዳደር እንዳለባቸው አሳስበዋል።

አክለውም ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ የተመረተው እህል ወደ ገበያ እንዲቀርብም ከወረዳ እስከ ፌዴራል ያሉ የአስተዳደር መዋቅሮች በአግባቡ መሥራት አለባቸው ብለዋል።

የሰላም ሚኒስትሩ ብናልፍ አንዱዓለም፤ በየጊዜው በሰው ሰራሽ ምክንያቶች የሚፈናቀሉ ዜጎች ጉዳይ ሁሉንም የሚያሳስብና የጋራ መፍትሄ የሚሻ መሆኑን ተናግረዋል።

ለዜጎችን መፈናቀል ምክንያት የሆኑ ችግሮችን በጋራ እልባት በማበጀትና መልሶ በማቋቋምም በተለይም ክልሎች ሚናቸውን እንዲወጡም አስገንዝበዋል።

በመድረኩ የተሳተፉ የክልል ከፍተኛ አመራሮች በበኩላቸው፤ በተፈጥሮና የሰው ሰራሽ አደጋዎች እየተፈጠሩ ያሉ ችግሮች ለክልሎችም ለሀገርም ጫና መፍጠራቸውን ጠቅሰዋል።

አደጋዎቹ ድህነትን የሚያባብሱ፣ የኢኮኖሚ ሉዓላዊነትን በአጭር ጊዜ እንዳይረጋገጥ እንቅፋት የሚፈጥሩ እና የብሔራዊ ደህንነት ስጋት በመሆናቸው በተደመረ አቅም ከችግሮቹ ለመሻገር መትጋት አለብን ብለዋል።

በመሆኑም ክልሎች በመተጋገዝ፣ ማህበረሰቡን ከተረጂነት በማላቀቅ፣ የሌማት ትሩፋት፣ የበጋ መስኖና ሌሎችንም እምቅ የልማት አቅሞችን አሟጦ መጠቀም ከሁላችን ይጠበቃል ማለታቸውን ኢዜአ ዘግቧል፡፡

# መንግሥት ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

የታለመለት ነዳጅ ድጎማ በ2014 ሐምሌ ወር ተግባራዊ የተደረገ ሥርዓት ነው። በ2016 የመጀመሪያው የሩብ ዓመትም በታለመለት የነዳጅ ድጎማ መንግሥት ከስድስት ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ብር በላይ ድጎማ አድርጓል፡፡

የታለመለት ነዳጅ ድጎማ በ2014 ሐምሌ ወር ተግባራዊ ከተደረገበት ጀምሮ እስከ መስከረም 30 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ከ23 ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር በላይ ለተሽከርካሪዎች ድጎማ መደረጉን አመልክተው፤ በተያዘው ዓመት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ከስድስት ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ብር በላይ ለተሽከርካሪዎች ድጎማ መደረጉን አቶ ሰልማን ተናግረዋል።

መንግሥት የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ላይ የተሰማሩ ተሽከርካሪዎችን በመለየት የነዳጅ ድጎማ ተጠቃሚ እንዲሆኑም አድርጓል ብለዋል።

እንደ አቶ ሰልማን ገለፃ፤ በድጎማ ሥርዓቱ የሚካተቱ ተሽከርካሪዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል። የነዳጅ ድጎማ ሥርዓቱ ከተዘረጋ አንስቶ እስከ መስከረም 30 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ 240 ሺህ 890 ተሽከርካሪዎች ወደ ዲጂታል ሥርዓቱ ገብተዋል። በሩብ ዓመቱ ዘጠኝ ሺህ 872 ተሽከርካሪዎች ለድጎማ ተመዝግበዋል።

በአዲስ አበባና በሁሉም የክልል ከተሞች ተሽከርካሪዎች በሥርዓቱ እንዲመዘገቡ ተደርጓል ያሉት አቶ ሰልማን፤ በአጠቃላይ ከተመዘገቡት ተሽከርካሪዎች ውስጥ 197 ሺህ 454 የሚሆኑት የነዳጅ ድጎማ ተጠቃሚ ሆነዋል። ከዚህ ውስጥ ከ20 ሺህ በላይ የሚሆኑት ተሽከርካሪዎች በሩብ ዓመቱ የድጎማ ተጠቃሚ የተደረጉ ናቸው ብለዋል።

በመላ ሀገሪቱ የሚገኙ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ተሽከርካሪዎች የታለመለት የነዳጅ ድጎማ ተጠቃሚ ለመሆን አስፈላጊ መረጃዎችን በመስጠት በኢትዮ ቴሌኮም የሽያጭ ማዕከላት በኩል ምዝገባ ማድረጋቸውን አስታውሰው፤ በዚህም እስከ መስከረም 30 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ከ81 ቢሊዮን ብር በላይ የነዳጅ ግብይት መፈጸሙን ገልጸዋል።

# አገልግል

የቅዳሜ መጽሔት

የቁምነገር ገጾች




## «የኮሚሽኑ ዋና ተግባር በየአካባቢው ለግጭት የዳረጉንን ጉዳዮች ወደ ሀገራዊ ምክክር አጀንዳነት ማምጣት ነው»

- ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርዓያ

ገጽ 6



ዘራፊው ተሳፋሪ

ገጽ 9



ተልዕኮዋን የጨረሰችው ETRSS-1

ገጽ 18


ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል፣ኪነጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

አፍሪቃዊቷ መልኅቅ


# የዓለም የቱሪስት መዳረሻዋ አዲስ አበባ

**ዳንኤል ዘነበ**

ኢትዮጵያ ፈርጀ ብዙ የቱሪዝም ሀብቶች ባለቤት ብትሆንም ዘርፉን በሚገባ አልምቶ ተገቢውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንዲያመነጭ ከማድረግ አኳያ ሰፊ ክፍተቶች እንዳሉ ይገለጻል። ይሁን እንጂ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በመንግሥት በኩል ይህን ታሪክ መቀየር የሚያስችሉ እንቅስቃሴዎች መታየት ጀምረዋል። በኢትዮጵያ የተደረገው የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ (Homegrown Economic Reform) ውስጥ ልዩ ትኩረት ከተሰጣቸው አምስቱ የኢኮኖሚ መሰረቶች ውስጥ ማለትም ማዕድን፣ ማኑፋክቸሪንግ ግብርና፣ አይ.ሲ.ቲ ቱሪዝም አንዱ ነው።

በዚህ መልኩ ትኩረት በመስጠት ለዘርፉ ፈጣን እድገት ዋስትና የሚሆኑ ሞዴል የመዳረሻ ልማት ፕሮጀክቶችም ገበታ ለሀገር፣ ገበታ ለትውልድ እና ገበታ ለሸገር በሚል እየተተገበሩ ይገኛሉ። እንደ ከተማ ደግሞ ፓርኮች ፣ አደባባዮች ፣ ሙዚየሞችና ተጨማሪ ማራኪ የመስህብ ቦታዎች እንዲለሙ ተደርጓል። ይህም በጥቂት ሙዚየሞች ላይ ተንጠልጥሎ የነበረው የከተማዋን የቱሪዝም መዳረሻ ወደ ባለብዙ አማራጭነት ያሸጋገረ መሆኑን የሚናገሩት የአዲስ አበባ ባህል ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ሀፍታይ ገብረእግዚአብሔር ናቸው።

አቶ ሀፍታይ ፣ በዓለም ለ44ኛ በሀገራችን ደግሞ ለ36ኛ ጊዜ "ቱሪዝም ለአረንጓዴ ልማት - አረንጓዴ ልማት ለቱሪዝም" Tourism and Green Investment' በሚል መሪ ቃል ከጥቅምት 20 እስከ 22 ቀን 2016 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የተከበረውን የዓለም የቱሪዝም ቀን አስመልክተው ባስተላለፉት መልዕክት እንደገለጹት ፤ አዲስ አበባ ከተማ የበርካታ ተፈጥራዊ እና ሰው ሰራሽ የቱሪዝም መስህብ ፀጋዎች ባለቤት ከመሆን ባሻገር ያሏትን እምቅ የቱሪዝም ሀብቶች አልምቶ ለከተማዋ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ ፋይዳ ሊያመጣ በሚችል መልኩ መጠቀም የሚያስፈልግበት ወቅት ላይ ተደርሷል። ይህንንም በመረዳት እንደተቋም የተለያዩ የሪፎርም ሥራዎችን በማከናወን ውጤት እየተመዘገበ መሆኑን ጠቁመዋል።

"ቢሮው ከ2013 ዓ.ም እስከ 2015 ዓ.ም ባደረገው እንቅስቃሴ ለ5 ሺህ 112 የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አዲስ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሰጥቷል። ለ14 ሺህ 760 ተቋማት ደግሞ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ዕድሳት አድርጓል። በዚህም በቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ ከአገልግሎት አሰጣጥ አንፃር የሚስተዋሉ ችግሮች እንዲሻሻሉ የራሱን አስተዋፅኦም አድርጓልም " ብለዋል ።

አቶ ሀፍታይ ፣ ባለፉት ሦስት ዓመታት የሀገር ውስጥ ጎብኚ ቁጥር 14 ሚሊዮን 484 ሺህ 381 ፣ የውጭ ሀገር ጎብኚ ቁጥርም 1 ሚሊዮን 85 ሺህ 129 የደረሰበት ሲሆን ከውጭ ቱሪስቶች ወደ ከተማው ኢኮኖሚ 64 ነጥብ 06 ቢሊዮን ብር ፈሰስ የሆነበት ወቅት እንደነበር አስታውሰው ፣ ለዚህ ስኬት መመዝገብ የከተማችን አስተዳደር ለከተማው አዳዲስ የመዳረሻ ልማት ፕሮጀክቶች ትኩረት መስጠቱ ፣ በከተማዋ ያለው ሰላም እና የህብረተሰቡ እንግዳ ተቀባይነት በጉልህ የሚጠቀሱ ምክንያቶች መሆናቸውን አመልክተዋል።



**አቶ ሀፍታይ ገብረ እግዚአብሔር**
**የአዲስ አበባ ባህል ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ምክትል ኃላፊ**

በተጨማሪም በእነዚህ ዓመታት ትኩረት ተደርጎ ከተሠሩት ሥራዎች መካከል ለከተማችን ህብረተሰብ በዘርፉ አዳዲስ የሥራ ዕድሎችን በመፍጠር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ መሆኑን ገልጸዋል። በዚህም ለ34 ሺህ 143 ለከተማችን ሥራ አጥ ወጣቶች በቋሚና በጊዜያዊነት የሥራ ዕድል በመፍጠር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ እንደተቻለም ምክትል ኃላፊ አስታውቀዋል ።

በመጨረሻም ፤ "ቱሪዝም በባህሪው ሰው ተኮር ከመሆኑ ጋር በተያያዘ በቀጣይም የከተማችንን ህብረተሰብ ተጠቃሚ የሚያደርጉ ፕሮክቶችን በመቀየስና ተግባራዊ በማድረግ፣ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ጎብኚን ቁጥር በመጨመርና የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራቱን በማሻሻል አዲስ አበባ ከዘርፉ መጠቀም ባለባት ደረጃ መጠቀም እንድትችል ትኩረት ሰጥተን በጋራ መሥራት ይጠበቅብናል" ሲሉ አቶ ሀፍታይ መልዕክታቸውን ቋጭተዋል።

በአጠቃላይ ኢትዮጵያ የዓለም የቱሪዝም ድርጅት መስራችና አባል መሆኗና ቱሪዝምን ቀድማ ማስተዋወቋ በቱሪዝም የዳበረች አድርጓታል። ሀገራችን የዓለም የቱሪዝም መዳረሻ ብቻ ሳትሆን ወደ መስህብነት እየተለወጠች ትገኛለች። በተለይም አዲስ አበባ ከተማ ከአምስት ዓመት ወዲህ እየተሠሩ ያሉ መዳረሻዎች የዓለም ቱሪስቶችን ቀልብ እየሳበች መሆኑ ይታወቃል። በቅርቡም የዓለም የቱሪዝም ፌዴሬሽን አባልነት ከተማዋ የተቀላቀለች ሲሆን ፣ ይህም በዓለም አቀፍ ደረጃ ለከተማ የተሰጠው ትኩረት የሚያሳይ ነው። በቱሪዝም ዘርፍ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ መስራት መቻሉን ተከትሎ የተገኘ ውጤት ሲሆን ፤ በቀጣይም ቢሮው ከተማዋ ያላትን የቱሪዝም ሀብቶች በማስተዋወቅ የሀገር ውስጥና የውጭ ጎብኚዎችን ቁጥር ለመጨመር የጀመረውን ሥራ አጠንክሮ እንደሚቀጥልም ይጠበቃል።

**ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች**

# የዘመን እንግዳ

# ‹‹የኮሚሽኑ ዋና ተግባር በየአካባቢው ለግጭት የዳረጉንን ጉዳዮች ወደ ሀገራዊ ምክክር አጀንዳነት ማምጣት ነው››

*-ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርዓያ*

**እፀገነት አክሲሱ**

*ሀገራዊ ምክክር ስር የሰደዱ ሀገራዊ አለመግባባቶችን፣ ግጭቶችን ለመፍታት ጥቅም ላይ የሚውል አንድ አይነት የግጭት መፍቻ ዘዴ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ድርድር (negotiation) የተለያየ ጥቅምና ፍላጎት የሚወክሉ አካላት በሰጥቶ መቀበል መርሕ ልዩነቶቻቸውን የሚፈቱበት ዘዴ ነው፡፡ ሌላው እርቅ (reconciliation) ሲሆን የደረሰ በደል ላይ ጥልቅ ውይይት ማድረግና በመተማመን ይቅር በመባባል ስምምነትን ማስፈኛ ዘዴ ነው። የማስማማት (mediation) የግጭት መፍቻ ዘዴ በሦስተኛ ወገን አማካኝነት ልዩነትን ለማስወገድ ጥቅም ላይ የሚውል ነው፡፡*

*ከግጭት መፍቻ ዘዴዎች መካከል አንዱ የሆነውን ሀገራዊ ምክክር (national dialogue) ለማድረግ እንዲቻል የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን ማቋቋያ አዋጅ አፅድቆ ወደ ሥራ ከገባ አስራ ሰባት ያህል ወራቶች ተቆጥረዋል፡፡*

*የኢትዮጵያ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ተግባራዊ ያደረገው ዘዴ አካታች ሀገራዊ ምክክርን ሲሆን ሀገራዊ ምክክር በሀገራችን ወቅታዊና ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ተመራጭ ግጭት መፍቻ ዘዴ ነው፡፡ ሀገራዊ ምክክር አንድ ወጥ ሀሳብ እና አንድ ወገን ብቻውን የሚመክርበት ሳይሆን በየአጀንዳው የተለያዩ ሀሳቦች፣ ጥቅሞች፣ ፍላጎቶችና መብቶች የሚወከሉበትና ምክክር የሚደረግበት፣ እነዚህን ሀሳቦች የሚያንጸባርቁ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚወከሉበት ብዝኃነት ያለው መድረክ ስለመሆኑም ተደጋግሞ ይነሳል ፡፡*

*በዚህም በሀገራችን የሚስተዋሉ መሠረታዊ ችግሮችን እና ልዩነቶችን ወደ ጠረጴዛ ዙሪያ በማምጣት፣ የተለያዩ ጥቅሞችና የኅብረተሰብ ክፍሎች በሚሳተፉበት ምክክር የጋራ መፍትሔ ለማምጣት የተመረጠና ጥቅም ላይ የሚውል ዘዴ ሆኖ እየተተገበረ ነው፡፡*

*የሀገራዊ ምክክር ጥቅም በዋናነት ግጭትን ለማስወገድ፣ የፖለቲካና ዴሞክራሲ ሽግግርን ለማሳለጥ የሚጠቅም ነው። በተለይም ግጭቶችን ለመከላከል፣ ለማስተዳደር እና ለመፍታት አይነተኛ መሣሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃም በበርካታ ሀገራት በተለያዩ ጊዜያት በተለያየ መነሻ ምክንያቶች ሀገራዊ ምክክሮችን አካሂደዋል። የተወሰኑት የተሳካላቸው ሲሆን በተወሰኑት የሚፈለገውን ግብ ሳያሳካ ቀርቷል፡፡*

*የሀገራዊ ምክክር ዓላማዎች መሠረታዊ የሆኑ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ያሉ ልዩነቶችን በማጥበብ መግባባትን ለመፍጠር፣ በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከልና ከመንግሥት ጋር ያለን ግንኙነት ለማሻሻል፣ መተማመንን ለማጎልበት፣ የመነጋገር የፖለቲካ ባሕልን ለማስፈን፣ ዘላቂ ሰላምን ለማምጣት፣ ጠንካራና ቅቡልነት ያለው ሀገረ መንግሥት በጋራ ለመገንባት፣ ልዩነቶችን በሰላማዊና ሕጋዊ መንገድ ለመፍታት፣ የዴሞክራሲና የፖለቲካ ሽግግር ለማስቻል፣ ልማትን ለማፋጠን የሚጠቀሱ ናቸው፡፡*

*በተጨማሪም የሀገራዊ ምክክር ዓላማ መሠረታዊ አለመግባባቶች፣ ልዩነቶችና ግጭቶች ምን እንደሆኑና መሠረታዊ ምክንያታቸውን መለየት እና በእነዚህ ላይ ልዩነቶችን በምክንያታዊ፣ በሠለጠነ፣ በመቻቻል መንገድ የጋራ መግባባቶች ላይ ለመድረስ እና የግጭቶቹ መንስኤ የሆኑ ልዩነቶችን ለማጥበብ ካልሆነም በልዩነቶች ላይ በመስማማት በሀሳብ ለመለያየት ብሎም ይህን የሀሳብ ልዩነት በዴሞክራሲያዊ፣ ሰላማዊና ሕጋዊ መንገድ መፍታት የሚቻልበትን ዘዴ በጋራ በመቀየስ ተግባራዊ ለማድረግ ለመግባባት የጋራ ጥረት የሚደረግበት መድረክ ነው፡፡*

*ሀገራዊ ምክክር ዓላማን ለማሳካት ምክክሩ ሊከተላቸው የሚገቡ መርሆች እንዳሉት በግልጽ የተቀመጠ ሲሆን በዚህም መሠረት አካታችነት፣ ግልጽነት፣ ተአማኒነት፣ መቻቻልና እና መከባበር፣ ምክንያታዊነት፣ የምክረ ሀሳቦች ተግባራዊነት እና ዓውድ ተኮርነት፣ ገለልተኛ አመቻች፣ የአጀንዳ ጥልቀትና አግባብነት፣ ዴሞክራሲያዊነት፣ የሕግ የበላይነት ይጠቀሳሉ፡፡ ከዚህ አንፃር ኮሚሽኑ ተሳታፊዎች በቅን ልቦና እንዲሳተፉ እና ፍትሐዊነት መርሆችን ሊያካትት ይችላል።*

*የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽንም ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ምን ዓይነት ተግባራትን አከናውኗል? በውጤት ደረጃስ ያለበትና አሁን እየሠራ ያለውን ሥራ በተመለከተ ከኮሚሽኑ ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርዓያ ጋር ቆይታን አድርገናል።*



ፎቶ፡ ሐዲስ አብርሃ

> **ኮሚሽኑ ሥራ ሲጀምር አብረውን ለመሥራት ፈቃደኛ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሦስት የነበሩ ሲሆን ባከናወናቸው ተከታታይ ሥራዎች ግን በአሁኑ ወቅት የፓርቲዎቹ ቁጥር 47 ደርሷል፡፡ ሥራ ስንጀምር ከእኛ ጋር አብሮ ለመሥራት ፈቃደኛ የሆኑት ፓርቲዎች ከሦስት ባለመብለጣቸው በወቅቱ አስደንጋጭ ሁኔታ ውስጥ ገብተን ነበር**

**አዲስ ዘመን፡- በሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ እስከ አሁን የተከናወኑ ተግባራት ምን መልክ አላቸው?**

**ፕሮፌሰር መስፍን፡-** የኢትዮጵያ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን በአዋጅ ተቋቁሞ ወደ ሥራ ከገባ 17 ወራት አካባቢ እያለፉት ነው። በእነዚህ ጊዜያት ደግሞ የተለያዩ ተግባራትን አከናውኗል፤ በተለይም ሀገር ካለችበት ሁኔታ አንጻር ምን ዓይነት ተግባር ማከናወን ነው የሚጠበቅበት? የሚለውን በጥልቀት በማየትና በመገምገም ብዙ ርቀቶችን ለመጓዝ ሙከራን አድርጓል።

አሁን ላይ የቅድመ ዝግጅት ጊዜውን አጠናቆ የዝግጅት ምዕራፉንም በማገባደድ ላይ ይገኛል። ይህም ሲባል በመላው ሀገራችን ምን መሠራት አለበት? እነማን ናቸው ተሳታፊ ሊሆኑ የሚገባቸው? የሚለውን የማየትና የመወሰን ሥራንም አብሮ እየሠራም ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የቅድመ ዝግጅት ሥራውን አጠናቆ የዝግጅት ምዕራፉን በማገባደድ ላይ ከሆነ በተለይም በዝግጅት ሥራው ላይ ምን እያከናወነ ነው?**

**ፕሮፌሰር መስፍን፡-** አዎ በመላው ሀገሪቱ ለምክክር ኮሚሽኑ ግብዓት ይሆናሉ ያስፈልጋሉ ሥራውንም ውጤታማ ሊያደርጉ ይችላሉ የተባሉ ሥራዎችን በሙሉ እየሠራን ነው። በተለይም በሀገሪቱ ካሉ ፲ሺ 4 መቶ ወረዳዎች ዘጠኝ ዘጠኝ ባለድርሻ አካላትን የመለየት ሥራ የተሠራ ሲሆን ከእነዚህ ባለድርሻ አካላት ውስጥ ደግሞ አስር አስር ሰው ማለትም ከዘጠና እስከ መቶ ሰው ድረስ እየተመረጠ ነው። እዚህ ላይ ከዘጠና እስከ መቶ ሰው ሲባል ምን ለማለት ነው ብትይ ከባለድርሻ አካላት ዘጠና ተወካዮች ይመረጡና የቀሩት አስሩ ደግሞ በወረዳው ላይ ተፈናቃዮች ካሉ ለእነሱ የሚሰጥ እድል ይሆናል ማለት ነው። ከእነዚህ ሰዎች ደግሞ እንደገና ሁለት ሁለት ሰዎች እንዲመረጡ ይሆናል፤ እነዚህ ሁለት ሰዎች ደግሞ ወደ ክልል በመምጣት የወረዳቸውን አጀንዳ የሚያንጸባርቁ ይሆናል።

**ወደ ገጽ 7 ዞሯል**

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

## ‹‹የኮሚሽኑ ዋና ተግባር በየአካባቢው...

ከ6ኛው ገጽ የዞረ

በነገራችን ላይ በክልል ደረጃ 16 ገደማ ባለድርሻ አካላት የመለየት ሥራ የተሠራ ሲሆን እነዚህ ተቋማት የክልል መስተዳድር ምክር ቤትን ጨምሮ የፖለቲካ ፓርቲዎችንና ሌሎችንም ያቀፈ ነው።

በመሆኑም ከወረዳ የሚነሱት ከክልል ጋር ከሚገኙት ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመሰብሰብ ከወረዳ ጀምሮ እስከ ክልል ድረስ ያላቸውን ሀገራዊ አጀንዳዎች የሚያስረክቡበት ሂደት ይኖራል።

**አዲስ ዘመን፡- እነዚህ ሥራዎች ከተሠሩ የዝግጅት ምዕራፉ ተጠናቋል ማለት እንችላለን?**

**ፕሮፌሰር መስፍን፡-** የዝግጅት ምዕራፉ ተጠናቀቀ የሚባለው አጀንዳዎች ከተሰባሰቡ በኋላ ከወረዳ ጀምሮ ክልል የደረሱ ተሳታፊዎች በሀገራዊ የምክክር ሂደቱ ላይ የሚሳተፉ ሰዎችን መርጠው ሲያጠናቅቁ ነው።

ይህም ሲባል የወረዳ ተሳታፊዎች ክልል ላይ መጥተው አጀንዳዎቻቸውን ከክልል ጋር አብረው ሰጥተው በተመሳሳይ በፌደራል ደረጃ የተለዩ ተሳታፊዎችም አጀንዳቸውን ሰጥተው ካጠናቀቁ በኋላ በክልልና በፌደራል ደረጃ ለዋናው ሀገራዊ ምክክር የሚሳተፉ ይመረጣሉ።

**አዲስ ዘመን ፡- ይህ እንግዲህ በሀገር ውስጥ የሚከናወነው ተግባር ነው፤ ነገር ግን የምክክር ኮሚሽኑ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንንም ለማሳተፍ እቅድ ይዞ ነበርና እዚህስ ላይ የተሠራው ሥራ ምን መልክ ይኖረው ይሆን ?**

**ፕሮፌሰር መስፍን፡-** ከላይ ያነሳነው ወረዳ ክልልና ፌደራል የሚባለውን ሂደት አንዱ ነው፤ በስተመጨረሻም ግን በተለያዩ የዓለም ሀገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን አጀንዳዎቻቸውን እንዲያቀርቡ የሚደረግበት አካሄድም ይኖራል። በጠቅላላው በእስከ አሁኑ ሂደት ተሳታፊዎችን በወረዳ የመለየት በእነዚህ መካከል ደግሞ ሁለት ሁለት ተወካዮቻቸውን እንዲመርጡ ማድረግ ተሠርቷል።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ላይ ሥራው በሁሉም ክልሎች ተዳርሷል ማለት ይቻላል?**

**ፕሮፌሰር መስፍን፡-** አሁን በሰባት ክልሎችና በሁለት ከተማ መስተዳደሮች ላይ ሥራው ተገባዷል። ከእነዚህ ክልሎች መካከልም ሲዳማ፣ ሐረሪ፣ ጋምቤላ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ የሚገኙበት ሲሆን፡፡ በቀጣይ በኦሮሚያ፣ አማራ፣ ሶማሌ፣ ትግራይና አዲሶቹ ክልሎች የተሳታፊዎች ልየታ ለማድረግ ታቅዷል፤ ሶማሌ ክልል በአሁኑ ጊዜ ሥልጠናዎች ተጀምረዋል፤ በቅርቡ በክልሉ በወረዳ ደረጃ የተሳታፊዎች ልየታ ይደረጋል። ቀሪ ክልሎች ደግሞ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ይጠናቀቃል ብለን እናስባለን። በዚህ ሰሞን አፋር ላይ ሥራዎች እየተሠሩ ነው በሚቀጥሉት ቀናቶች ደግሞ ሶማሌ ክልል እንሄዳለን።

**አዲስ ዘመን ፡- በሥራው ላይ የክልሎችን እንዲሁም የሌሎችን አካላት ተሳትፎና ትብብር እንዴት ይገልጹታል?**

**ፕሮፌሰር መስፍን፡-** ተባባሪዎች ሲባል እንግዲህ እስከ አሁን ድረስ በየወረዳው አምስት ተባባሪ አካላትን መርጠናል፤ በዚህም መምህራን። የሀይማኖት ተቋማት ተወካዮች እድሮች የፖለቲካ ፓርቲዎችና የሲቪክ ማኅበረሰብ ተወካዮች ይካተታሉ። በእስከ አሁኑ የሥራ ሂደትም ከእነዚህ ተቋማት ጋር የስምምነት ማዕቀፍ የተፈራረምን በመሆኑ የእኛ ተባባሪ ሆነው በየወረዳው ተወካዮቻችንን የሚያስመርጡልንና ወደፊት እንዲመጡ የሚያደርጉልን ናቸው።

ሥራዎቻችንን የምንሠራው ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመጣመር ነው። ለምሳሌ ወደየወረዳው በምንወርድበት ጊዜ የዩኒቨርሲቲ አጋሮቻችን ብዙ ድጋፎችን ያደርጉልናል። በዚህም የተወሰኑ የዩኒቨርሲቲ መምህራንን በመመልመልና ስለ ምክክሩ ጽንሰ ሃሳብና ሂደት በማሰልጠን ሲሆን እነዚህ መምህራን ደግሞ የአካባቢውን ቋንቋ በመጠቀም ለአካባቢያቸው ሰዎች ሥልጠናውን ይሰጡልናል።

ይህ ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት ደግሞ የኮሚሽኑ



**እኛ ሥራችንን እየሠራን ያለነው በሙሉ ነፃነት ነው። እስካሁን የመንግሥት ይሁን የውጭ ጣልቃ ገብነት እንዲኖር አልፈቀድንም፤ መቼም ቢሆን አንፈቅድም**

ሥራ ወደአንድ ጎን ያጋደለ እንዳይሆን ለማድረግ ሲሆን በፓርቲዎች ደረጃ እንኳን ተቃዋሚዎችንም በሙሉ ፍቃደኝነት ያሳተፈ በመሆኑ ሥራዎች በትክክል እንዲሠሩና ተመራጮችም በፍጹም ነፃነት ወደፊት መጥተው ቀጣዩን ሥራ ለመሥራት መደላድሎችን ይፈጥራል። ይህ በራሱ አላስፈላጊ የሆኑ ሐሜቶችን የሚቀንስ ከመሆኑም በላይ የኮሚሽኑንም ገለልተኝነት የሚያረጋግጥ ነው።

**አዲስ ዘመን ፡- በአሁኑ ወቅት ወደሶማሌና ኦሮሚያ ክልሎች እየተንቀሳቀሳችሁ እንደሆነ ገልጸዋል፤ ችግሮች ሲስተዋሉባቸው የቆዩት ትግራይና አማራ ክልል ላይስ ምን ታስቧል፤ ሂደቱ ምን መልክ አለው?**

**ፕሮፌሰር መሰፍን፡-** አዎ ወደሁለቱ ክልሎች ሄደናል፤ አሁን ላይ በሶማሌ ክልል ሥልጠናዎችን ሰጥተን ወደማጠናቀቁ ደረጃ ላይ ደርሰናል፤ ኦሮሚያም እንደዚሁ ነው። ትግራይ እስከ አሁን ድረስ በነበረው የፀጥታ መደፍረስ ምክንያት ሳንሄድ ቆይተናል። ነገር ግን ከቀናት በፊት እኔም ባለሁበት ወደክልሉ ተጉዘን ነበር። በዛም የጊዜያዊ መንግሥቱን ርዕሰ መስተዳድር እንዲሁም ረዳቶቻቸውን አግኝተን ብዙ ነገሮችን ተነጋግረናል፤ በቀጣይም ካቢኔያቸውንና በየደረጃው ያሉ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ከፍተኛ አመራሮች እንዲሁም በየክልሉ እንዳደረግነው የማኅበረሰቡን አመራሮች በማነጋገር በዞኖቹና በወረዳዎቹ የሚደረጉትን የሥራ ሂደቶች በሚገባ ለመወያየት አቅደናል።

በነገራችን ላይ ከትግራይ ርዕሰ መስተዳድር ጋር ባደረግነው ውይይት ከፍ ያለ ይሁንታን አግኝተናል፤ የበለጠ ይሁንታን ማግኘት የምንችለው ግን ከካቢኔያቸውና ከሌሎች አመራሮች ጋር በሚኖረን ውይይት መሆኑን እሳቸውም ገልጸውልናል።

እንግዲህ ሀገራችን ላይ ብዙ ችግሮች አሉ በተለይም ጋምቤላ አካባቢ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት ምክትል ኮሚሽነሩ ቡድናቸውን ይዘው ተንቀሳቅሰው አብዛኛውን ችግር ፈተው ተመልሰዋል። በቀጣይም ይህንን ሁኔታ በተጀመረው መልኩ የማጠናቀቅ ሥራም ይሠራል። እዚህ ላይ ግን ኮሚሽኑ ሰላም በደፈረሰባቸው አካባቢዎች ላይ ሰላምን ለማምጣት ያላሰለሰ ሥራን እየሠራ ቢሆንም መንግሥት በግጭት ውስጥ ያሉት ወገኖች በተቻለ መጠን ወደግጭት ያስገቧቸው አጀንዳዎች በመያዝ ወደ ድርድርና ምክክር መጥተው ነገሮች በሰላም እንዲቋጩ የበኩላቸውን መወጣት አለባቸው። ይህንንም ያደርጋሉ የሚል ተስፋ ነው ያለን።

**አዲስ ዘመን ፡- እንደ ኮሚሽን አብረዋችሁ የሚሠሩ ብዙ ባለድርሻ አካላት እንዳሉ ሲገልጹ ከዚህ በኋላ ከማን ምን ይጠበቃል ይላሉ?**

**ፕሮፌሰር መስፍን፡-** ኮሚሽኑ ያለፉትን 17 ወራት ሥራዎቹን ሲያከናውን የቆየው በሙሉ ነፃነት ነው። የመንግሥት ጣልቃ ገብነት አልነበረም፤ እኛም የውጭም ሆነ የውስጥ ጣልቃገብነት እንዲኖር አንፈቅድም፤ በመሆኑም በተለይም የሀገር ውስጥ መገናኛ ብዙኃን ይህ የምክክር መድረክ በትክክል እንዲሄድና የታለመለትን ግብ እንዲመታ ከፍ ያለ እገዛቸውን ማድረግ አለባቸው።

በመሆኑም ሚዲያ የእኛን መልዕክት ለሕዝቡ ከማድረስ ጎን ለጎን የአስተማሪነት ሚናውንም መወጣት ይጠበቅበታል። በመሆኑም ለየክልሉ ሕዝብ በራሱ በሚገባውና በሚያግባባው ቋንቋ የምክክርን ፅንሰ ሀሳብና ዓውድ ማስረዳት ትልቁ ሥራ ሊሆን ይገባል። የተለመደ ትብብርን ከማድረግ ባሻገር ሰፊ ሚናንም መወጣት የምንጠብቀው ጉዳይ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በመጨረሻም ማለት የሚፈልጉት ነገር ካለ?**

**ፕሮፌሰር መሰፍን፡-** የምክክር ኮሚሽኑ የጥቂት አካባቢዎች ሥራ ብቻ አይደለም እየሠራ ያለው። ሁሉንም የሀገራችንን ክልሎችና ሕዝቦች ማካተት መቻል ያለበት በመሆኑ በዚህ ልክ ነው እየተንቀሳቀሰ ያለው በመሆኑም ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ወደዚህ ሥራ መምጣት ይጠበቅባቸዋል።

ኮሚሽኑ ሥራ ሲጀምር አብረውን ለመሥራት ፈቃደኛ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሦስት የነበሩ ሲሆን ባከናወናቸው ተከታታይ ሥራዎች ግን በአሁኑ ወቅት የፓርቲዎቹ ቁጥር 47 ደርሷል፡፡ ሥራ ስንጀምር ከእኛ ጋር አብሮ ለመሥራት ፈቃደኛ የሆኑት ፓርቲዎች ከሦስት ባለመብለጣቸው በወቅቱ አስደንጋጭ ሁኔታ ውስጥ ገብተን ነበር፤ ኮሚሽኑ ደረጃ በደረጃ ባከናወናቸው ሥራዎችና በፈጠረው ቅርርብ በአሁኑ ጊዜ በምርጫ ቦርድ ከተመዘገቡ 53 የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ 47ቱ ከእኛ ጋር አብረው ለመሥራት የስምምነት ማዕቀፍ ተፈራርመዋል። በተከታታይ ሥራዎቻችን የተነሳ አብዛኛዎቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች አብረውን ለመሥራት ፈቃደኛ መሆናቸውን ገልጸውልናል፤ አሁንም ጥቂት ፓርቲዎች ገና አልመጡም፤ እነዚህ ፓርቲዎች ከኮሚሽኑ ጋር አብረው እንዲሠሩ ጥሪ እናቀርባለን እኛም በቀሪዎቹ ጊዜያቶች መሥራት ያለብንን ነገር እንሠራለን።

በሀገራዊ ምክክሩ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎችና ኢትዮጵያውያን መሳተፍና መካተት አለባቸው፤ የቀሩትን ትተን ምክክር ማድረግ አንችልም፡፡ ምክንያቱም ሀገራዊ ምክክሩ የሁሉም ኢትዮጵያውያንና ፖለቲካ ፓርቲዎች ነው። ሀገራዊ ምክክሩ ስኬታማ እንዲሆን እኛ የምንሠራውን ሥራ መከታተል ብቻ ሳይሆን በቀናነት ከኮሚሽኑ ጋር ተገናኝቶ አብሮ መሥራትና መደገፍ ያስፈልጋል። እኛ ሥራችንን እየሠራን ያለነው በሙሉ ነፃነት ነው። እስካሁን የመንግሥት ይሁን የውጭ ጣልቃ ገብነት እንዲኖር አልፈቀድንም፤ መቼም ቢሆን አንፈቅድም።

የኮሚሽኑ ዋና ተግባር በየአካባቢው ለግጭት የዳረጉን ጉዳዮችን እጅግ መሠረታዊ የሚባሉትን ወደ ሀገራዊ ምክክር አጀንዳነት ማምጣት ነው። ኮሚሽኑ ግጭት ባለባቸው አካባቢዎች ሰላም እንዲሰፍን የበኩሉን እየሠራ ቢሆንም መንግሥትም ሆነ በግጭት ውስጥ ያሉ ወገኖች በተቻለ መጠን ወደ ድርድርና መነጋገር መጥተው ወደ ግጭት ያስገቧቸው አጀንዳዎች ላይ ውይይትና ምክክር በማድረግ ችግሮቻቸውን ሊፈቱ ይገባል ፡፡

**አዲስ ዘመን ፡- ስለነበረን ቆይታ በጣም አመሰግናለሁ።**

**ፕሮፌሰር መስፍን ፡-** እኔም አመሰግናለሁ

Herald Guest

# Red sea a source of cooperation than confrontation

- Assistance Professor Ahmed Zekaria

**BY GIRMACHEW GASHAW**

*Today, Ethiopia is one of many countries that have no ports. So many years have elapsed since the country has lived without a port. When Eritrea was declared independent, it took both the Assab and Massawa ports.*

*The East African country has several options for peaceful access to the sea. All of them could have a positive economic impact not only in Ethiopia but across the region. The options include further engagement with Eritrea, Djibouti, and Somaliland on equitable terms for the use of their ports.*

*The Lamu Port-South Sudan-Ethiopia Transport (LAPSSET) corridor with Kenya, which is still in its early phases, could also be a game-changer in the region if built to completion. Ethiopia is one of the fastest-growing economies on the continent. It also has a large population, estimated at around 126 million and projected to grow at about 2.7% a year. This indicates a big market, and many needs need to be met.*


*Economic development became central to fiscal and economic planning and projections in the period between 2000 and 2012. But lack of direct coastal access became a notable obstacle to Ethiopia's efforts to achieve middle-income status via export-oriented industrialization. At one time, Eritrea's Assab port handled 70% of Ethiopia's trade.*

*At present, Ethiopia's imports and exports mainly pass via the port of Djibouti. Reliance on Djibouti has proved costly and unsustainable, however, leading Addis to search for alternatives. Coastal access would give Ethiopia more political clout to help it achieve its ambition of dominating the Horn of Africa.*

*Peaceful access to the coast would depend on its relationships with its neighbors. Some have been strained, others harmonious.*

*Since 1991, Ethiopia has been on a path of regional dominance, aided by its economic dominance in the region and in Africa. This was interrupted by its war with Eritrea between 1998 and 2000, which remained unresolved until 2018. The conflict limited but did not end Ethiopia's political ambitions in the region, as seen in the country's foreign policy since the early 1990s. Addis has appeared willing to get its own way in the region by whatever means.*

*Ethiopia continues to host the African Union and has been an active and dominant member of the Intergovernmental Authority on Development, a regional organization. Since 2018, the country's foreign policy has taken a conciliatory tone. We see this in the rapprochement with Eritrea following a peace deal that restored relations between the two states after two decades of conflict. This suggests a shift from a rigid security-focused foreign policy to a more pragmatic approach to issues that include diplomacy, climate change, migration, terrorism, and access to the sea.*



**As our economic activities were limited, we did not comprehend the advantages of ports and ships and the benefits they bring to a nation's economy**

*Because of its history and geopolitical position, Ethiopia has the potential to be a force for either stability or instability in the region. Finding a peaceful way to improve coastal access would make it a force for stability. Today's guest of the Ethiopian Herald is Ahmed Zekaria, Assistance Professor at the Institute of Ethiopian Studies, Addis Ababa University. He recently had a short stay with Ethiopian press agency reporters and raised important issues on how Ethiopia can access the sea port. Enjoy the reading!*

**First of all, how would you describe the East African region where Ethiopia is located?**

The East African region has numerous histories, and it is an area where various miracles were undertaken. As it is the cradle of humanity, Ethiopia is a country that has several histories. The East Africa region is tied up in a multitude of problems. In this region, there are two types of restless envy. This is more concerning in Ethiopia. These rivals are classified into two categories: historical and natural. Historical rivalry has a wide and long history. Natural rivals are envious of the wealth of the country.

**How would you describe Ethiopia's role in the region, especially in the Red Sea area?**

Water movements are a sign of civilization. This is expressed in big rivers and seashores. All civilizations seen so far revolve around this. For instance, humankind is moving here and there using various modes of transportation, such as on foot, on mule, on horseback, and on camel, as well as vehicles, trains, and airplanes. However, there is no mode of transportation greater than ships do in terms of bringing benefit to the country.

As our economic activities were limited, we did not comprehend the advantages of ports and ships and the benefits they bring to a nation's economy. As time goes on, our population is increasing alarmingly, followed by an increase in demand for consumer goods. Above all, the economic progress that we have recorded so far has forced us to look into alternative ships.

The desire to seek additional ships also forced us to see alternative ports. At times, when Ethiopia was the owner of the Red Sea, it exported what it produced to Middle East countries. Ethiopia, the owner of the Red Sea and Massawa ports for centuries, is now becoming poor and backward.

In those years, Ethiopia was a pioneer among many countries that gained political, social, and economic diplomatic progress in the Red Sea region. With this, Ethiopia has been recoiled by various foreign diplomats as it has built a capacity that can change the world scenario. The secret behind this is its ownership of the port.

The history of the Red Sea is wide, and it is correlated with Christianity, Islam, and Judaism. As it was a place that centralized the Nile Gorge civilization, we will talk about its history. Because Ethiopia was able to control the Red Sea port, it was a cause for the development of the Axum civilization. Sea trade was the primary reason to be counted as a top civilization, among others.

**How could Ethiopia lose its dominant power over the Red Sea port?**

Ethiopia has lost its red sea dominance due to colonization. The Horn of Africa is a strategic place that magnetizes the attention of many countries. As the area

*Continued to Page 9*

## ተናጋሪው ዶሴ

# ዘራፊው ተሳፋሪ

**አስመረት ብስራት**



በግምት ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አካባቢ ነው። የጨረቃ ብርሃን አይታይም፤ ድቅድቅ ጨለማ ነበር። ጨለማውን ለማሸነፍ ትንቅንቅ ከገጠሙት የመንገድ መብራቶች ስር አንዲት ቪትዝ መኪና ቆማ ትታያለች።

የቪትዟ መኪና ሾፌር በመጋቢት 26 ቀን 2014 ዓ.ም በግምት ከምሽቱ 2 ሰዓት ከ15 አካባቢ ጀሞ መንገድ ዳር ቆሞ ተሳፋሪዎችን በመጠባበቅ ነበር። በወቅቱ አንድ ተሳፋሪ ወደ አየር ጤና መሄድ እንደሚፈልግ ተናግሮ የመኪናዋን የኋላ በር ከፍቶ ገባ።

የእለት ሥራውን ለማጠናቀቅ አንድ ተሳፋሪ ብቻ የሚጠብቀው ወጣት ወደ መኖሪያ ሰፈሩ አቅጣጫ ተሳፋሪው መሄዱ አስደስቶት መኪናውን አስነሰቶ ጉዞ ጀመረ። ከጀሞ የተነሳው መኪና በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 ክልል ልዩ ስሙ ቆሼ ታፍ ነዳጅ ማደያ ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ ሲደርስ፤ ተሳፋሪው መውረድ እንደሚፈልግ ተናግሮ መኪናውን አስቆመው።

መኪናው ይቁምልኝ ብሎ የጠየቀበት ቦታ የመንገድ መብራት ባለመኖሩ የተነሳ ጨለማው ከበድ ያለ ነበር። የመኪናው መብራትም ጨለማውን አቋርጦ ረዥም ርቀት መብራት ተስኖታል። ሹፌሩ ልክ መኪናውን እንዳቆመ ተሳፋሪው የተገለገለበትን ገንዘብ እንዲሰጠው ዞር ሲል ባላሰበው ሁኔታ ከኋላ ሽጉጥ ተደቅኖበት ይመለከታል።

ለቀን ገቢው ማሟያ ያሰበው ሥራ የቀን ሕይወቱን ሊያጨልም መሆኑን ሲመለከት በድንጋጤ የሚያደርገው የጠፋው ወጣት የዘራፊውን ትእዛዝ መቀበል ጀመረ።

**ባለ ራይዱ**

ወጣት ያሬድ መንግሥቱ በጠዋቱ የወጣትነት ዘመን እንደ ረፋድ ፀሐይ ሳያቃጥል ሳይቀዘቅዝ ሞቅ ባለ ልስላሴ የሚጓዝ ዓይነት ወጣት ነው። በሕይወት ዘመኑ ልክነትን የሕይወት መርሁ አድርጎ ይንቀሳቀሳል። የሰው ሀቅ የማይፈልግ የራሱንም ያለአግባብ የማያስነካ ነው። የላቡን ፍሬ ይበላ ዘንድ ማልዶ ተነስቶ እስከ ምሽት ደፋ ቀና የሚል፤ ደከመኝ ሰለቸኝን የማያውቅ ወጣት ነው።

በትጋቱ የገዛትን መኪና ማልዶ የትራንስፖርት አገልግሎት ሲሰጥበት ቆይቶ በሥራ መግቢያ ሰዓቱ ወደ ሥራው ይገባል። ከሥራም ሲወጣ እስከ ምሽት ገንዘብ ሰብስቦ ወደቤቱ ይገባ ነበር። ኑሮን በሥራ መለወጥ የሚያቅደው ወጣት ወደ ትዳር ሕይወት ከመግባቱ በፊት ጥሪት መያዝን አላማው አድርጎ ደፋ ቀና ይል ነበር።

ለእናቱ ብቸኛ ልጅ የሆነው ወጣት፤ እንደተለመደው በእለቱም ማልዶ እናቱን ተሰናብቶ ከቤት ወጣ። የጠዋት ሥራውን ጨርሶ በመደበኛ ሥራው ላይ ከዋለ በኋላ ልክ ከመሥሪያ ቤቱ ሲወጣ ያገኘው የስልክ ጥሪ ወደ ጀሞ የሚያደርስ ነበርና ይዞት የሄደውን ተሳፋሪ አድርሶ ባዶውን እንዳይመለስ በጀሞ የጋራ መኖሪያ መንደር አካባቢ ቆመ።

በጠዋት ስለወጣ ድካም ተሰምቶት ነበር። ስለዚህ ያገኘውን ሰው ጭኖ ለመመለስ በሚል ከራይድ ሳይደወልለት የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰጥ የጠየቀውን ሰው ጭኖ አድርሰኝ የተባለበት ቦታ ለመድረስ ጉዞ ጀመረ።

የጉዞውን የመንገድ ግማሽ እንዳጋመሰ ‹‹ወራጅ አለ›› የሚል ድምፅ ሰማ። እሱም አየር ጤና አድርሰኝ ያለው ሰው ድንገት አቁመልኝ ማለቱ አስገርሞት የመንገዱን ዳር ይዞ ቆመ። ለመንገዱ የሚጠይቀውን ክፍያ ለመቀበል ዞር ሲል፤ ይሆናል ብሎ ያልገመተው ነገር አጋጠመው።

**ቅድሚያን መተዳደሪያው ያደረገው ሌባ**

እንደ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ልጅ ያደገው ሮጦና ቦርቆ ነው። እድሜው ለትምህርት ሲደርስ ተገቢውን ትምህርት ተምሮ የመጀመሪያ ዲግሪውን ይዟል። በምንም ምክንያት ተቀጥሮ መሥራት የሚሉትን ሃሳብ ወደ አእምሮው ጓዳ አስገብቶ አያውቅም ነበር። ሁልጊዜ በአቋራጭ መክበርን ህልሙ አድርጎ ይንቀሳቀሳል። ወጣት ማርቆስ ጡምደደ ጊባንቾ ይባላል። እድሜው 24 ነው።

በዚህ እድሜው ሳይሰራ የመክበር ፍላጎት የተጠናወተው ወጣት፤ ይህን ፍላጎቱን ለመሳካት ዝርፊያን ተቀዳሚ ተግባሩ አድርጎ ወደ ሥራው ገባ። ዝርፊያን ሥራዬ ብሎ የያዘው ወጣት አንድ ሁለት እያለ ፍርሃቱ ጠፍቶ ቋሚ ሌባ እስኪሆን ድረስ ንጥቂያን ተለማመደ።

ይህንን ልምዱን ደግሞ አቅዶና ተዘጋጅቶ ሰዓት እየጠበቀ በንጥቂያ ያለመው የሀብት ማማ ላይ ለመቆናጠጥ ይታተር ጀመር። ከተራ ሌብነት ወጥቶ መኪና ለመቀማት ያቀደው ቀማኛ አድብቶ ሲጠብቅ ከነበረበት አካባቢ ለህልሙ መሳካት የምትሆን የትራንስፖርት አገልግሎት የምትሰጥ መኪና ቆሞ ተመለከተ።

ምንም ሳያመነታ ወደ መኪናው ገብቶ ጉዞ ጀመረ። ቀደሞም ለዘረፋ ተዘጋጅቶ የገባው ይህ ሰው ለእኩይ ተግባሩ ምቹ ቦታ ሲያገኝ መውረድ እንደሚፈልግ ተናግሮ መኪናውን ካሰቆመ በኋላ አላማው ዝርፊያ ብቻ በመሆኑ "እገልህ ነበር ግን አሳዘንከኝ በማለት" መኪናውንና ሌሎች የተበዳዩን ንብረቶች በሽጉጥ አስፈራርቶ ዘርፎ ተሰወረ።

**ጥቆማ የደረሰው ፖሊስ**

የግል ተበዳይ አቶ ያሬድ መንግሥቱ የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3 - በ.38528 አ.አ የሆነ የሻንሲ ቁጥሩ ኤስ ሲ ፒ 10 0325833 የሞተር ቁጥሩ 1 ኤስ ዜደ -0812672 የሆነ እና የዋጋ ግምቱ ብር 830ሺህ ብር የሆነ ቪትዝ መኪና ይዞ የራይድ አገልግሎት ለመስጠት በቆመበት መዘረፉን ለፖሊስ ካመለከተ በኋላ ፖሊስ ጉዳዩን ይዞ መከታተል ጀመረ።

ዝርፊያው ሲካሄድ በዳይ መኪናውን እንዲያቆም ካደረገ በኋላ ሽጉጥ በመደቀን ‹‹እገልህ ነበር፤ አሳዝነከኝ ነው፤ አሁን ከመኪናህ ውረድ›› በማለት አስፈራርቶ ከመኪናው እንዲወርድ አድርጎ ተሽከርካሪው ውስጥ ያገኘውን የግል ተበዳይን መንጃ ፍቃድና የቀበሌ መታወቂያ እንዲሁም የአዋሽ ባንክ ኤ ቲ ኤም ካርድ ከነሚስጥር ቁጥሩ እንደያዘ የተሰወረውን ቀመኛ ለማገኘት ፖሊስ ብዙ ጥረት ካደረገ በኋላ አንድ ቀን በለስ ቀናው።

ፖሊስ ስለመኪናዋ ያለውን መረጃ በሙሉ ለሁሉም የፖሊስ ክፍል አባላት በማድረሱ በመጋቢት 29 ቀን 2014 ዓ.ም በግምት ከምሽቱ 12 ሰዓት ከ30 ላይ መኪናውን ሰሌዳ ቁጥር 2-11562 ኦሮ የሚል ለጥፎበት ያየ አንድ ባልደረባ በቁጥጥር ስር ሊያውለው ችሏል።

ፖሊስ ሊይዘው በሚሞክርበት ጊዜም ሊያመልጥ ያደረገው ሙከራ በአካባቢው ሰዎች በተደረገ ርብርብ ሲደረስበት መኪናውን ጥሎ ያመለጠ ቢሆንም በኋላ ግን በብዙ ትግል ተይዞ፤ በፈፀመው ከባድ የውንብድና ወንጀል ተከሷል።

**የፌደራል አቃቤ ሕግ ክስ**

ከሳሽ የፌደራል አቃቤ ሕግ ተከሳሽ ማርቆስ ጡምደደ ጊባንቾ እድሜው 24 ሲሆን፤ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 671(1)(ለ) ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ክስ ቀርቦበታል።

የወንጀሉ ዝርዝርም ተከሳሽ የማይገባውን ብልጽግና ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ በመጋቢት 26 ቀን 2014 ዓ.ም በግምት ከምሽቱ 2 ሰዓት ከ15 ሲሆን በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 ክልል ልዩ ስሙ ቆሼ ታፍ ነዳጅ ማደያ ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ የግል ተበዳይ አቶ ያሬድ መንግሥቱ የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-በ.38528 አ.አ የሆነ የሻንሲ ቁጥሩ ኤስ ሲ ፒ 10 0325833 የሞተር ቁጥሩ 1 ኤስ ዜደ -0812672 የሆነ እና የዋጋ ግምቱ ብር 830ሺህ ብር የሆነ ቪትዝ መኪና ይዞ የራይድ አገልግሎት ለመስጠት እየተጠባበቀ እያለ ተከሳሽ ጀሞ አካባቢ መንገድ ላይ ቆሞ በመጠበቅ የግል ተበዳይን በማስቆም አየር ጤና እንዲወስደው ጠይቆ በተሽከርካሪው ከኋላ በኩል ከገባ በኋላ፤ ከላይ የተገለፀው አካባቢ ሲደርሱ ደርሻለሁ አቁምልኝ በማለት የግል ተበዳይ መኪናውን እንዲያቆም አድርጓል፡፡

ከኋላ በኩል ሽጉጥ በመደቀን እገልህ ነበር አሳዝነህኝ ነው አሁን ከመኪናህ ውረድ በማለት አስፈራርቶ ከመኪናው እንዲወርድ አድርጎ ተሽከርካሪው ውስጥ የግል ተበዳይን መንጃ ፍቃድ የቀበሌ መታወቂያ የአዋሽ ባንክ ኤቲ ኤም ካርድ ከነሚስጥር ቁጥሩ እንደያዘ ከተሰወረ በኋላ በ29/07/2014 ዓ.ም በግምት ከምሽቱ 12ሰዓት ከ30 ላይ መኪናውን ሰሌዳ ቁጥር 2-11562 ኦሮ የሚል ለጥፎበት ሲገኝ ሊያመልጥ ሲል በአካባቢው ሰዎች በተደረገ ርብርብ ሲደረግበት መኪናውን ጠሎ ያመለጠ መሆኑን በፈፀመው ከባድ የውንብድና ወንጀል ተከሷል።

ሁለተኛ ክስ ወንጀሉ የብሔራዊ የክፍያ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 718/2003 አንቀፅ 35/4/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ሲሆን፤ የወንጀሉ ዝርዝር ተከሳሽ የክፍያ ሰነዱን የተሰረቀ መሆኑን እያወቀ በ1ኛ ክስ በተገለፀው ጊዜ እና ቦታ በወሰደው ተሽከርካሪ ውስጥ ያገኘውን የግል ተበዳይ አቶ ያሬድ መንግሥቱ የአዋሽ ባንክ የኤቲ ኤም ካርድ ከነሚስጥር ቁጥሩ በተለያዩ ጊዜያት በመጠቀም ከግል ተበዳይ ሂሳበ ቁጥር ላይ ሃምሳ ሺ ብር የወሰደ መሆኑን የተሰረቀ የክፍያ ሰነድ በመጠቀም ክስ ወንጀል ተከሷል።

ሶስተኛ ክስ ተሽከርካሪ መለያና መመርመሪያ መመዝገቢያ አዋጅ ቁጥር 618/2002 አንቀፅ 48/2/ለ/ ስር የተመዘገበውን በመተላለፍ ሲሆን፤ የወንጀሉ ዝርዝርም ተከሳሽ በአንደኛ ክሰ በተገለፀው አግባብ የወሰደውን ንብረትነቱ የግል ተበዳይ አቶ ያሬድ መንግሥቱ የሆነ የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3- በ.38528አ.አ የሻንሲ ቁጥሩን ኤስሲፒ 10-0325833 የሞተር ቁጥሩ 1 ኤስ ዜደ -0812672 የሆነውን ተሽከርካሪ የራሱ ያልሆነውን እና ከአቶ ኤሊያስ አዳነ ከተባለ ሰው በተሰጠ ውክልና መሠረት የሚያስተዳድረው በመምሰል እና የሰሌዳ ቁጥር 2-11562 ኦሮ በመለጠፍ ተሽከርካሪውን የተጠቀመበት በመሆኑ በፈፀመው አንድን ተሽከርካሪ የራሱ ያልሆነውን የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ለጥፎ በመገኘት ወንጀል ተከሷል።

**ውሳኔ**

ተከሳሽ ማርቆስ ጡምደደ ጊባንቾ በተከሰሱበት የውንብድና ወንጀል በፌደራል ከፍተኛ ደረጃ ፍርድ ቤት የልደታ አንደኛ ምድብ በሚያዝያ 7 ቀን 2015 ዓመተ ምህረት በዋለው ችሎት ክስና ማስረጃውን ከሕግ ጋር አገናዝቦ በ11 ዓመት ፅኑ እስራት እና በአስር ሺ ብር ቅጣት እንዲቀጣ ወስኗል።



(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# ስደትና ፍልሰት "የታሪካችን ሾተላይ"

**"እግር ከቤት ልብ ከደጅ"**

"በዜጎች ጎርፍ የሚጥለቀለቀው ኢሚግሬሽን" በሚል መሪ ርዕስ በዚህ ዓምድ የጥቅምት 17 ቀን 2016 ዓ.ም ዕትም በተስተናገደው ጽሑፍ ስለተጠቀሰው መንግሥታዊ ተቋም መረርና ኮስተር ያለ ትዝብት ማስነበባችን ይታወሳል፡፡ ባለጉዳዩ መንግሥታዊ መሥሪያ ቤት ለቀረበበት ስሞታ "ንስሐ ገብቶ" የዐይኑን ጉድፍ ይጥረግ አይጥረግ ወደፊት የምናየው ስለሆነ ለጊዜ ጊዜ ሰጥተን ወደ ዛሬው ተያያዥ ጉዳያችን ማዝገሙን መርጠናል፡፡

ቀደም ሲል በተጠቀሰው ጽሑፉ ውስጥ "የቀደምት ዜጎቻችን የስደት ታሪክ እንዴት፣ ወዴትና ምን ይመስል እንደነበር በሚቀጥለው ሳምንት የአንድ የደቡብ አሜሪካ ሀገርን ታሪክ በመንደርደሪያነት ተጠቅመን የዳሰሳ ያህል ለማሳየት ስለምንሞክር ለጊዜው ርዕሰ ጉዳዩን በይደር አቆይተናል" የሚል የቤት ሥራ ተቀብለን ማለፋችን ይታወሳል፡፡ በቃላችን መሠረትም የዛሬው ጽሑፋችን ዋና ትኩረት ልንፈወስበትና ልንፈውሰው ባልቻልነውና በሾተላይ በመሰልነው የዜጎቻችን የስደት ጉዳይ ላይ ጥቂት ቁዘማ እናደርጋለን፡፡

"ሾተላይ" የሚለውን ቃል በሙያው ባለሙያዎች የተዘጋጁ ሰነዶች ሳይሆኑ የዘወትር መጠቀሚያችን የሆኑት መዛግብተ ቃላት የሚበይኑት እንዲህ በቀላሉ እንዲገባን አድርገው ነው፡- "ሾተላይ የወንድና የሴት የደም ዓይነት ቅንጅት ተስማሚ ባለመሆኑ ሽሉ እንደ ተፀነሰ ወይም እንደተወለደ እንዲሞት ያደርጋል ተብሎ የሚታመንበት ከወሊድ ጋር የተያያዘ መሠረታዊ ችግር ነው፡፡"

የሀገራችንና የታሪካችን መስተጋብር ከሾተላይ ጋር ተነጻጽሮ መቅረቡ በየሥርዓተ መንግሥታቱ ያለፍንበትና ዛሬም እያለፍንበት ያለው ኑሯችን በአብዛኛው ትውልዱን ለስደትና ለፍልሰት እየዳረገ ሲያመክን የኖረ ክፉና ፈውስ ያልተገኘለት በሽታ መሆኑን ለማመልከት ነው፡፡ የሀገር ማህፀን ያፈራቸው በርካታ ዜጎች በባሕር፣ በየብስና በአየር እየወጡ የፈለሱባቸው ታሪኮች ዓይታቸውም ሆነ ዝርዝራቸውም የትየለሌ የሚሰኝ ነው፡፡

**"አይሄ! ያስለቅሳል፣ ያስተክዛል፣**
**ያሳለፍነው መች ደረሳል፣**
**የእኛ ነገር መች ደረሳል፡፡"**
**በሰቲት ሑመራ በገዳሪፍ ካርቱም፣**
**ጅቡቲ ኬኒያ በእግሬ ሳዘግም በረሃ ሳቋርጥ፣**
**እግሬ አውጭኝ እያልኩኝ ድንበር ኬላ ስሰብር"**

በማለት ድምፃዊ ነዋይ ደበበ በአራራይ እንጉርጉሮ በተቃኘ ዜማው ያስደመጠን ሀገሪቱን የወላድ መካን አድርጎ "ሾተላይ" የሆነባት የትናንትና ብቻ ሳይሆን ዛሬም ያልተፈወሰችበት ተግዳሮቷ ግድ ብሎት ይመስላል፡፡ ሌላዋ ድምፃዊትም እንዲሁ "ስደት ይጠራኛል አቤት አልለውም፤ ቃሉ ያስፈራኛል" በማለት ያዜመችው ይህንኑ እንደ መዥገር ተጣብቆ አልፈወስ ያለውን የሀገር ማህፀን አምካኝ "በላ" ለማስታወስ ሳይሆን አይቀርም፡፡

**የታሪክ ማስታወሻ፤**

በሕዝቦች የስደት ዜና መዋዕል ተደጋግመው ከሚጠቀሱት መካከል በኩባ የተደረገው የዜጎች ፍልሰት ብዙ የሚነገርለት ታሪክ አለው፡፡ እ.ኤ.አ በ1959 በፊደል ካስትሮ የሚመራው የተዋጊ ቡድን በለስ ቀንቶት የአምባገነኑን የባቲስታ መንግሥት አንበርክኮ ካስወገደ በኋላ 1.4 ሚሊዮን ዜጎች ሀገራቸውን ትተው ወደ አሜሪካ የተሰደዱት በማግሥቱ ነበር፡፡ በማስከተልም 300,000 የሚሆኑ ተጨማሪ ዜጎች ውለው ሳያድሩ ወደ ተጎራባች ሀገራት እና ወደ አውሮፓ በመትመም ዓለም አጋጥሟት በማያውቅ ፍልሰት እንድትጥለቀለቅ ምክንያት ሆነዋል፡፡

እነዚህ ስደተኞች ዝርያቸው የሚመዘዘው በአብዛኛው ከ1492-1898 በምድሪቱ ላይ በባርነት ተግዘው ከተወሰዱ የመከረኛዋ አፍሪካ ልጆች ነበር። ከፊደል ካስትሮ መራሹ የኩባ አብዮት ማግሥት በጀልባ ባሕር እያቋረጡ ወደ አሜሪካ የገቡትን ዜጎች በተመለከተ ሀገሪቱ የዜጎቿን የፍልሰት ታሪክ ለልጆቿ የምታስተምረው በአምስት አንጓ በመከፋፈል ነው፡፡

የመጀመሪያውን የፍልሰት ማዕበል (ከ1959-1962) የሰየመችው "ታሪካዊ ፍልሰት" (Historical exile) በማለት ነው፡፡ በዚህ የመጀመሪያው የስደት ጎርፍ ሀገራቸውን ጥለው ለመሰደድ የበቁት በመቶ ሺህዎች የሚቆጠሩት ዜጎቿ ብዙዎቹ በከፍተኛና በመካከለኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙና በዝባዥ የሚል ቅጽል የተሰጣቸውና ለነፍሳቸው ሰግተው የኮበለሉ ነበሩ፡፡

ከ1965-1973 የተከናወነው ሁለተኛው የፍልሰታቸው ስያሜ "የነፃነት ፍሊጋ ሽሽት" (Freedom flights) በመባል የሚታወቅ ሲሆን ቅንብሩ ደግሞ በአሜሪካ እውቅና የተቸረውና ፍልሰተኞቹን ዜጎች የምትቀበለው ሀገር ራሷ የአውሮፕላን ቲኬት እየገዛችላቸው "ኑልኝ!" በማለት በይፋ በመጋበዝ ነበር፡፡ የታሪክ ልሒቃን ይህንን መሰሉን የኩባ ስደት የሚገልጹት "የክብር ባርነት፣ የፖለቲካ አስቀያሚ መገለጫ መልክ ወዘተ.) በማለት ነው፡፡

ከኤፕሪል እስከ ሴፕቴምበር 1980 ለስድስት ወራት ያህል በተከናወነውና ከመቶ ሃያ ሺህ በላይ ኩባውያን የተሰደዱበት ሦስተኛው ምዕራፍ ደግሞ የማሪዬል ዘፀአት (Mariel exodus) በመባል ይታወቃል፡፡ በዚህ የስደት ማዕበል የተገፉት አብዛኞቹ ዜጎች ከእስር ቤት ምሕረት አግኝተው የተለቀቁና የትኛውንም የጉልበት ሥራ ለመሥራት ፈቃደኛ የሆኑ ምስኪኖች እየተመረጡ የተሰደዱበት የፍልሰት ዓይነት ነበር፡፡

የባልሴሮ ቀውስ (Balsero crises) በሚል ስያሜ የሚታወቀውና ለሁለት ወራት ብቻ በፈጣን ሁኔታ የተከናወነው አራተኛው የዜጎች ፍልሰት በአሳዳጇ ሀገር በኩባና በስደተኞች ተቀባይዋ አሜሪካ መካከል በተደረገ የጋራ ስምምነት ውል የተደረገ ፖለቲካዊ ወዘና የነበረው ክስተት ነበር፡፡

እ.ኤ.አ ከ1995-2017 ለረዥም ዓመታት የዜጎች ኩብለላ የተስተዋለበትና በአምስተኛነት የሚጠቀሰው (Post-Soviet migration) የኩባውያን ስደት ግን የተለየ ስያሜና ታሪክ ያለው ነው፡፡ በተጠቀሱት ዓመታት 650,000 ያህል ስደተኞች "ሁሉ በሁሉ ነኝ" ባዩዋ አሜሪካ የገቡት ስደተኞች ይለዩ የነበረው "ኮቴ ደረቅ" (dry-foot) ወይንም ኮቴ ርጥብ (wet-foot) በሚሉ ስያሜዎች ነበር፡፡ "ኮቴ ርጥብ" የሚባሉት በጀልባና በባሕር ወደ አሜሪካ ለመግባት ሞክረው የተሳካላቸው ወይንም ሙከራው ከሽፎባቸው ተጠርዘው ወደ ሀገራቸው የተመለሱትን ሲመለከት፤ "ኮቴ ደረቆቹ" ደግሞ በሕጋዊ መጓጓዣ በየብስ ወይንም በአየር የገቡትን ለማመላከት ነው፡፡ ዝርዝር ታሪኩ ሰፋ ስለሚል ለማሳያነት ይሄው ይበቃ ይመስለናል፡፡

**የእኛ ዜጎች የስደትና የፍልሰት ታሪክ ምን ስያሜ ሲሰጠው ይችላል?**

መቼም ተወዳጁን እንጂ ጥዩፉን ታሪካችንን በይፋ ለመግለጽ ለማንደፋፈረው ለእኛ ቢወራና ቢተረክ ከልብ የምንወደውና ሌሎችም እንዲወዱልን "ታሪካችን" ብለን ሳንሰለች የምንተርከው "ኢትዮጵያችን የስደተኞች ተቀባይ ሀገር እንደሆነች" እንጂ "የከፋ የዜጎች ፍልሰት ባለታሪክ" እንደሆነች አፍ ሞልተን ለመናገር አፋችንን ይይዘናል፡፡

በሃይማኖት፣ በኢኮኖሚም ሆነ በፖለቲካ ምክንያት የተሰደዱ የብዙ ሀገራት ዜጎችን መቀበላችንን የምንሰብከውን ያህል እኛ እርስ በእርስ መሳደዳችን በፍጹም እንዲነሳብን አንፈልግም፡፡ ከቅርቡ ዘመናት እንጀምር እንኳን ብንል ሀገሬን "ሾተላይ" ሆኖ ማህፀኗን ለእርግማን የዳረገው የዜጎቿ የስደትና የፍልሰት ታሪክ በእጅጉ አንገት አስደፍቶ የሚያስለቅስ እንጂ ለመስማት የሚያጓጓ አይደለም፡፡

በተለዋጭ ትርጉም ግልጋሎት ላይ የሚውሉትን "ስደት" እና "ፍልሰት" የሚሉ ሁለቱ አሻሚ ቃላት በዚህ ጽሑፍ ውስጥ አገልግሎት ላይ የዋሉት "ስደት" በአንድ ጉዞ ለሚደረግ ውሱን የዜጎች ኩብለላ፣ "ፍልሰት" ደግሞ በርከት ላሉና በቡድንና በጅምላ የሚፈጸም ሽሽትን ለመወከል ነው፡፡

በነጠላም ሆነ በቡድን፣ በጥቂትም ሆነ በእልፍ ቁጥር ሲፈጸሙ የኖሩት የሀገሬ ዜጎች የፍልሰት ታሪኮች የሚነገሩት "ትናንት" በሚል የኃላፊ ጊዜ ብቻ ሳይሆን "ዛሬም" እየተባለ መሆኑ ልብ ሊባል ይገባል፡፡ ለምን ስደት የኑሯችን ዘይቤ ሊሆን ቻለ? እያንዳንዱ ዜጋ ከሀገሩ ለመሸሽ ልቡ ሊሸፍት የቻለውስ ለምንድን ነው? ኢትዮጵያ ዜጎቿን ለማኖር አቅም ስለሌላት ወይንስ "አቅመ ስንኩል ያደረጋትን" ወደረኛ መከራዋን መቋቋም ስለተሳናት? ምላሹ ድፍረት፣ መልሱም ኅምዛዛ ስለሆነ "በሆድ ይፍጀው" እህህታ ማለፉ ይመረጣል፡፡

በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ዜጎች ሀገር ጥለው ለመኮብለል እጅግም አይደፋፈሩም ነበር፡፡ በኢጣሊያ ወረራ ወቅት ተስፋፊዋ እብሪተኛ ሀገር ዜጎቻችንን እያፈሰች ከሀገር ውጭ ታፈልስ እንደነበረ አይዘነጋም፡፡ ከወረራው በኋላ መንግሥት በእግሩ ከቆመም በኋላ ሥርዓቱን ይቃወሙ የነበሩ የነውጠኞቹ የኮሌጅ ተማሪዎች ሙከራ "አውሮፕላን እስከ መጥለፍ" በደረሰ ድፍረት በየብስም ሆነ በአየር "የትግል ስልት" በሚል ስያሜ ሀገር ጥሎ መኮብለልና መሰደድ የዘመኑ ፋሽን ከመሆን የዘለለ እጅግም የሚነገርለት ዝርዝር ታሪክ የለውም፡፡

የዜጎች ፍልሰት ሊባል የሚቻለው በአብዛኛው በሀገር ውስጥ ይፈጸም የነበረ እንጂ ድንበር የሚሻገሩት ስደት እጅግም ነበር፡፡ በተለየ ሁኔታ ግን የ1966 ዓ.ም ክፉ የድርቅና የረሃብ ታሪካችን እጅግ ዘግናኝ የሀገር ውስጥ የፍልሰት ታሪክ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ንጉሡን ከመንበራቸው ያስወገደ ክስተት ጭምር መሆኑ በሚገባ ይታወቃል፡፡

የደርግ ዘመን የዜጎች ፍልሰት ግን በታሪካችን ውስጥ ጥቁር አሻራው የደመቀና መከራና ስቃዩም የከፋ እንደነበር ያልመሸበት ታሪካችን ምስክር ነው፡፡ በቀይና ነጭ ቀለማት የሚታወቀው ሽብር ብዙ ዜጎቻችንን ለከፋ ስደትና ፍልሰት መዳረጉን የምናስበው በጨፈገገ ስሜት ነው፡፡ የዚያድ ባሬዋ ሶማሊያ ኢትዮጵያን በወረረችበት ዓመታት ያጋዘቻቸው በሺህዎች የሚቆጠሩ ዜጎቻችንም የሚዘነጉ አይደሉም፡፡ በርዕዮተ ዓለማቸው ልዩነት፣ በሃይማኖታቸው ምክንያት የተሰደዱትን ሁለቱን ብቻ ተገቢ ትኩረት ሰጥተን በየፈርጁ እንዘርዝር ብንል የጋዜጣው ውሱን ዓምድ ስለሚገድበን እንዲሁ ብቻ አስታውሶ ማለፉ ይበጅ ይመስለናል፡፡

በዘመናት ውስጥ በአይሁድ እምነታቸው ምክንያት የመከራ ወስከንባይ ተደፍቶባቸው አሳር እያዩ የኖሩትና የተገፉት የእምዬ ልጆች "ቤተ እሥራኤላውያን" ሀገር ጥለው ስለምን የኢያሱን፣ የሙሴንና የሰሎሞንን ስያሜ በያዙ የፍልሰት ኦፕሬሽኖች ወደ ተስፋ ሀገራቸው እንደገቡ በዝርዝር ለመተረክ ርዕሰ ጉዳዩ ይገድበናል፡፡

የዘመነ ሕወሓት/ኢሕአዴግ ዘመን ግን በታሪካችን ውስጥ እጅግ የከፋና የከረፋ ታሪክ የተሸከመ ስለሆነ ክርፋቱን ለመዘርዘር ይፈታተናል፡፡ የሀገር ሠራዊት በትኖ በመቶ ሺህዎችን ያሳደደና ለፍልሰት የዳረገ ሌላ ሀገር ስለመኖሩ በታሪክ ላይ የተመሠረተ ጥናት ተደርጎ ውጤቱ እስኪታወቅ ድረስ እንዲሁ እንዳንገሸገሸን ብናልፈው ይቀላል፡፡ የኬኒያና የጎረቤት ሀገራት የስደተኛ ጣቢያዎች ይመስክሩ ብሎ በደምሳሳው ማለፉ ይቀላል፡፡ አሜሪካ በዕጣ ያንበሸበሸቻቸው ዜጎች ፍለሰት ግን አከራካሪ ስለሆነ የምናልፈው በጥቅሻ ይሆናል፡፡

በሀገራቸው ብቻ ሳይሆን በቀያቸው ጭምር ዜጎቿ ተረጋግተው እንዳይኖሩ "የመከራዋ ሾተላይ" የጸናባት ሀገሬ ዛሬም ልጆቿን በብብቷ አቅፋ ለማኖር ስለተቸገረች ቀለቧ እንባዋ ከሆነ ውሎ አድሯል። ብዙው ዜጋ ልቡና መንፈሱ ለስደት አኮብኩቦ መቀመጡን በድፍረት ባንናገር ከሐሊናችን ጋር እንጣላለን፡፡ ግን ስለምንና በማን ምክንያት? መልሱን እናውቀዋለን፤ ብንናገር ዝርዝሩ ስለሚሰፋ ግን እናልፈዋለን፡፡

ዳሩ በታመመ የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ እንዴት መረጋጋት ይቻላል? እንደምንስ ጦርና የጦር ወሬ የዕለት ስንቅ ሆኖ እስኪቆጠር ድረስ "የሰላም ርግብ በቆሰለችበት" ሀገር ዜጎች ተረጋግተው እንዲቀመጡ ይበረታታሉ? ከቶ እንደምን በተሳከረ የኑሮ ምሕዋር ውስጥ ሚዛንን ጠብቆ ቀን መግፋት ይቻላል? ዜጎች በቋንቋቸው፣ በባሕላቸው፣ በብሔራቸውና የራሳቸው መለያ በሆኑ በሚያከብሯቸው ማንነታቸው ተከብረውና ተከባብረው እንዲኖሩ ምድሪቱ እስካልፈቀደች ድረስ እንደምን ስደትና ፍልሰትን ምርጫ አይሆኑም?

ሀገሬ ሆይ! ዜጎችሽ በቅርብም ሆነ በርቀት ሆነው ለሚሞግቱሽ ጥያቄ ምን መልሱ እንደማይጠፋሽ እናምናለን፡፡ ግን በርግጡ ልጆችሽን ለማኖር አቅም የለሽም? "በስደትና ፍልሰት ሾተላይ" የወላድ መካን መባሉስ ተስማምቶሻል? በመደማመጥና በመነጋገር ለማያምኑ ልጆችሽ በእምባሽም ይሁን በምክርሽ ምን ትያቸዋለሽ? ስለ አንቺ እንጃልሽ! ስለ እኛ ግን ባለቅኔው "እስኪ ተጠየቁ" ያለውን ጥያቄ ተውሰን እንጠያየቃለን!

**ቸገረኝ ጨነቀኝ ብጠይቅ አጥብቄ፣**
**ምላሽ አጥቼለት ለልቤ ጥያቄ፣**
**ያንጀት ልቅሶ ሆኖ የዘመኑ ሳቄ፡፡**
**እንዲህ ተወስኖ ኑሮው ምጥ ነው እንጂ፣**
**ሳይገላገለው ታሥሮ እጅ ከፍንጅ፤**
**እንዳማጡ መኖር የኑሮ አተላ፣**
**መፍትሔ የሌለው በድፍን ነው ሾላ፡፡**

ይሄው ነው፡፡ ሰላም ለሕዝባችን ለዜጎችም በጎ ፈቃድ።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## አርታኢዎቹ የት ናቸው?

መልካምሥራ አፈወርቅ

ሰሞኑን ከአንድ የሀገራችን ታዋቂ የቴሌቪዥን ጣቢያ አንድን ጉዳይ ስታዘብ ከረምኩ፡፡ በዚህ ጣቢያ የተላለፈው ዝግጅት ጊዜው የራቀ አይደለምና በርካቶች ያስታውሱታል የሚል ግምት አለኝ፡፡ ሁሌም በጣቢያው በተለመደ ሰዓት የሚቀርበው ሳምንታዊ ዝግጅት በአብዛኛው ችግሮችን በግልጽ አሳይቶ መፍትሄ መሻት ላይ የሚያተኩር ነው፡፡

እስካሁን በተላለፉ ፕሮግራሞችም ይህንኑ በግልጽ ስናስተውል ቆይተናል፡፡ ይህ ብቻ አይደለም አዕምሯችን ጥቂት የማይባሉ ሰዎችን አሳዛኝ ታሪኮች ከትቦ አስቀርቷል። እንደተመልካች እኛም በልብ ሰባሪ ታሪኮቻቸው እኩል አንብተናል፣ ከልብ አዝነናል፡፡ መለስ ብለንም ዕንባቸው ሲታበስ አይተን በተለወጠ ሕይወታቸው ተደስተናል፡፡

በአጠቃላይ ይህ የቴሌቪዥን ዝግጅት ቁምነገር አዘል ነውና የበርካታ ተመልካቾች ምርጫ ነው ማለት ያስደፍራል፡፡ ከሰሞኑም የእነዚህን ዓይነት ታሪኮች የሚጋራ አንድ ሰው በዚሁ የቴሌቪዥን ዝግጅት ብቅ ብሎ አሳዛኝ ታሪኩን አውግቶናል፡፡

የዚህ መሰናዶ እንግዶች ችግሮቻቸው በርካታ ነው፡፡ ሁሌም በታሪኮቻቸው መሀል ሀዘንና ለቅሶ ይስተዋላል፡፡ የዝግጅቱ ዋና ዓላማም የሰዎችን ችግር አሳይቶ መተው አይደለም ፡፡ ይልቁንም ያዘኑ፣ ያለቀሱ ምስኪኖችን ዕንባ ማበስ ነው፡፡ በተቻለ አቅም ጎዶሏቸው ሞልቶ ቀና ይሉ ዘንድ መቋቋሚያ ድጋፍን እነሆ! ማለትም ለምዷል፡፡

ታሪኩን የሚመለከት ታዳሚ ታዲያ በሚያየውም በሚሰማውም እውነት ማዘንና መጨነቁ አይቀርም፡፡ እንዲያም ሆኖ ከዚህ ሀቅ በስተጀርባ የሚገኘውን መልካም ውጤት መጠበቁ የግድ ነው፡፡ መጨረሻው በጎ ሲሆን ታዲያ በርካቶች ከባለጉዳዮቹ እኩል ፊታቸው ይፈካል፡፡

አስቀድሜ ወደጠቆምኳችሁ ባለታሪክ ልለፍ፡፡ በቅርቡ በዚሁ የቴሌቪዥን ጣቢያ እንግዳ ሆኖ የቀረበ ወጣት ነው፡፡ የዚህ ሰው የሕይወት ፈተና ከገጠር ኑሮው ይጀምራል፡፡ ገና በልጅነት ዕድሜው ወላጅ እናቱን በሞት ያጣው ይህ ወጣት ከእሱ በታች ያሉትን ሁለት እህቶችና ወንድሙን ለማሳደግ ቀላል የማይባል ዋጋ ከፍሏል፡፡

ባለታሪኩ ሲናገር እንደተሰማው የወላጅ እናቱ የሞት መንስኤ የኤች አይ ቪ ኤድስ በሽታ ነው፡፡ በወቅቱ ከሕመሙ ጋር ተያይዞ የነበረው አድልኦና መገለል የከፋ በመሆኑም የእናት ሕመም ምስጢር ሆኖ ነው የዘለቀው። ምስጢሩ እንዳይዛመት ማሳመኛው ደግሞ የአባወራው ከቫይረሱ ነጻ መሆን ነበር፡፡

የመገለሉ ጉዳይ እንዲህ ቢቃለልም ዳሩ ከሁለቱ ሕጻናት የትልቋ ልጅ ከቫይረሱ አለማምለጥ ደግሞ ለቤተሰቡ ከባድ የሚባል ሀዘን ማትረፉ አልቀረም፡፡ ይህ እውነት እንደታወቀ ሕይወቷን ለመታደግ የጸበልና የሕክምና ትግሉ አልተቋረጠም፡፡ አባት ባለቤታቸውን በሞት ካጡ ወዲህ ልጆቻቸውን ለማሳደግ ብዙ ደክመዋል። ሌላ ሚስት ላለማግባት ወስነውም በብቸኝነት ዓመታትን ቆጥረዋል፡፡

የዚህ ቤተሰብ ሌላው ፈተና ደግሞ የትንሹ ልጅ ጤና ማጣት ነበር፡፡ ይህ ልጅ እናቱ ከሞቱ በኋላ በነበረ ጥርጣሬ በተደጋጋሚ የኤች አይ ቪ ምርመራ ተደርጎለታል። አንድም ውጤት ግን በደሙ ቫይረሱ እንደሚገኝ አልጠቆመም። የምርመራው ውጤት ይህን ያመላክት እንጂ ልጁ ግን ጤና ይሉት የለውም፡፡ በሰውነቱ የወጣው ቁስል የዘወትር ሕመም ሆኖ ያሰቃየዋል፡፡ ከሕክምናው በላይ ባህላዊ ልማድን የመረጡት ቤተሰቦች ለመዳኑ መፍትሔ ያደረጉት በጋለ ብረት አካሉን ማስተኮስ ነበር፡፡

እንግዳው ዛሬ ላይ ሆኖ በወቅቱ የነበረውን ወንድሙን ስቃይ በተለየ ስሜት ያስታውሰዋል፡፡ ያልበረታው የሕጻን ገላው ከአንድ አይሉት በሁለት ሰዎች እጅ በጋለ ብረት ተተኩሷል፡፡ ዕባጩን ለማፍረጥ በሚደረገው ጥረት ሁሉ ሰውነቱ በፍም ግሎ በሚወጣ ብረት ጋይቷል፡፡ ነፍስና ሥጋው እየተጨነቀ ቆዳው እንደ ጨርቅ ሲጨስም ቆይቷል፡፡

ይህ እውነት የባለታሪኩ አይረሴ የሕይወት ክፍል ነው፡፡ ምንጊዜም ያለፈውን ሲያነሳ ዓይኖቹ በእንባ ይሞላሉ፡፡ ካሳለፈው የመከራ ሕይወት ሁሉ ይሄኛው ሀቅ ሚዛን ደፍቶ ከልብ ያስለቅሰዋል፡፡ ይህ ወጣት ለሁለቱ ሕጻናት መኖር ብዙ ሆኗል፡፡

የተወለደበትን አካባቢ ትቶ ከወጣ በኋላም ስለእነሱ የሴት፣ የወንድ ሳይል ባገኘው ሥራ ታግሏል፡፡ በዚህ ገጽ ብቻ ተገልጾ በማያበቃው የሕይወት ውጣ ውረድ ተራምዶም የእህትና ወንድሙን እስትንፋስ አቆይቷል፡፡ ይህ የወጣቱ ታሪክም የቴሌቪዥን ጣቢያውን ትኩረት በመሳቡ ነው በእንግድነት ያስመረጠው፡፡

የእኔ የትዝብት ቅኝትም የሚዳስሰው የትንሹን ልጅ ታሪክ ነው፡፡ የቴሌቪዥኑ ብርቱ እንግዳ እንደነገረን ሁለቱን ልጆች እሱ ከሚኖርበት አዲስ አበባ ካመጣቸው ሰነባብቷል፡፡ ለዚህ ምክንያቱ የአባቱ መቸገርና ወደ ጸበል መግባት ነው፡፡ ልጆቹ እሱ ዘንድ ከመጡ ጀምሮ ግን የትምህርት ዕድል አላገኙም፡፡ ቀናቸውን ቴሌቪዥን በማየት ሊገፉት ግድ ብሏል፡፡

ከጸበሉ ቆይታ በኋላ ጤናው ያልተመለሰው ትንሽ ልጅም ወደ ሕክምና ደርሶ በድጋሚ ምርመራ ይደረግለታል። ይህ አጋጣሚ ግን ታሪኩን እንዳልነበረ ቀየረው፡፡ እስከዛሬ ከቫይረሱ ነጻ ነው ሲባል የኖረው ሕመምተኛ በደሙ ኤች አይ ቪ መኖሩ ተረጋገጠ፡፡ ይህ እውነት ለባለታሪኩ ወጣት ሌላ ሸክም ሆኖ ሕይወቱን አከበደው፡፡ ሁለት ታናናሾቹ ከቫይረሱ ጋር እየኖሩ መሆኑን አምኖ ለመቀበል እስኪቸገር ተፈተነ፡፡

ይህን እውነታ በቴሌቪዥን ጣቢያው ቀርቦ የሚነግረን ወጣት አሁን ጭንቀቱ በእጥፍ ከብዷል፡፡ ስለ ሕይወት ሸክሙ መፍትሔ ለመሻትም በአደባባይ ወጥቶ እውነታውን አጋርቷል፡፡ ይህን ታሪክ ከሁሉም ለየት የሚያደርገው ደግሞ ትንሹ ልጅ ስለራሱ ማንነት ፈጽሞ ያለማወቁ ነው። የዚህ ጽሑፍ ዋነኛ ትዝብትም በዚህ ጉዳይ ያተኩራል፡፡

ከታሪኩ ነገራ ለማወቅ እንደሚቻለው ልጆቹ ትምህርት ቤት ስለማይሄዱ ውሏቸውን ቴሌቪዥን በማየት ያሳልፋሉ። ወጣቱ ደግሞ ትንሹ ልጅ ቫይረሱ እንዳለበት ፈጽሞ እንዲያውቅ አይፈልግም፡፡ እሱ ይህን ይበል እንጂ ሌሎች ሰዎችን ጨምሮ ታማሚው ያለማንም ነጋሪ የራሱን ታሪክ የሚያውቅበት ዕድል ሰፊ ነው፡፡

እንዴት ከተባለ ደግሞ ይህ ታሪክ ለተመልካች ተደራሽ በሚሆነው የቴሌቪዥን ስርጭት ሲተላለፍ ውሎ አያድርምና ነው፡፡ እንደሚታወቀው በቴሌቪዥን የቀረበው ፕሮግራም የማን ታሪክ እንደሆነ ግልጽ ነው። ባለቤቱ ማንነቱን በይፋ ካስተዋወቀ ደግሞ ቤተሰቡንና ኑሮውን ለመለየት አይቸግርም፡፡ ይህ ሀቅ ባለበት ሁኔታም ጉዳዩን መስጥሮ «ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ» ማድረጉ ትርጉሙን ያዛባዋል፡፡

የሚያስገርመው ጉዳይ ወጣቱ እውነታውን ለወንድሙ አልነግረውም ማለቱ ላይ አይደለም፡፡ የጣቢያው አዘጋጆች ብዙ እያወቁ «ንገረው፣ አትንገረው» ከሚሉት ምክር መግባታቸው እንጂ፡፡ ወዳጆቼ! እስቲ እናንተም ቆም ብላችሁ አስቡት፡፡

ይህ ልጅ ታሪኩን የሚያወጋለት የራሱ ወንድም ነው። ተናጋሪው ደግሞ ፈጽሞ ራሱን ሊደብቅ አልሞከረም፡፡ ከመነሻው አንስቶ እየገለጸ የቀጠለው የመላውን ቤተሰብ ታሪክ ነበር፡፡ ስሙን አልጠራም እንጂ ስለማን እንደሚያወራ ግልጽ ሆኖ ተቀምጧል፡፡ ሁሉም ጉዳይ ለሁሉም እንዲህ ይፋ በሆነበት አጋጣሚ «በዕድሜ እስኪበስል ህመሙን ልነግረው አልፈልግም» ማለቱ እንደኔ ጉዳዩን የሞኝ ተረት ከማድረግ አያንስም፡፡

ይህ ልጅ ዕለቱን ከቴሌቪዥን እይታ እንደማይርቅ እየታወቀ ሙሉውን ሃሳብ ሳይቆርጡ ማስተላለፍም ከተጠያቂነት አያድንም፡፡ ፕሮግራሙ አርታኢ (ኤዲተር) የለውም እንዴ? ሊያስብልም ይችላል፡፡ በእነሱ ቤት ይህ ልጅ ዕድሜው እስኪበስል አያውቅም፣ አይሰማም ማለት ነው።፡ የቴሌቪዥኑ ጉዳይስ? አንድ አበባል አለ «አትንገር ብዬ ብነግረው አትንገር ብሎ ነገረው» ይሉት ተረት፡፡

እንዲህ ዓይነቱ ትንሽ የሚመስል ስህተት ሊያስከትል ከሚችል ድንገተኛ ድንጋጤ ባለፈ የሞራል ስብራቱ ይከፋል፡፡ እኔ ግን እላለሁ፤ ከመጣደፍ ይልቅ ቆም ብሎ ማሰብ ይቀድማል፡፡ ምክሬም ትዝብቴም ነው፡፡

# ዓለም አቀፍ

## ሩሲያ 'ከዓለም አቀፉ የኑክሌር ሙከራ እግድ ስምምነት' ወጣች

በጋዜጣው ሪፖርተር

ሩሲያ 'ከዓለምአቀፉ የኑክሌር ሙከራ እግድ ስምምነት' ወጣች።

ሩሲያ በዓለም አቀፍ ደረጃ የኑክሌር ሙከራ እንዳይደረግ ከሚያግደው ስምምነት መውጣቷን አስታወቀች።

ፕሬዚዳንት ፑቲን በትናንትናው እለት ሩሲያ ካጸደቀችው እና በዓለም አቀፍ ደረጃ የኑክሌር ሙከራን ከሚያግደው ስምምነት የወጣችበትን ሕግ መፈረማቸውን ሮይተርስ ዘግቧል።

የጦር መሣሪያ ሕጎች እንዲከበሩ የሚጠይቁ ድርጅቶች የሩሲያን ከስምምነቱ የመውጣት ውሳኔ አውግዘዋል። ይህ ውሳኔ ከ1962 የኩባ የኑክሌር ቀውስ ወዲህ በአሜሪካ እና በሩሲያ መካከል ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የደረሰውን ግንኙነት የበለጠ ያቀዛቅዘዋል ተብሏል።

አሜሪካ በሩሲያ ውሳኔ በጣም እንደሚያሳስባት ገልጻለች።

"የሩሲያ ውሳኔ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን የጦር መሣሪያ ቁጥጥር ወጣች። ችግር ውስጥ የሚያስገባ ነው" ሲሉ የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒዮ ብሊንከን ተናግረዋል።

ሞስኮ ካጸደቀችው ኮምፕሪሄንሲቭ ኑክሌር ቴስት ባን (ሲቲቢቲ) የወጣችው ሩሲያን ስምምነቱን ፈርማ ካላጸደቀችው አሜሪካ ጎራ ለማሰለፍ ነው ብላለች።

አሜሪካ የማትጀምር ከሆነ ሩሲያ የኑክሌር ሙከራ እንደማታደርግ የሩሲያ ዲፕሎማት ተናግረዋል።

ነገር ግን የወሰኑ የምዕራባውያን የጦር መሣሪያ ባለሙያዎች በዩክሬን ጦርነት እያካሄደች ያለችው ሩሲያ ለማስፈራራት የኑክሌር ጦር መሣሪያ ልትሞክር ትችላለች የሚል ስጋት አላቸው።

ፕሬዚዳንት ፑቲን ግን ባለፈው ጥቅምት ወር ሩሲያ የኑክሌር ጦር መሣሪያ ሙከራ ትጀምራለች ወይስ አትጀምርም ለማለት ዝግጁ አለመሆናቸውን ገልጸው ነበር።



ፕሬዚዳንት ፑቲን ሩሲያ ካጸደቀችው እና በዓለም አቀፍ ደረጃ የኑክሌር ሙከራን ከሚያግደው ስምምነት የወጣችበትን ሕግ ፈርመዋል

## የጣልያን ጠቅላይ ሚኒስትር በሩሲያ ድምጽ አስመሳዮች መታለላቸው ተገለጸ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የጣልያን ጠቅላይ ሚኒስትር በሩሲያ ድምጽ አስመሳዮች መታለላቸው ተገለጸ፡፡

በቅጽል ስማቸው ቮቫን እና ልክሰስ የተሰኙት ሩሲያዊያን ድምጻቸውን በማስመሰል የሀገራት መሪዎችን እና ታዋቂ ሰዎችን በማዋራት ይታወቃሉ።

ከሰሞኑ ደግሞ ለጣልያኗ ጠቅላይ ሚኒስትር ጎርጊያ ሜሎኒ ራሳቸውን የአፍሪካ ዲፕሎማት አስመስለው ስልክ መደወላቸውን ዩሮ ኒውስ ዘግቧል፡፡

እንደዘገባው ከሆነ ጠቅላይ ሚኒስትር ሜሎኒ የአውሮፓ መሪዎች በዩክሬን ጦርነት ጉዳይ መማረራቸውን ተናግረዋል ተብሏል፡፡

አውሮፓዊያን ዩክሬን ከሩሲያ ጋር በመደራደር ጦርነቱ እንዲቋጭ እንደሚፈልጉ የተናገሩት ጠቅላይ ሚኒስትር ሜሎኒ በሆነ ምክንያት ይህ ጦርነት እንዲቆም እንፈልጋለን እንዳሉም ተገልጿል፡፡

በጦርነቱ ጉዳይ ሁላችንም ደክሞናል፣ የዩክሬንም የመልሶ ማጥቃት በታሰበው ልክ ውጤታማ ሊሆን አልቻለም በሆነ መንገድ ከዚህ ጦርነት መውጣት እንፈልጋለን ሲሉም ተደምጠዋል ጠቅላይ ሚኒስትር ሜሎኒ፡፡

ዩክሬናዊያን የሚችሉትን እያደረጉ ነው የዓለም አቀፍ ሕግን ባልጣሰ መልኩ ጦርነቱ በሰላም የሚጠናቀቅበት መንገድ መፈለግ አለበት ሲሉም ተደምጠዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሯ ራሳቸውን የአፍሪካ መሪ እንደሆኑ ከደወሉላት ሩሲያዊያን ጋር ለ13 ደቂቃ በስልክ ቆይታ አድርገዋልም ተብሏል፡፡



የጣልያን ጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ቆይቶ ባወጣው መግለጫ ጠቅላይ ሚኒስትር ጆርጂያ ሜሎኒ በሩሲያዊያኑ ድምጽ አስመሳዮች በመታለላቸው መጸጸቱን አስታውቋል፡፡

ጽህፈት ቤታቸው አክሎም ጠቅላይ ሚኒስትሯ ስልኩን ያነሱት ከአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን የተደወለላቸው መስሏቸው እንደሆነም ገልጿል፡፡

የጣልያን ፖለቲከኞች በጠቅላይ ሚኒስትር ጆርጂያ ሜሎኒ ላይ ትችቶችን ሰንዝረዋል የተባለ ሲሆን የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ማቲዮ ሬንዚ እና ጉሴፔ ኮንቴ ዋነኞቹ ናቸው፡፡

የቀድሞ የጣልያን ጠቅላይ ሚኒስትሮች እንዳሉት ጆርጂያ ሜሎኒ ተላላ ናቸው፣ ለጣልያናዊያን ያልነገሩትን እውነት ለሩሲያዊያን ተናግረዋል እና ሌሎችንም ትችቶችን ሰንዝረዋል፡፡

ሩሲያዊያኑ ድምጽ አስመሳዮች ከዚህ በፊት የዩክሬንን ፕሬዝዳንት ቮሎዶሚር ዘለንስኪን ጨምሮ ሌሎች መሪዎችን በስልክ እየደወሉ ብዙ ሚስጢሮችን እና ሃሳባቸውን በማውጣጣት ይታወቃሉ ሲል የዘገበው አል ዓይን ነው፡፡

ማህበራዊ

# መጋቢ አዕምሮ

## ተስፋ መቁረጥ ስምን?

አስናቀ ፀጋዬ



ልክ የዛሬ ዓመት አንድ ወጣት የዚህ ዓለም ኑሮ እንደመረረውና በራሱ ተስፋ እንቆረጠ ተናግሮ ይህችን ምድር በራሱ ፍቃድ ተሰናብቷል፡፡ በቅርቡ ደግሞ በተመሳሳይ አንዲት ወጣት ‹‹ዓለማዊ ኑሮ በቃኝ፤ ያኛው ዓለም ይሻለኛል እናንተም ወደእኔ ኑ›› ብላ ለሌሎችም የሞት ግብዣ አቅርባ ራሷን አጥፍታለች፡፡ ሌሎችም ወጣቶች በእንዲህ ዓይነቱ መንገድ ገና ብዙ መሥራት በሚችሉበት እድሜ ራሳቸውን አጥፍተዋል፡፡

ድሮ ድሮ በኢትዮጵያ ራስን ማጥፋት እንደ ትልቅ ነውር የሚቆጠር ተግባር ነበር፡፡ እንዲህ ታስቦበትና አስቀድሞ ለመሞት ተናዞ የሚደረግም አልነበረም። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ራስን ማጥፋት በኢትዮጵያ ብዙም እንግዳ የሆነ ነገር አይደለም፡፡ ይሁንና አሁን አሁን እንዲህ ዓይነቱ ራስን የማጥፋት ተግባር ባልተለመደ መልኩ በኢትዮጵያ እየጨመረ መጥቷል። በዚህ መልኩ የሚከወነው ራስን የማጥፋት ተግባር ታዲያ በብዛት በወጣቶች ዘንድ እየተስተዋለ ነው፤ ድርጊቱ አንዱ ሌላኛውን እየሳበም ይገኛል፡፡

ሰው ራሱን ለምን አጠፋ ብሎ እንዲሁ በደፈናው መኮነን አይቻልም፡፡ ምክንያቱም ራሱን ለማጥፋቱ በርካታ ምክንያቶች ይኖሩታል፡፡ ግን ደግሞ ራስን ከማጥፋት የሚገኝ ነገር የለም፡፡ ከመጥፋት መኖር ይሻላል፡፡ ሰው ራሱን ሲያጠፋ ‹‹የሞተ ተጎዳ›› የሚባለው ተረት ለእርሱ ብቻ አይሰራም፡፡ እርሱ በሕይወት እያለ የእርሱን መኖርና ድጋፍ የሚሹ አሉና ሞቱ ሌሎችንም ይጎዳል፡፡ ስለዚህ በአንድ ጊዜ ተስፋ ቆርጦ ለመሞት መወሰን እጅግ ይከብዳል፡፡

ዘመናት በተቀያየሩ ቁጥር የሕዝብ አኗኗር ሁኔታ፣ የኢኮኖሚ፣ ፖለቲካና ማህበራዊ ገጽታም አብሮ ይቀየራል፡፡ በተለይ ደግሞ በዚህ የቴክኖሎጂ ዘመን ነገሮች በሰከንዶች ውስጥ ይቀየራሉ፡፡ በርግጥ ያለፈውም የአሁኑም ጊዜ አንድ ዓይነት ቢሆንም የአሁኑ ጊዜ በፍጥነት እየበረረ እንደሆነ ብዙዎች ይሰማቸዋል። ይህም ሰዎች ከሥራ ባለፈ በተለያዩ የግልና የጋራ ጉዳዮች ላይ መወጠርና ጊዜ ከማጣት የመነጨ ነው፡፡ በዚህ የሩጫ ዘመን ታዲያ አንዱን ሲያገኙ ሌላ ማጣት ይኖራል፡፡ አንዱን ሲሳኩ በሌላ በኩል መውደቅ አለ፡፡ አንዱን ሲጨብጡ በዛኛው በኩል ሌላኛውን መልቀቅ ያጋጥማል።

ይህ በሕይወት ኡደት ውስጥ የሚያጋጥምና በሰዎች ተፈጥሯዊ ባህሪ ውስጥ የተለመደ ጉዳይ ነው፡፡ እንግዲህ እዚህ ጋር ነው የሰው ልጅ መከራው ሲበዛበት፣ ጥረቱ መና ሲቀር፣ ያሰበው ሳይሳካ ሲቀር፣ ልፋቱ ከንቱ ሲሆን ተስፋ ቆርጦ ራሱን ለማጥፋት የሚነሳው፡፡ ከራሱ ጋር ሲጋጭና መስማማት ሲያቅተው ነው የሞትን መንገድ የሚመርጠው፡፡ ብሎ ብሎ አልሆንለት ሲለው፤ ነገም ሌላ ቀን ነው እና ከዛሬ ነገ ይሻላል ብሎ ሌላ ሙከራ ማድረግ ሲያቅተው ነው ሞት አማራጭ መስሎ የሚታየው፡፡

ዛሬ ላይ የፖለቲካ ውጥንቅጥ፣ የኑሮ ውድነት፣ በሽታ፣ ጦርነት፣ ስደት፣ መፈናቀልና ሌሎችም ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታዎች በምድራችን እየበዙ መጥተዋል። የሕይወት ትግሉ በርትቷል፡፡ የኑሮ ውጣ ውረዱ አይሏል፡፡ የእርስ በርስ ፉክክሩና ፍትጊያው ጨምሯል። ገንዘብ አልበረከት ብሏል፡፡ ፍቅርም እንደዛው፡፡ እነዚህና መሰል ስንክሳሮች ብዙዎችን ተስፋ እያስቆረጡ ነው፡፡ ከመንገድም እያስቀሩ ነው፡፡ ብዙዎች ሞትን እንደመጨረሻ አማራጭ እንዲወስዱ እያስገደደም ይገኛል፡፡

አንዳንዴ የትግላችን፣ የጥረታችን፣ የልፋታችን ውጤት መና የቀረ የሚመስልበት ጊዜ አለ፡፡ ውጥናችን ውሃ አልቋጥር፣ ጠብ አልል ሲለን፣ መንገዱ ሁሉ ረዥም፣ በሮች ሁሉ ዝግ፣ ጩኸቱ ሁሉ ሰሚ አልባ ሲመስለን በመጨረሻ የምንወስደው መፍትሄ ዓለምን ሁሉ መተውና መሸነፍ ይሆናል፡፡ ከዚህ በኋላ አበቃ ማለት እንጀምራለን። እንኳን እኛ ቀርቶ ሌሎች እንኳን እንዳይበረቱ ‹‹ባክህ እኛም ብለነው ብለነው አቅቶን ነው›› እያልን ተስፋ እናስቆርጣቸዋለን፡፡ የተስፋ መቁረጥ ሕመማችንን ሌሎች ላይም አጋብተን አጥፍተን መጥፋት እንፈልጋለን፡፡

ነገር ግን ሰው መልፋት፣ መትጋት፣ መታገልና መሮጥ ያለበት የት ነው? ሰው ተስፋ መቁረጥ ያለበት የት ደረጃ ሲደርስ ነው? የመንገዱ ማለቂያው የት ነው? ውጤቱን ዛሬ ያላየነው ነገ ሁሉ ውጤት አልባ ሆኖ ሊቆጠር ይችላልን? በታሰበው ጊዜ ያልተደረሰበት ነገር ሁሉ ሊደረስበት የማይችል ነገር ነው ማለት ነው? መንገዱስ እኛ የያዝነው ብቻ ነው? በሌላስ መንገድ ሊሞከር አይቻልምን? ለመሆኑ ከማቆምና ከመቀጠል የትኛው ይመረጣል? ከማቆም ምን ይገኛል? የሚሉትና ሌሎች መሰል ጥያቄዎችን መመለስ ይገባል፡፡

ተስፋ ቆርጦ የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ከመድረስ በፊት ተስፋ ያስቀረጠንን ምክንያት ማወቅና በሚገባ መመርመር ያስፈልጋል፡፡ ተስፋ ያስቀረጠንን ጉዳይ በሚገባ ካወቅንና ከመረመርን ደግሞ ይህን ተስፋ ያስቀረጠንን ምክንያት እንዴት አድርገን መቀልበስና በሌላ አማራጭ መተካት እንደምንችል መንገዶችን መለየት ይገባናል፡፡ ሌሎች ወደ ተስፋ የሚመልሱ መንገዶች መልካም ሆነው ካገኘናቸው እሰየው ብለን ወደፊት መቀጠል ነው፡፡ ሆኖም አሁንም የመረጥናቸው መንገዶች ዳግም ተስፋ የሚያስቆርጡ ከሆኑ እንደገና ሌላ መንገድ መፈለግ እንጂ ተስፋ ቆርጦ ያልሆነ ውሳኔ መወሰን ተገቢ አይደለም፡፡

ከተስፋ መቁረጥ በቀር የሚዳዝ ሰው ጊዜው ይረዝም ይሆናል እንጂ አንድ ቀን የሚፈልገው ቦታ ይደርሳል። የቆመ ሰው ግን እንኳንስ ወደሚፈልግበት ለመሄድ ይቅርና ወደተነሳበት ቦታም ተመልሶ አይደርስም፡፡ የሚታገል ሰው አንድ ቀን ያሸንፋል። የቆመ ሰው ግን ሳይማረክ እጁን ሰጥቷል፡፡ ደጋግሞ የሚያንኳኳ ሰው ከተገኙት ሰዎች ውስጥ አንዱን መቀስቀሱ አይቀርም፡፡ ማንኳኳት ያቆመ ግን እንኳንስ ሊቀሰቅስ ቀርቶ እራሱም የተኛ ነው፡፡ አስቀድሞ በራሱ ላይ ሞት ፈርዷል፡፡

የሚሄድ መኪና ጋራዥ ይደርሳል፡፡ የቆመ መኪና ግን ባለበት ይወላልቃል፡፡ ለማሸነፍ ትልቁ መፍትሔ አቋምን መቀየር ሳይሆን መንገድን መቀየር ነው። የተለያዩ ነገሮችን መሞካከር ሳይሆን አንድን ነገር በተለያዩ መንገዶች መሞከር ነው፡፡ የተለያዩ ነገሮችን ማየት ሳይሆን አንድን ነገር በተለየ እይታ መመልከት መቻል ነው፡፡ ተስፋ መቁረጥ ሳይሆን በውሳኔ ጊዜ መቁረጥ መቻል ነው፡፡ ራስን ማጥፋት ትልቁ የስንፍና ውጤት ነው፡፡ እናም ወዳጄ! የምታገኘውን ሞት ከመመኘት የማታገኘውን ሕይወት በሚገባ መኖር መቻል አለብህ፡፡

ከተሸነፉት መማር ያለብን እኮ ለምን ተሸነፉ የሚለውን እንጂ የጥረት መጨረሻው መሸነፍ አይደለም። ሽንፈት እኮ ትምህርት አያስፈልገውም። ሽንፈት እኮ ልምድ አያስፈልገውም፡፡ ሽንፈት እኮ እውቀት አያስፈልገውም። ሽንፈት እጅን አጣጥፎ መቀመጥ ብቻ ይበቃዋል፡፡ ለሽንፈት ምሳሌ መጥቀስ አያስፈልግም፡፡ ሽንፈት ማለት በቀላሉ የሚደርስበት ነገር ነው፡፡ ሳይለፉ የሚያገኙት ነገር ነው፡፡ ምሳሌ፣

**‹‹ሽንፈት እኮ ትምህርት አያስፈልገውም፡፡ ሽንፈት እኮ ልምድ አያስፈልገውም። ሽንፈት እኮ እውቀት አያስፈልገውም። ሽንፈት እጅን አጣጥፎ መቀመጥ ብቻ ይበቃዋል። ለሽንፈት ምሳሌ መጥቀስ አያስፈልግም። ሽንፈት ማለት በቀላሉ የሚደረስበት ነገር ነው። ሳይለፉ የሚያገኙት ነገር ነው። ምሳሌ፣ አርዓያ፣ ልምድ፣ እውቀት፣ ጥበብ የሚያስፈልገው ድል ብቻ ነው፡፡ ስኬት ብቻ ነው።››**

አርዓያ፣ ልምድ፣ እውቀት፣ ጥበብ የሚያስፈልገው ድል ብቻ ነው፡፡ ስኬት ብቻ ነው፡፡ እርሱ በቀላሉ ስለማይገኝ ካገኙት ሰው ልምድና ጥበብ መቅሰም ያስፈልጋል፡፡ እንዲህ ማድረግ ሲቻል ነው ከተሸናፊነት ወደ አሸናፊነት መሻጋገር የሚቻለው፡፡

ብርቱ ጥረት የሚያደርጉ ሰዎች በጥረታቸው ውስጥ ደስታን ያገኛሉ፡፡ ጥረት የሚያደርጉና አስቀድመው የተሸነፉ ሰዎች ግን ሁሌም በሀዘን ውስጥ ናቸው፡፡ ጥረት እኮ ባይሳካ እንኳን ደስታን ያጎናፅፋል፡፡ ከቁዘማና ከድብርት ነፃ ያወጣል፡፡ የሚጥር ስለነገ ያቆመ ስለትላንት ያስባል፡፡ የሚጥር ስለኑሮው ያቆመ ስለሞት ያስባል። በሩጫ ዓለም በመጀመሪያው ዙሮች ቀዳሚውም መጨረሻውም እኩል ናቸው፡፡ እንደውም አንዳንዴ ተሸናፊው ከአሸናፊው የተሻለ መስሎ የሚታይበት ጊዜ አለ፡፡ ግን ደወል ይደወላል፡፡ ያን ጊዜ አሸናፊውም ተሸናፊውም ይለያል፡፡

የሌላ ሰው እገዛ ውጤት የሚያመጣው የራስ ጥረት ካለ ብቻ ነው፡፡ አፉን ያልከፈተ ሰው ማጉረስ፤ ላልተነፈሰውም ሰው ጉርሻ(ቦነስ) መስጠት አይቻልም። ከመቆም ምንም አይገኝም፡፡ በቃኝ ብሎ ተስፋ ከመቁረጥ አንዳች ትርፍ የለም፡፡ ነገር ግን በጥረት ውስጥ ደስታና ጥንካሬ አለ፡፡ በጥረት ውስጥ ተስፋና አሸናፊነት አለ። ትጋት ከቁዘማና ከድብርት ነፃ ያወጣል። አስተውል! የሚጥር ስለነገ ያቆመ ስለትላንት ያስባል፡፡ የሚጥር ስለኑሮው ያቆመ ስለሞት ያስባል፡፡

ዛሬ ላይ የሚታዩ ነገሮች ሰዎችን ለጊዜው ተስፋ ሊያስቆርጡ ይችላሉ፡፡ የኑሮው ሁኔታ፣ ውጣውረዱ፣ እንግልቱ ሊያሰለች ይችላል፡፡ እዛም እዚም የሚደመጡ የሰዎች ሞት፣ ስደት፣ መፈናቀልና ሰቆቃ ያሳምማሉ፡፡ ሰላምና መረጋጋጥ መጥፋቱም እጅግ ተስፋ ሊያስቆርጥ ይችላል፡፡ መከራና ግፉም ያስመርራል፡፡ ነገር ግን ከዛሬ ነገ ይሻላልና የነገውን ጥሩ ለማድረግ ዛሬ ላይ ተስፋ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ተስፋ ከመቁረጥ ተስፋ ማድረግ ይሻላልና፡፡

እናም ወዳጄ ብትወድቅ ብትከፋም ያለኸውና የምትኖርበት እዚቹ ምድር ላይ ነው፡፡ ስለዚህ ተፍጨርጨርባት፣ ሥራባት፣ ሌላውን ሳታሰናብት አንተ አትሰናበት፡፡ እስከመጨረሻው ጣር፡፡ መቼም መብቴ ብለህ ወደህ መርጠህ ወደዚች ምድር አልመጣህም፡፡ ምድሯም አንተን ለማኖር ምንም አልጠበባትም፡፡ ስለዚህ ወደዚች ምድር እስከመጣህ ድረስ የመጨረሻውን የሞት ፅዋ እስክትጎነጭ ድረስ በምድሯ ላይ ሥራ፡፡

ተስፋ ለቆረጡ ሰዎች መድኃኒት ይሆን ዘንድ ጀኒ ራጋ፣ ዘሪቱ ከበደና አብነት አጎናፍር እንዲህ ሲሉ አቀንቅነዋል፤ አንተም ቢሆን ግድ የለም ተስፋ መቁረጡን ተወውና እስቲ ይህ ሙዚቃ አዳምጠው.......

አብነት አጎናፍር፡- ብትወድ ብትከፋህ የያዘችህ ቤትህ ዓለም

ሳታሰናበት መሰናበት በራስ የለም
መች መብቴን ብለህ ወደህ መርጠህ መጣህባት
መብትህ ነው ብላለች አንተን ማኖር መች ጠበባት

ዘሪቱ ከበደ፡- ኖሮ ሳይቀምሳት ማን ኑርባት ሞክር አለህ

እንዳንተ ሆኖ ኖሮም አይቶ እያት አለህ
ነፍሴን ጠላኋት ብለህ የውሸት አትካዳት
ለሌላው ሁንና ኖረህ የእውነት አትውደዳት

ጀኒ ራጋ፡- ግድ ነው ኑሮን መላመድ
ከኛ ጋር ሆነሃል ዘመድ
ላንተ የሚሆን መቼ አንሶን ቦታ
መሄድክን አናይ በቸልታ
መኖርህን ሌሎች ይሻሉ ይፈልጋሉ
በሕይወት እስካለህ ድረስ ይበረታሉ
የኔ መኖር ነው ላንተ መኖር ያንተም ለኔ
ለሕይወት አብረን እንዘምር ቁም ከጎኔ

በጋራ፡- ኑር ባታምንም ላንተ ባይመስልም
ለከንቱ አልተፈጠርክም
የዛሬው ሕይወትህ ባይሞቅም
ነገም ካንተ ውጭ አይደምቅም
ድፈር ክረም ኑር በሕይወት
ለሌሎች አቁያት
ፈሪ ነው የሰው ያልሞገተው
ሳይገሉት ቀድሞ የሚሞተው .......

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# መነሻውን ዕውቀትና ልምድ ያደረገው አሚጎስ

ፍሬሕይወት አወቀ

ብርቱዎች የዕለት ኑሯቸውን ለማሸነፍ ብሎም ነገን የተሻለ ለማድረግ ዛሬ ላይ በብዙ ይጥራሉ፤ ይውተረተራሉ፡፡ ለጥረታቸው ስኬትም የተለያዩ አማራጮችን ይጠቀማሉ፡፡ ከእነዚህ አማራጮች መካከል የገንዘብ ቁጠባና ብድር የፋይናንስ ተቋማት ይገኙበታል። የቁጠባና ብድር ተቋም ሰዎች የቆጠቡትን ገንዘብ እስከተወሰነ እጥፍ ድረስ መበደር የሚችሉበትን ዕድል ይፈጥራል፡፡ በዚህም በርካታ ሰዎች ጓዳ ጎድጓዳቸውን ሲያሟሉ፣ ጥሪት ሲያፈሩ፣ የተለያዩ የንግድ ሥራዎችን ሲጀምሩና ሲያስፋፉ ይስተዋላል፡፡

ሀገራት የሚሰሩበትና ኢትዮጵያ ውስጥም እየተስፋፋ የመጣው የቁጠባና ብድር አገልግሎት ተቋም ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው ጉልህ ነው፡፡ ሰዎች ሀብትና ንብረት በማፍራት ነገን የተሻለ ለማድረግ ሲያስቡ ገንዘብ በብድር ማግኘትን ተቀዳሚ ጉዳያቸው ያደርጋሉ። ለዚህ ጥያቄም ለአባላት በቅርበት የሚገኙት የቁጠባና ብድር ተቋማት ምላሽ አላቸው፡፡

በኢትዮጵያም በርካታ የብድርና ቁጠባ ተቋማት ይንቀሳቀሳሉ፡፡ የተቋማቱ አባላት የብድርና ቁጠባ አገልግሎት ተጠቃሚ በመሆን ችግሮቻቸውን መፍታት፣ ጥሪት ማፍራት፣ ሀብት ማግኘት የቻሉባቸው ሁኔታዎች በርካታ ናቸው፡፡ የቁጠባ ማህበራቱም ከአባላት መዋጮ ተነስተው ብዙ ቢሊየን ብር እስከማንቀሳቀስ የደረሱበት ሁኔታ የሚታይ ሲሆን፣ ወደ ባንክ ያደጉም እንዳሉ ይታወቃል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኙ የቁጠባና ብድር ተቋማት መካከል አሚጎስ የቁጠባና ብድር ህብረት ሥራ ማህበር አንዱና ቀዳሚ ተጠቃሹ ነው፡፡ ‹‹ድር ቢያብር አንበሳ ያስር›› እንዲሉ በሥራና በትምህርት የሚተዋወቁ ጓደኛሞች ተሰባስበው ያቋቋሙት አሚጎስ የቁጠባና ብድር ህብረት ሥራ ማህበር፤ ማህበረሰቡ የቁጠባ ባህሉን ማሳደግ እንዲችልና ኑሮውን በማሻሻል ነገን ተስፋ እንዲያደርግ ላለፉት አስር ዓመታት ሲተጋ ቆይቷል፡፡

በአስር ዓመት የሥራ እንቅስቃሴውም የአባላቱን ቁጥር አስፍቷል፤ ገቢውንም ከዓመት ዓመት እያሳደገ ውጤታማ ሥራ መሥራት ችሏል፡፡ በ20 አባላት በዘጠኝ ሺ ብር ካፒታል የተጀመረው አሚጎስ የቁጠባና ብድር ህብረት ሥራ ማህበር በአሁኑ ወቅት / ስድስት ሺ / 6000 አባላትን ማፍራት ችሏል፤ ካፒታሉንም ሁለት ቢሊዮን የሚጠጋ ነው፡፡

የዕለቱ የስኬት እንግዳችን የአሚጎስ ቁጠባና ብድር ህብረት ሥራ ማህበር መሥራችና ሥራ አስኪያጅ አቶ ፍጹም አብርሃ ነው፡፡ አቶ ፍጹም በትግራይ ክልል ነው ተወልዶ ያደገው፡፡ ከ8ኛ ክፍል እስከ ዩኒቨርሲቲ ያለውን ትምህርቱን በአዲስ አበባ ተከታትሏል፡፡

የዩኒቨርሲቲ ትምህርቱን ኢኮኖሚክስ ላይ ትኩረት አድርጎ መከታተል መቻሉ ደግሞ ለዛሬ ማንነቱ እንደጠቀመው ይናገራል፡፡ የዩኒቨርሲቲ ትምህርቱን ባጠናቀቀ ማግስት በአንድ የፋይናንስ ኩባንያ ውስጥ ከፋይናንስ ጋር በተያያዘ በማማከር አገልግሎት ተቀጥሮ ለአምስት ዓመታት አገልግሏል፡፡

የኢኮኖሚክስ ትምህርቱን በሥራ ላይ ባዋለበት ጊዜ የቁጠባን ጥቅም በሚገባ መረዳት መቻሉን የሚናገረው አቶ ፍጹም፣ በተለይም ህብረት ሥራ ማህበር፣ ማይክሮ ፋይናንስ፣ ባንኪንግ ወዘተ... ምን ማለት እንደሆነና ጠቀሜታውን ጭምር መረዳት መቻሉን ይናገራል፡፡ በትምህርት ያገኘውን ዕውቀት እንዲሁም በሥራ ዓለም ያካበተውን ልምድ ቀምሮ የቁጠባና ብድር አገልግሎት ህብረት ሥራ ማህበር ለማቋቋም ከልቡ ተማክሯል፡፡ ምክሩን ወደ ተግባር ለመቀየር ጊዜ ሳይወስድ ከሁለት ጓደኞቹ ጋር ማህበሩን የማቋቋም ሥራ እንደጀመረ ይናገራል፡፡

ሰዎች ቁጠባን ባህል ቢያደርጉ ነገን የተሻለ ማድረግ እንደሚችሉ በልኩ የተረዳው አቶ ፍጹም፤ ከሁለት ጓደኞቹ ጋር በወር ሃምሳ ብር በመቆጠብ ቁጠባው ‹‹ሀ›› ብሎ እንደተጀመረ ያስታውሳል። በወቅቱ አንደኛው አባል ሃምሳ ብር መቆጠብ ባለመቻሉ አርባ ብር ቆጥቦ



አቶ ፍጹም አብርሃ

**በ20 አባላት በዘጠኝ ሺ ብር ካፒታል የተጀመረው አሚጎስ የቁጠባና ብድር ህብረት ሥራ ማህበር በአሁኑ ወቅት / ስድስት ሺ / 6000 አባላትን ማፍራት ችሏል፤ ካፒታሉንም ሁለት ቢሊዮን የሚጠጋ ነው**

በወር 140 ብር ሲቆጥቡ ቆይተዋል፡፡ ከስምንት ወራት ቁጠባ በኋላ ግን በማህበር በመደራጀትና አባላቱን በማብዛት የበለጠ ተጠቃሚ መሆን እንደሚቻል በማመን ጓደኞቹን አሳምኖ ተጨማሪ አባላትን በማምጣት ወደ ማህበር ምስረታው ተገባ ፡፡

የፋይናንስ ህብረት ሥራ ማህበር ብዙ ካፒታል የማይፈልግና በቀላሉ የሚጀመር መሆኑ የገባው አቶ ፍጹም፣ በፍጥነት ወደ ማህበር ምስረታው ገባ፤ ሰዎች ቆጥበው እንዲበደሩ በማድረግ ወለድ እንደሚያገኙና ገቢ እንደሚኖራቸው ከጓደኞቹ ጋር በመመካከር አባላቱን ማብዛትና የአባላቱ ቁጥር ሲጨምርም የገቢ መጠናቸው እንደሚያድግ በመረዳት በዘጠኝ ሺ ብር ካፒታልና በ20 አባላት አሚጎስ የቁጠባና ብድር ሕብረት ሥራ ማህበርን ከጓደኞቹ ጋር መሰረተ፡፡

በቁጠባና ብድር ህብረት ሥራ ማህበር አማካኝነት ብዙ ሀገራት ማደግ እንደቻሉ የጠቀሰው አቶ ፍጹም፤ ብዙም ገቢ የሌላቸውና በገጠር የሚኖሩ ዜጎች ቁጠባን ባህል አድርገው ተጠቃሚ ሲሆኑ በሥራ አጋጣሚ መመልከት መቻሉን ይገልጻል፡፡ ለዚህም ነው በሥራ ያካበተውን ልምድ ካለው የኢኮኖሚክስ ዕውቀት ጋር ደምሮ ሥራውን ወደ ከተማ በማምጣት ከጓደኞቹ ጋር ቢሠራ ውጤታማ ሆኖ ትልቅ ደረጃ ላይ መድረስ እንደሚቻል ያመነው፡፡

ከሁለት ጓደኞቹ ጋር የተጀመረው ቁጠባም ሃያ አባላትን በማሰባሰብ በዘጠኝ ሺ ብር ካፒታል በወርሃ ጥር 2005 ዓ.ም በአራዳ ክፍለ ከተማ ህብረት ሥራ ማህበር ጽ/ቤት አሚጎስ የቁጠባና ብድር ህብረት ሥራ ማህበር በሚል ስያሜ ተደራጀ፡፡ በሥራና በትምህርት የሚተዋወቁ ጓደኛሞች ተሰባስበው የመሰረቱት ይህ ማህበርም በአሁኑ ወቅት አስር ዓመቱን አጠናቅቆ ለ11ኛ ዓመት የሥራ ውጤት እየተጋ ይገኛል፡፡ በእነዚህ ዓመታት ከአባላቱ ጋርም እንዲሁ በቆጠቡት ገንዘብ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚ መሆን እንዲችሉ በማድረግ ጥብቅ የሆነ ግንኙነትን መፍጠር መቻሉን አጫውቶናል፤ ከኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ባሻገር በጓደኛሞቹ መካከል ጠንካራ ግንኙነት መፍጠር መቻሉን ይገልጻል፡፡

አሚጎስ የቁጠባና ብድር ህብረት ሥራ ማህበር እስካሁን ባለው የሥራ እንቅስቃሴ ከሶስት ሺ ለሚልቁ አባላቶች ከሶስት ቢሊዮን ብር በላይ የብድር አገልግሎት መስጠት እንደቻለ የጠቀሰው አቶ ፍጹም፤ የብድር ዓይነቶቹም በትራንስፖርት ዘርፍ እንዲሁም በማኑፋክቸሪንግና በሌሎች ዘርፎችም ለተሰማሩ ማቅረብ እንደተቻለ አስረድቷል፡፡ ለአብነትም ቀደም ሲል በትራንስፖርት ዘርፍ ለ2 ሺህ 100 የራይድ አገልግሎት የሚሰጡ መኪኖችን ገዝቶ ለአባላቱ አስረክቧል፡፡

በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍም እንዲሁ ሚስማር የሚያመርቱ፣ በምግብ ዘርፍ የተሰማሩና የጽዳት ዕቃዎችን ፈሳሽ ሳሙና እና ሌሎችንም የሚያመርቱ አባላት የብድሩ ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ለቤት ውስጥ ቁሳቁስ በተለይም ኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎችን በመግዛት በርካታ አባላት ተጠቃሚ መሆን ችለዋል፡፡

ንግድ ለመጀመር ላሰቡና የጀመሩትን ለማስፋፋት ጭምር ብድር ያገኙ አባላት ስለመኖራቸው የገለጸው አቶ ፍጹም፤ ሰዎች መቆጠብ በመቻላቸው ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚ መሆን እንደቻሉ ያስረዳል፡፡ በተለይም የቁጠባና ብድር ተቋማት በተስፋፉበት በዚህ ወቅት በሚቆጥቡት ገንዘብ ጊዜያዊ ችግሮቻቸውን ከመሻገር ባለፈ ቋሚ ንብረት በማፍራት የገቢ ምንጭ መፍጠርና ኢኮኖሚያዊ አቅማቸውን ማጎልበት የቻሉ ሰዎች በርካቶች መሆናቸውን አስታውቋል፡፡ በዚህም አሚጎስ የቁጠባና ብድር ህብረት ሥራ ማህበር ቁጠባና አክሲዮን በመሰብሰብ የተሻለ የብድር አገልግሎት በማቅረብ የተሳለጡ የማህበራዊ ግንኙነቶችን እና ኢኮኖሚያዊ ለውጦችን በአባላትና በማህበሩ ዘንድ መፍጠር መቻሉን ነው የገለጸው፡፡

በአሁኑ ወቅትም መንግሥት ከተማ ውስጥ ያሉትን አሮጌ ላዳ ታክሲዎችን ለመቀየር እያደረገ ባለው ጥረት አሚጎስ የቁጠባና ብድር ህብረት ሥራ ማህበር ለባለታክሲዎቹ ብድር እያቀረበ መሆኑን የተናገረው አቶ ፍጹም፤ የአሚጎስ አባል የሆኑ ባለ ላዳ ታክሲዎችን የአዳዲስ መኪኖች ባለቤት ለማድረግ የጀመረውን ጥረት በማጠናከር በሀገር ውስጥ ከሚገኙና መኪና ገጣጥመው ከሚሸጡ ድርጅቶች ጋር በመዋዋል አዳዲስ መኪኖችን እንዲያቀርቡ እያደረገ ነው፡፡ አሁን ላይ 200 ታክሲዎችን በአዳዲስ መኪኖች ለመተካት ዝግጅቱ መጠናቀቁን ጠቅሶ፣ አባላቱ ከ20 እስከ 35 በመቶ ቆጥበው አዳዲስ መኪኖችን ከኩባንያው ማግኘት የሚችሉበትን ውል ፈጽመዋል ብሏል፡፡

ማንም ሰው የአሚጎስ የቁጠባና ብድር ህብረት ሥራ ማህበር አባል መሆን እንደሚችል አቶ ፍጹም ጠቁሟል፤ ማህበሩ ከፖለቲካ፣ ከኃይማኖትና ከብሔር ነጻ መሆኑን ጠቅሶ፣ ዕድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ ማንኛውም ሰው አባል መሆን እንደሚችል ነው ያስረዳው፡፡

ማህበሩ በአስር ዓመት የሥራ እንቅስቃሴ ውስጥ ያጋጠሙ ችግሮችን አስመልክቶም ሲያብራራም፤ አሁን ባለው የዋጋ ግሽበት ማህበሩ በእጅጉ እየተፈተነ መሆኑን ገልጿል፡፡ ማህበሩ የብድር አገልግሎቱን ባቀደው ልክ እንዳይሰጥና አባላቱም ብድሩን ባገኙ ጊዜ ገበያው ላይ ወጥተው የፈለጉትን መግዛት እያስቻላቸው አለመሆኑን የገለጸው አቶ ፍጹም፤ በየጊዜው የሚጨምረው የዋጋ ንረት የሰዎችን የመግዛት አቅም እያዳከመና የማህበሩን የማበደር አቅምም ውስን አድርጎታል ነው ያለው፡፡

ሌላው የሁሉም ነገር መሠረት የሆነው ሰላም በራሱ ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለው በመጥቀስ፤ የሰላምና ጸጥታ ሁኔታ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የፋይናንስ ተቋማት ላይ ተጽእኖ እንደሚያሳድር ጠቅሶ፣ ለዚህም በትግራይ ክልል ጦርነት በነበረ ወቅት የባንኮች መዘጋት ያሳደረው አሉታዊ ተጽዕኖ ከባድ እንደነበር አስታውሷል፡፡ ሰላም መሠረታዊ ጉዳይ መሆኑን ጠቅሶ፣ የሰላም እጦት ቢዝነሱን እንደሚጎዳ አመልክቷል፡፡

ባንኮች ከአብዛኛው ማህበረሰብ የሰበሰቡትን ገንዘብ ለጥቂቶች ወይም ትልቅ ሀብት ላላቸው የሚያበድሩ መሆናቸው የጠቀሰው አቶ ፍጹም፣ እንደ አሚጎስ የቁጠባና ብድር ህብረት ሥራ ማህበራት ያሉ ተቋማት ገንዘቡን ለቆጠበው አባል ሁሉ የሚያበድሩ በመሆናቸው ከባንኮች በእጅጉ ይለያሉ ይላል፡፡ ዓላማቸውም ሰዎች ገንዘባቸውን ቆጥበው መበደር እንዲችሉ ምቹ ሁኔታን መፍጠር እንደሆነ አስረድቶ፣ በዚህም አብዛኛውን የማህበረሰብ ክፍል ተደራሽ እንደሚያደርጉ ተናግሯል፡፡

አሚጎስ የቁጠባና ብድር ህብረት ሥራ ማህበር ለሌሎች አርዓያ መሆን እንዲችል በተለያየ ጊዜ ስልጠና እንደሚሰጥ የጠቀሰው አቶ ፍጹም፤ በተለይም በአራዳ ክፍለ ከተማ የሚገኙ ከትንሽ ተነስተው ትልቅ ደረጃ ላይ መድረስ ለሚፈልጉ የተለያዩ አካላት በዘርፉ ስልጠና ለመስጠት ከፍተኛ ጥረት መደረጉን ገልጿል። ይህም ማህበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት እያበረከተ ካለው አስተዋጽኦ መካከል ተጠቃሹ እንደሆነ አመላክቶ፣ ከዚህ በተጨማሪም በክፍለ ከተማው የሚገኙ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን አቅመ ደካሞች በማገዝ እንደሚሰራም ተናግሯል፡፡ ለተማሪዎችም የትምህርት ቁሳቁስ ከማሟላት ጀምሮ በርካታ ድጋፎችን ያደርጋል ብሏል። ሀገራዊ በሆኑ ጥሪዎችም እንዲሁ የነቃ ተሳትፎ በማድረግ ማህበራዊ ኃላፊነቱን እየተወጣ እንደሚገኝ አስታውቋል።

ሥራ አስኪያጁ እንደሚለው፤ የቁጠባና ብድር ተቋሙ 70 ለሚደርሱ ዜጎች በቋሚነት የሥራ ዕድል መፍጠር የቻለ ሲሆን፤ በትርፍ ጊዜ የሚሠሩ አስር የሚደርሱ ሠራተኞች/ አብዛኞቹ የዩኒቨርሲቲ መምህራን ናቸው/ አሉት፡፡ በቀጣይም ማህበሩ የአባላቱን ቁጥር በማስፋትና የብድር መጠኑን በማሳደግ የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት እየተጋ መሆኑን መሆኑን አመላክቷል፡፡ በተለይም የጀመረውን ሥራ አጠናክሮ በማስቀጠል የአባላቱን ቁጥር እስከ አስር ሺ ለማድረስና አምስት ቢሊዮን ብር ካፒታል ለማፍራት ዕቅድ እንዳለው አቶ ፍጹም ተናግሯል፡፡

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## ግንባታቸው እየተሳለጠ ያለው የከተማዋ የትራፊክ ማሳለጫ ድልድዮች

**ኃይሉ ሣህለድንግል**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገዶች ባለሥልጣን የከተማዋን የመንገድ መሠረተ ልማት ለማሻሻልና ለማዘመን እየሠራ ይገኛል፡፡ መንገዶች የአገልግሎት ዘመናቸው የተራዘመ እንዲሆን ለማድረግ የጥገና ሥራዎችን ይሰራል። በከተማዋ የተለያዩ አካባቢዎች በሚገኙ መንገዶች ላይ የከተማዋን የመንገድ ኔትወርክ በማስተሳሰር የተሻለ የትራፊክ ፍሰት እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችሉ ግንባታዎችንም ያካሂዳል፡፡

የአዲስ አበባ መንገዶች ባለሥልጣን የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ኢያሱ ሰለሞን፤ በከተማዋ የተለያዩ አካባቢዎች የበርካታ መንገዶች ግንባታ መካሄዱንና እየተካሄደ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ባለሥልጣኑ ከሚያካሂዳቸው የመንገድ መሠረተ ልማት ግንባታዎች መካከልም በዋና ዋና መንገዶች አደባባዮች ላይ የሚታየውን የትራፊክ መጨናነቅ ለመቀነስ እንዲያስችሉ የሚገነቡት የማሳለጫ መሻገሪያ ድልድዮች ግንባታ እንደሚገኙበት አስታውቀዋል፡፡

አቶ ኢያሱ ባለሥልጣኑ በቅርቡ ተመርቆ ሥራ የጀመረውን የቦሌ ሚካኤል ማሳለጫ ድልድይን ጨምሮ በከተማዋ የተለያዩ መንገዶች ላይ ወደ ስድስት የሚደርሱ የማሳለጫ ተሻጋሪ ድልድዮች ግንባታዎች እየተካሄዱ መሆናቸውን አመልክተዋል፡፡

በውስጠኛው ቀለበት መንገድ/ ከመገናኛ በቦሌ፣ ቃሊቲ፣ ለቡ መካኒሳ አየር ጤና፣ ኮልፌ አዲሱ ገበያ ያለው/ በዋና ዋና የመጋጠሚያ ቦታዎች ላይ የሚታየውን ከፍተኛ የትራፊክ መጨናነቅ ለመቀነስ በሶስት ቦታዎች ላይ የማሳለጫ ተሻጋሪ ድልድዮች ግንባታ እየተካሄደ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ እነዚህም የቦሌ ሚካኤል፣ የኢምፔሪያልና የለቡ ቀለበት የመንገድ መጋጠሚያ የትራፊክ ማሳለጫ ተሻጋሪ ድልድዮች ግንባታዎች መሆናቸውን ጠቁመዋል።

### የቦሌ ሚካኤል ማሳለጫ ተሻጋሪ ድልድይ

አቶ ኢያሱ እንዳሉት፤ የቦሌ ሚካኤል ተሻጋሪ ድልድይ ግንባታ ሙሉ ለሙሉ ተጠናቅቆና ተመርቆ ለአገልግሎት ክፍት ተደርጓል፡፡ ማሳለጫ ድልድዩ በአጠቃላይ ወደ 600 ሜትር ርዝመት እና 30 ሜትር የሚደርስ የጎን ስፋትም አለው፡፡ የግንባታው ሥራውም በአጠቃላይ በአካባቢው የተሰሩትን የመቃረቢያ መንገዶችን ጨምሮ ከ787 ሚሊየን ብር በላይ በጀት ተመድቦለት የተከናወነ ነው፡፡

ፕሮጀክቱ የተጀመረው በ2013 ሲሆን፣ በአካባቢው መነሳት የነበረባቸው በርካታ ቤቶች እና መሠረተ ልማቶች ነበሩበት፡፡ በሁለት አቅጣጫ /ከቦሌ ወደ ቡልቡላ/ ወደ መንገድ መጋጠሚያ የሚመጡ መንገዶችን ጨምሮ የግንባታ ሥራው ተከናውኗል፡፡

የዚህ ድልድይ ግንባታ ለየት የሚያደርገው ነገር እንዳለም ነው አቶ ኢያሱ ያስታወቁት፡፡ ግንባታው የተከናወነው በሀገር ውስጥ ተቋራጭ መሆኑ ለየት እንደሚያደርገው ገልጸዋል፡፡ ግንባታውን ያካሄደው የሀገር ውስጥ ተቋራጭም አሰር ኮንስትራክሽን ድርጅት እንደሚባል ጠቁመዋል፡፡

የዚህን ፕሮጀክት ጨምሮ የዘጠኝ ፕሮጀክቶች የግንባታ ወጪ የተሸፈነው በሀገር ውስጥ በጀት መሆኑን ጠቁመው፣ የግንባታ ሥራዎቹም ሙሉ ለሙሉ ከማማከር አንስቶ ዲዛይንና ግንባታው በኢትዮጵያውያን መካሄዱን አስታውቀዋል፡፡

### የለቡ ማሳለጫ ተሻጋሪ ድልድይ

ይህ ተሻጋሪ ድልድይ በአጠቃላይ አንድ ነጥብ አንድ ኪሎ ሜትር ርዝመትና አርባ ሜትር ስፋት እንዲኖረው ተደርጎ እየተገነባ ይገኛል፤ ለግንባታውም ከ634 ሚሊየን ብር በላይ በጀት የተመደለት ነው፤ ፕሮጀክቱ በቻይና ፈርስት ሀይዌይ ኢንጂነሪንግ ኩባንያ ሥራ ተቋራጭነት እየተከናወነ ሲሆን፣ የማማከር ሥራው ደግሞ ስታዲያ በተባለ ድርጅት ነው የሚከናወነው፤ ባለፈው ክረምት ወቅት የዚህ ተሻጋሪ ድልድይ አብዛኛዎቹ የግንባታ ሥራዎች ተጠናቀው ለትራፊክ ክፍት ተደርጎ አገልግሎት ሲሰጥ መቆየቱን አቶ ኢያሱ ጠቅሰው፣ አሁን የማጠናቀቂያ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

የኤምፔሪያል ማሳለጫ ተሻጋሪ ድልድይ

ይህ ተሻጋሪ ድልድይ አጠቃላይ 300 ሜትር ርዝመት እና 40 ሜትር የጎን ስፋት እንዲኖረው ተደርጎ የተገነባ ነው። መቃረቢያ መንገዶችን ጨምሮ ወደ አንድ ነጥብ ስምንት ኪሎ ሜትር የሚሆን ፕሮጀክት ነው፡፡ ግንባታውም በቻይና ፈርስት ሀይዌይ ኢንጂነሪግ ኩባንያ እየተካሄደ ይገኛል፡፡

የዚህ ፕሮጀክት ግንባታ ሥራም በአሁኑ ወቅት 91 በመቶው መጠናቀቁንም ኃላፊው አስታውቀው፣ ከ814 ሚሊየን ብር በላይ በጀት የተመደበለት መሆኑንም አመልክተዋል፡፡ የዚህን ፕሮጀክት /በሁሉም አቅጣጫ በቀኝ መታጠፊያ በኩል ባሉ የመንገድ መተላለፊያዎች ላይ/ አስፋልት የማልበስ ሥራ እየተከናወነ መሆኑን ጠቅሰው፣ የተቀሩትን የመንገዱን አካሎች አስፋልት የማልበስ ሥራ መጠናቀቁን አመልክተዋል፡፡



የቦሌ ሚካኤል ማሳለጫ ተሻጋሪ ድልድይ  በቅርቡ በከንቲባ አዳነች አቤቤ ተመርቆ ለትራፊክ ክፍት ተደርጓል

### የቃሊቲ ቱሉዲምቱ መንገድ ፕሮጀክቶች ድልድዮች

አቶ ኢያሱ በቃሊቲ ቱሉዲምቱ መንገድ ፕሮጀክት ላይም የተለያዩ ድልድዮች እየተገነቡ መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡ እሳቸው እንዳሉት፤ ከእነዚህም መካከል ቃሊቲ የቀለበት መንገድ መጋጠሚያ ላይ እየተገነባ ያለው ድልድይ አንዱ ሲሆን፣ ጥሩነሽ ቤጂንግ ሆስፒታል አካባቢም የሌላ ትልቅ ተሻጋሪ ድልድይ ግንባታ መካሄዱን ጠቅሰዋል፡፡ በተለምዶ ጋሪ ድልድይ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ላይም እንዲሁ 50 ሜትር ርዝመትና 20 ሜትር ስፋት ያለው ድልድይ ግንባታ እየተከናወነ ይገኛል፡፡

የቃሊቲ ቱሉ ዲምቱ እንዲሁም የቃሊቲ አደባባይ ቡልቡላ ቂሊንጦ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች ግንባታዎቹ ይከናወኑ የነበሩት ከቻይና ኤግዚም ባንክ በተገኘ የፋይናንስ ድጋፍ እንደነበር ኃላፊው አስታውሰው፣ ፕሮጀክቶቹ በገጠማቸው የፋይናንስ አቅርቦትና የወሰን ማስከበር ችግር ምክንያት መጓተታቸውን ገልጸዋል፡፡

የፕሮጀክቶቹ ወሰን ማስከበር እንዲሁም ከፋይናንስ አቅርቦት ጋር ተያይዞ የነበረው ችግር፣ የከተማ አስተዳደሩ በብድር ተወስዶ እንዲሰራ ባስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት በመፈታቱ ግንባታቸው በአሁኑ ወቅት በፍጥነት እየተካሄደ እንደሚገኝ አስታውቀዋል፡፡

በቀጣይም ከተማ አስተዳደሩ ሌሎች ማሳለጫዎችን እንደ ፋይናንስ አቅርቦቱ እና የማሳለጫዎቹ ተገቢነት እያየ እንደሚገነባም ኃላፊው ጠቁመዋል፡፡ በአየር ጤና ሌላ የማሳለጫ ተሻጋሪ ድልድይ ግንባታ እንደሚካሄድም አመልክተዋል፡፡ የአየር ጤና አካባቢ ከፍተኛ የመንገድ መጨናነቅ እንደሚታይበት ጠቅሰው፣ የዚህ ፕሮጀክት ግንባታ ከአየር ጤና አደባባይ አንስቶ እስከ ወለቴ እንደሚዘልቅ አስታውቀዋል፡፡ የግንባታው ውል ባለፈው ዓመት መፈጸሙንም አስታውሰው፣ ወደ ግንባታ ሥራው ለመግባት ግን የወሰን ማስከበር ሥራዎች ያልተጠናቀቁበት ሁኔታ እንዳለ አመልክተዋል፡፡ ይህ እንደተጠናቀቀ ወደ ግንባታ እንደሚገባም አስታውቀዋል፡፡

በ2016 የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ በግንባታ ላይ የሚገኙ ፕሮጀክቶችን አጠናቆ ለአገልግሎት ማብቃት፣ አንዱና ቀዳሚ የትኩረት አቅጣጫው መሆኑን ኃላፊው ጠቅሰው፣ ሁለተኛው የትኩረት አቅጣጫ ባለፈው ዓመት ውል ተገብቶባቸው ወደ ግንባታ ያልገቡ ፕሮክቶችን የወሰን ማስከበር ሥራዎችን በማጠናቀቅ ወደ ግንባታ ማስገባት መሆኑን ተናግረዋል፡፡

‹‹ከመሀል ከተማ ውጭ ባሉ አካባቢዎች የሚገነቡ መንገዶች የትራፊክ ማሳለጫ የሚጠይቁ ከሆነ አካተን እንገነባለን›› ያሉት ኃላፊው፣ ‹‹በቃሊቲ ቱሉ ዲምቱ መንገድ ላይ ሶስት ማሳለጫዎች የተገነቡትም ለዚሁ ነው›› ብለዋል፡፡

የከተማዋ የመንገድ ኔትወርክ ደህንነት የተጠበቀና ከትራፊክ መጨናነቅ ውጭ እንዲሆን ለማድረግ በርካታ ሥራዎች መሠራት እንዳለባቸው ባለሥልጣኑ እንደሚገነዘብ ጠቅሰው፣ ሁሉንም ነገሮች ለማድረግ ደግሞ ፋይናንስ ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

‹‹የከተማ አስተዳደሩ ከፍተኛ በጀት ከሚመድብባቸው ዘርፎች መካከል አንዱ የመንገድ ዘርፉ ነው፤ የከተማዋ በጀት በየዓመቱ ቢያድግም የኮንስትራክሽን ዋጋውም በዚያው ልክ እየጨመረ ነው፤ ያለው ፍላጎት ከፍተኛ ቢሆንም፣ መሥራት የሚቻለው ባለው አቅም በመሆኑ ቅድሚያ ለሚሰጠው ቅድሚያ በመስጠት ግንባታዎች እየተካሄዱ ይገኛሉ ሲሉ አብራርተዋል፡፡

### የማሳለጫ ተሻጋሪ ድልድዮቹ ትሩፋቶች

የቃሊቲ ቱሊዲምቱ መንገድ የከተማ ዋና የሀገሪቱ የወጭ ገቢ ንግድ ኮሪደር መሆኑን የጠቀሱት ኃላፊው፣ ማህበራዊ ፋይዳውም ከፍተኛ መሆኑን ነው ያስታወቁት። በዚህ መንገድ ላይ የተካሄዱ የማሳለጫ ድልድይ ግንባታዎች ፋይዳ ከፍተኛ እንደሆነም ተናግረዋል፡፡

ቀደም ሲል ከከተማ ውጪ በሚል እሳቤ የተገነባውና አሁን ከተማ ውስጥ የገባው የከተማዋ የውስጥ ቀለበት መንገድ (37 ሜትር ርዝመት ያለው መንገድ) ትልቅ የትራፊክ ፍሰት የሚታይበት መሆኑን ጠቅሰው፣ ለአጠቃላይ ለከተማዋ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ካላቸው የመንገድ መሠረተ ልማቶች መካከል እንደሚጠቀስም ተናግረዋል፡፡

በዚህ መንገድ ላይ ማሳለጫ እየተገነባባቸው ባሉ ሥፍራዎች ላይ ቀደም ሲል አደባባዮች እንደነበሩ አስታውሰው፣ ከዚያም ከፍተኛ የትራፊክ መጨናነቅ ሲፈጠር አደባባዮቹን በማፍረስ በትራፊክ መብራት አገልግሎት እንዲሰጡ መደረጉን ገልጸዋል፡፡ እነዚህ ጥረቶች በወቅቱ የነበረውን ችግር በተወሰነ መልኩ ማቃለል መቻሉን አመልክተው፣ ሙሉ ለሙሉ ችግሩን ባለመፍታታቸው በትራፊክ ማሳለጫ ተሻጋሪ ድልድይ እንዲቀየሩ ተደርጓል ብለዋል፡፡

ትላልቅ የመንገድና የማሳለጫ ድልድዮች ግንባታዎችን ሲያካሂዱ ከቆዩ የውጭ ተቋራጮች ስለተገኘ እውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር ጥያቄ የቀረበላቸው አቶ ኢያሱ በሰጡት ምላሽ አንድ ተቋራጭ በማሳለጫ ግንባታ ላይ ውጤታማ ሆኖ መገኘቱን አስታውቀዋል፡፡ በውስጠኛው ቀለበት መንገድ ላይ ከሚገነቡት ድልድዮች የቦሌ ሚካኤሉ የተገነባው በሀገር ውስጥ ተቋራጩ አሰር ኮንስትራክሽን መሆኑን ጠቅሰው፣ ኢትዮጵያውያን ተቋራጮች ትልቅ የመፈጸም አቅም እያዳበሩ ስለመምጣታቸው የዚህ ኩባንያ አፈጻጸም ያመለክታል ብለዋል፡፡

እስከ አሁን የትላልቅ ማሳለጫ ድልድዮች ግንባታ በሀገር ውስጥ ተቋራጮ የሚደፈሩ አልነበሩም ያሉት ኃላፊው፣ አሁን ግን ይህ ሁኔታ መቀየሩን ጠቅሰዋል። በሀገር ውስጥ ተቋራጭ የተሰራው የቦሌ ሚካኤል ማሳለጫ ድልድይ በሌሎች አካባቢዎች ከተሰሩት ማሳለጫዎች ጋር ሊወዳደር የሚችል መሆኑን ገልጸዋል። አሰር ኮንስትራክሽን በዚህ ደረጃ መገኘቱ የሀገር ውስጥ ተቋራጮች አቅም እየተገነባ ትላልቅ ፕሮጀክቶችን የሚሰሩ ተቋራጮች እየተፈጠሩ መምጣታቸውን እንደሚያመለክት ተናግረዋል፡፡ የፕሮጀክቱ አፈጻጸም ከቻይና ኩባንያዎች ብዙ ልምድ የተወሰደበትና በዚህም ተገልጋዩ ህብረተሰብ እየተደነቀ ያለበት ሁኔታ እንዳለ መረዳት የቻለበት ሁኔታ ተፈጥሯል ብለዋል፡፡

### የመንገድ መሰረተ ልማቱ ተግዳሮቶችና መፍትሔዎቻቸው

ከመንገድ ዘርፍ ጋር በተያያዘ ለሚታየው የፕሮጀክት መጓተት ትልቁ ምክንያት እየሆነ ያለው ከወሰን ማስከበር ጋር ተያይዞ ያለው ችግር መሆኑን አቶ ኢያሱ አስታውቀዋል። የወሰን ማስከበር ችግር በፍጥነት ከተፈታ ሥራዎችን በፍጥነት ማከናወን እንደሚቻል፤ በዚያው ልክም ችግሩ ካልተፈታ ሥራዎቹ ምን ያህል ሊጓተቱ እንደሚችሉ ሁለት ፕሮጀክቶችን በማሳያነት ጠቅሰው አብራርተዋል፡፡

ኃላፊው ለዚህ በአብነት ያነሱት አንዱ ፕሮጀክት የአሌክሳንደር ፑሽኪን ጎፋ ማዞሪያ ጎተራ መንገድን ነው፡፡ ይህ ፕሮጀክት የተጀመረው በ2012 መስከረም ሲሆን፣ ግንባታው ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ከጀመረ ከአንድ ዓመት በላይ ሆኖታል፡፡ ይህ ፕሮጀክት ትላልቅ ስትራክቸሮችን አካቶ የተገነባ፣ ሶስት መቶ ሃያ ሜትር ዋሻ ያለው፣ ከላይ መተላለፊያ ድልድይ የተካተተበት ነው፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ የአውቶብስ ተራ መሳለሚያ 18 ማዞሪያ መንገድ ፕሮጀክት ከዚሁ ፕሮጀክት ጋር አብሮ ነው የተጀመረው፡፡ ነገር ግን የወሰን ማስከበር ሥራው ሲጓተት በመቆየቱ በተፈለገው ደረጃ ግንባታውን ማከናወን አልተቻለም፡፡ ለፕሮጀክቶች መጓተት ትልቁ ፈተና የሚሆነው የወሰን ማስከበር ችግር ለመሆኑ ይህ አንድ ማሳያ ነው፡፡

ከዚህ ጎን ለጎን አንዳንዴ ፕሮጀክቶች የፋይናንስ አቅርቦት ችግር ይገጥማቸዋል፤ ለእዚህም የቃሊቲ አደባባይ ቱሉ ዲምቱ መንገድ ፕሮጀክት በአብነት ተጠቅሷል። ከሥራ ተቋራጮች የመፈጸም አቅም ውስንነት ጋር ተያይዞ የሚገጥም ችግርም አለ፡፡ ለእዚህም ማሳያ ተደርጎ የሚወሰደው በቅርቡ ተመርቆ ለትራፊክ ክፍት የተደረገው የአራራት ኮተቤ ካራ መንገድ ፕሮጀክት ነው፡፡

‹‹በመንገድ ግንባታ ወቅት ትልቅ ፈተና እየሆነብን የመጣው የወሰን ማስከበር ሥራ አለመጠናቀቅ ነው›› የሚሉት አቶ ኢያሱ፣ ብዙውን ጊዜ የወሰን ማስከበር ሥራ ሳይጠናቀቅ ለምን ወደ ሥራ አትገቡም የሚሉ ጥያቄዎች እንደሚቀርቡም ይጠቅሳሉ፡፡ ‹‹እኛ ደግሞ እንኳንስ ወሰን የማስከበር ሥራ ያልተከናወነላቸው ፕሮጀክቶች፣ ክፍት በሆኑ ቦታዎች ላይ የጀመርናቸው ፕሮጀክቶች ቀሪ የወሰን ማስከበር ሥራዎችን ለማከናወን በግንባታ ሥራ ላይ ትልቅ ፈተና እየገጠመን ይገኛል›› ብለዋል፡፡

የወሰን ማስከበር ሥራው ሙሉ ለሙሉ ካልተጠናቀቀ ፕሮጀክቶቹ እየተገፉ ለረጅም ጊዜ ሳይጀመሩ የሚቆዩባቸው ሁኔታዎች እንደሚገጥሙ ገልጸዋል፡፡ ‹‹ነገር ግን በተቻለ መጠን ክፍት በሆኑ ቦታዎች ላይ ጀምረን ወሰን ማስከበር ሥራውን ደግሞ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር በመሥራት ግንባታዎቹን በፍጥነት ለማከናወን ጥረት እያደረግን ነው፤ በዚህም የተሻለ ስኬት አለ ተብሎ ይወሰዳል›› ብለዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ጥቅምት ሃያ አራትን ስናስብ !

ችግሮችን በውይይትና በድርድር መፍታት በብዙ መልክ አትራፊ መሆን የሚያስችል ሰብዓዊ እሴት ነው። በተለይም በግጭት አዙሪት ውስጥ እየኖሩ ላሉ፣ በዚህም በየዘመኑ ያልተገቡ ዋጋዎችን ለመክፈል ለሚገደዱ የኛ ብጤ ሕዝቦች ችግሮችን በውይይትና በድርድር መፍታት እንደ ሀገር ያላቸውን ሕልውና አስጠብቆ የመሄድ ያህል ትርጉም ያለው እውነታ ነው።

በርግጥ በየትኛውም ማኅበረሰብ ውስጥ የልዩነት ምንጭ የሚሆኑ አስተሳሰቦች መፈጠራቸው ተፈጥሯዊ ነው። እነዚህ የሀሳብ ልዩነቶች አንድን ማኅበረሰብ እንደ ማኅበረሰብ ከአንድ የታሪክ ምዕራፍ /የአስተሳሰብ ዓውድ/ ወደ ቀጣይ ምዕራፍ ማሻገር የሚያስችሉ ማኅበረሰባዊ አቅሞች ናቸው። እነዚህ አቅሞች ደግሞ የማኅበረሰቡ ፀጋዎች ተደርገውም ይወሰዳሉ።

እነዚህን ልዩነቶች አቻችሎ ማስተናገድ የሚያስችል የአስተሳሰብ ማዕቀፍ በተዘረጋበት ማኅበረሰብ ውስጥ፣ እነዚህ ልዩነቶች ማኅበረሰቡን ከትናንት በመውጣት ዛሬን በራሱ መዋጀት የሚያስችል አቅም በመፍጠር፣ ነገን የበለጠ ብሩህና በተስፋ የደመቀ በማድረግ ሂደት ውስጥ ወሳኝ ጉልበት በመሆን ያገለግላሉ። የለውጥ እና የመለወጥ አስተሳሰብ መሠረትም ይሆናሉ ።

እነዚህን የአስተሳሰብ ልዩነቶች በኃይል/በጉልበት ለመደፍጠጥ እና ለማስቆም የሚደረጉ ጥረቶች፤ ማኅበረሰብ ከትናንቶቹ ጋር አብሮ እንዲኖር የመፍረድ ያህል ነው። ውጤቱም ማኅበረሰብ ከትናንት ችግሮቹ፣ ችግሮቹ ከሚወልዱት ሁለንተናዊ መጎዳቶች ጋር አብሮ እንዲኖር የማስገደድ ያህል የከፋ ወንጀል ነው። በማኅበረሰብ ዛሬና ነገዎች ላይ መፍረድም ነው።

ይህንን የከፋ ወንጀል ለመከላከል ሆነ ለማስቆም ከሁሉም በላይ ችግሮችን በውይይት የመፍታት ባሕልን ማበልጸግ ወሳኝ ነው። በተለይም በለውጥ ማግስት የሚፈጠሩ ልዩነቶች የለውጡ አካል ብቻ ሳይሆኑ፤ ለለውጡ ማግስት ተግባራት ስኬትም አቅም መሆናቸውን ተገንዝቦ ልዩነቶችን በሆደ ሰፊነት ማየት፣ ወደ ግጭት የሚወስዱ መንገዶችን መዝጋት የግድ የሚያስብል ነው።

እኛ ኢትዮጵያውያን ለመለወጥ ካለን ከፍ ያለ መሻት አንጻር በተለያዩ ወቅቶች ሀገራዊ ለውጥ እውን ማድረግ የሚያስችሉ ንቅናቄዎችን መፍጠር ችለናል። በነዚህ የለውጥ ንቅናቄዎቹ የየዘመኑ ትውልድ ብዙ ተስፋዎችን ሰንቆ ስለተስፋዎቹ እራሱን መስዋዕት ማድረግ በሚያስችል ቁርጠኝት ተሰልፏል።

ይህም ሆኖ ግን ልዩነቶችን በሰላማዊ መንገድ በውይይት መፍታት የሚያስችል ሀገራዊ/ማኅበረሰባዊ አቅም ባለመፍጠሩ ምክንያት በተለያዩ ወቅቶች ከተከናወኑ ለውጦች የተገኘው የተጠበቀው/ተስፋ የተደረገው ሳይሆን ያልተጠበቀው ሆኗል። ይህም በየወቅቱ የፈጠረው ሀገራዊ ስብራት ከፍ ያለ ነው።

ከነዚህ የትናንት የለውጥ ታሪክ ስብራቶቻችን መማር ባለመቻላችንም በዚህም ዘመን እንደ ሕዝብ የተፈጠረው የለውጥ መነቃቃት በተነሳበት ልክ ረጅም ርቀት መጓዝ የሚችልበትን ፍጥረታዊ ጉዞውን አደነቃቅፈናል፤ ከዛም ባለፈ በሀገሪቱ የቀደሙ የታሪክ ምዕራፎች ባልታየ መልኩ የሀገርን ሕልውና/እንደ ሀገር የመቀጠል ተስፋ አደጋ ውስጥ በሚከት ያልተገባ መንገድ ላይ ተገኝተናል።

ማንንም አሸናፊና ተሸናፊ በማያደርግ፤ ከሁሉም በላይ ሀገርና ሕዝብን ማቅ ያስለበሰ ትርክት ለመጻፍ የተገደድንበት የሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ግጭት እንዳይከሰት ብዙ የሰላም እጆች ከፍ ብለው ቢውለበለቡም፤ ሰላም የአንድ አካል ፍላጎት ብቻ ባለመሆኑ ሊሳካ አልቻለም።

የዛሬውን ጥቅምት 24 ስናስብም፤ ከሁሉም በላይ የሰላምን ዋጋ በማጤን፤ ችግሮችን በድርድርና በውይይት የመፍታትን ሁለንተናዊ ጥቅም በማሰላሰል፤ ተመሳሳይ ችግር በቀጣይ ትውልዶች እንዳይደገም መሠረታዊ የአስተሳሰብ ለውጥ ለመፍጠር ከራሳችን ጋር ቃል በመግባት ሊሆን ያስፈልጋል።

አለመግባባቶችን በኃይል ለመፍታት ብቻ ሳይሆን፤ አለመግባባቶችን በሀገርና በሕዝብ ስም በኃይል ለመፍታት የሚንቀሳቀሱ ግለሰቦች እና ቡድኖችን በቃችሁ የሚል የጋራ አስተሳሰብ በመገንባት፤ ሰላማችንን አስተማማኝ በሆነ መንገድ መጠበቅ የሚያስችል ሀገራዊ ማንነት በመፍጠርና ለመጪው ትውልድ በጠንካራ መሠረት ላይ በማዋቀር ጭምር ሊሆን ይገባል።


**አዲስ ዘመን**

ኢፕድ ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ ዓምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ከኑሮ ውድነት ጫና ለመላቀቅ ወደራስ መመልከት!!

**አስናቀ ፀጋዬ**

በአሁኑ ግዜ ኑሮ በዜጎች ላይ እያደረሰ ያለው ሁለንተናዊ ጫና ይህ ነው ተብሎ ሊገለፅ አይችልም። የኑሮ ውድነቱ ጣራ ነክቷል፡፡ በኑሮ ውድነት ያልተፈተነና ያልተማረረ የኅብረተሰብ ክፍል የለም። ዋጋ ያልጨመረ የምግብና የሸቀጣቀጥ እቃ የለም ለማለት አያስደፍርም፡፡ ኅብረተሰቡ ከነገ ዛሬ የኑሮ ውድነቱ ይቀነሳል ብሎ ተስፋ ቢያሳድርም እስካሁን ድረስ ጠብ ያለ ነገር የለም፡፡ በዚህም የኑሮ ውድነቱ ይበልጥ እያሻቀበ መጥቷል፡፡ በመንግሥም በኩል የኑሮ ውድነቱን ለመቀነስ እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች ቢኖሩም ገና ብዙ መሥራትን ይጠይቃል፡፡

በርግጥ አሁን በኢትዮጵያ እየታየ ያለው የኑሮ ውድነት በዓለም አቀፍ ደረጃ እየታየ ያለው የነዳጅና ሌሎች ሸቀጣሸቀጦች መናር ነፀብራቅ ነው፡፡ በዚህም ኢትዮጵያ ብቻ ሳትሆን ሌሎችም ሀገራት በዚሁ የኑሮ ውድነት ጦስ እየተሰቃዩ ነው፡፡ ዜጎቻቸውም ኑሮን መቋቋም ተስኗቸው በከፋ ችግር ውስጥ ቀናትን አሸንፎ ለመውጣት በብርቱ እየታገሉ ነው፡፡

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፣ በኢትዮጵያ የዋጋ ንረት አሁንም አስደንጋጭ የሚባል ደረጃ ላይ ነው፤ ይህም ሆኖ ግን ከኢትዮጵያ የባሱ በርካታ ሀገራት አሉ፡፡ ለምሳሌ በቱርክ የዋጋ ንረቱ 70 ከመቶ ደርሷል። በአርጀንቲና 51 በመቶ ተጠግቷል፡፡ በሲሪላንካ ደግሞ 30 ከመቶ ሆኗል፡፡

እንደውም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አንድ አካል የሆነው የዓለም ሠራተኞች ድርጅት/ILO/ እንደሚለው ከሆነ፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ የዋጋ ንረት ካለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር በእጥፍ ጨምሯል። ባለፈው መጋቢት ወር የዋጋ ንረቱ 3 ነጥብ 7 ከመቶ ብቻ እንደነበር፣ በዚህ ዓመት በመጋቢት ወር ወደ 9 ነጥብ 2 ከመቶ ማሻቀቡን ተናግሯል፡፡ ይህም ማለት የማንኛውም ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ሸቀጦች እንዲሁም የአገልግሎቶች ዋጋ በአስደንጋጭ ሁኔታ ማሻቀቡን ይጠቁማል፡፡

ዓለም ከሚገመተው በላይ በንግድ ሰንሰለት የተሳሰረ ነው፡፡ ለምሳሌ የኮቪድ ወረርሽኝንና ምጣኔ ሀብትን ምን ሊያገናኛቸው ይችላል? ተብሎ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ መልሱ በሚገባ ይገናኛሉ ነው። ምክንያቱም በንግድ ዓለም ሁሉ ነገር የተሳሰረ በመሆኑ ነው፡፡ እንዴት ከተባለ ደግሞ ለምሳሌ ኮቪድ በግዜው የእንቅስቃሴ ገደብ አስከትሏል፡፡ ላብ አደር ፋብሪካ አልሔደም፡፡ ምርት አልተመረተም፡፡ በዚህም ፋብሪካዎች ምርት ቀንሰዋል፡፡ ሠራተኛው ሥራውን አጥቷል፡፡ ሸማችም ምርት አልደርስ ብሎታል፡፡

በኮቪድ ምክንያት እዳቸውን በቱሪዝም ገቢ የሚከፍሉ ሀገራት ጭንቅ ውስጥ ገብተዋል፡፡ አምራች ሀገራት በበቂ ሁኔታ ማምረት አቁመዋል፡፡ ይህም የዋጋ ንረትን አስከትሏል፤ ይህንኑ ተከትሎ የኑሮ ውድነት ተከስቷል፡፡ ከአንድ ዓመት ከስድስት ወር ገደማ በፊት የተፈጠረው የሩሲያ ዩክሬን ጦርነትም ሁለቱ የዓለማችን ቁጥር አንድ ስንዴ አምራቾች ምርት መላክ በማቆማቸው ዓለም አቀፍ የስንዴ ምርት እጥረት ተከስቷል፡፡ በዚህም በስንዴ ምርት ላይ ከፍተኛ የዋጋ ንረት ታይቷል፡፡ ይህ የዋጋ ንረት ደግሞ በኑሮ ውድነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡

በየዘመኑ የኑሮ ውድነት ይከሰታል፡፡ የዘንድሮውስ የከፋ ነው ሲባል ሌላ የከፋ ይመጣል፡፡ ነገሩ ከሚገመተው በላይ ውስብስብ በመሆኑ ሀገራትም ይህንን የሚቋቋሙበት ሁነኛ መላ የላቸውም፡፡ ለዚህም ነው የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች ቀጥተኛ መልስ መስጠት የሚከብዳቸው፡፡ ሆኖም ግን ከችግሩ መውጣት የሚያስችለው አንዱ መንገድ ምርትን መጨመር ነው፡፡ እርግጥ ነው ደሃ ሀገራት መርፌም ጭምር ከውጪ ሀገራት ስለሚያስገቡ ከዚህ የኑሮ ውድነት ለመውጣት ፍዳቸውን ማየታቸው አይቀሬ ነው፡፡

አንዳንድ ሀገራት አሁን እየታየ ያለውን የኑሮ ውድነት ጫና ለመቀነስ የየራሳቸውን ስትራቴጂ ቀይሰው እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ፡፡ ለአብነትም የሀገር ውስጥ ምርታቸውን በስፋት በማሳደግና ከውጭ ሀገር የሚያስገቧቸውን ምርቶች በመቀነስ የኑሮ ውድነቱን ጫና በመጠኑም ቢሆን መቀነስ ችለዋል። ሌሎቹ ደግሞ የሀገር ውስጥ ምርታቸውን በማሳደግ ያጋጠማቸውን የኑሮ ውድነት ጫናን ከመቋቋም አልፈው ለሌላም ሀገር ተርፈዋል፡፡ ያ ማለት ምርቶቻውን ወደውጪ ሀገራት በመላክ የውጪ ምንዛሪ ጭምር እስከማግኘት ደርሰዋል፡፡

ኢትዮጵያም ብትሆን የኑሮ ውድነቱን ለመቀነስ እያደረገቻቸው ካሉ ጥረቶች ውስጥ አንዱ ይሄው የሀገር ውስጥ ምርት መጠንን ማሳደግና ለዜጎቿ በስፋት ማቅረብ ነው፡፡ ለዚህም አንዱ ማሳያው በተለይ ስንዴን በስፋት በማምረት ለዜጎች ማቅረብና አለፍ ሲል ደግሞ ለውጪ ገበያ በማቅረብ የውጪ ምንዛሪ ማግኘት ነው፡፡ ይህ ስንዴን በስፋት የማምረት ሥራ ካለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ በስፋት ተሠርቶበት ከፍተኛ ምርት ማግኘት ተችሏል። እንደውም ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ስንዴን ወደ ኬንያ ልካ የውጪ ምንዛሪ እስከማግኘት ደርሳለች፡፡ አሁን ደግሞ ለዜጎቿ ስንዴን የማዳረስ ሥራ በስፋት ለመሥራት እንቅስቃሴ እያደረገች ትገኛለች፡፡

ይህ በሀገር ውስጥ የሚመረተውን የስንዴ ምርት በማሳደግ የዜጎችን የኑሮ ጫና የመቀነስና የምግብ ዋስትናን የማረጋገጥ ስልት እጅግ የሚያበረታታ ነው። እንደውም ከበቂ በላይ ስንዴ በማምረትና ወደውጪ ሀገራትም ጭምር በመላክ የውጪ ምንዛሪ ለማግኘትና አሁን የሚታየውን የውጪ ምንዛሪ ክፍተት ለመሙላት በእጅጉ ያግዛል፡፡ ከዛ ባለፈም የሚገኘውን የውጪ ምንዛሪ ለሌሎች አንገብጋቢና ለኑሮ ውድነት ጫና ማርከሻ ለማዋል ያግዛል፡፡

በሀገር ውስጥ ስንዴን አምርቶ አሁን የሚታየውን የምግብ እጥረት ችግር ለመቅረፍ የሚደረገው ጥረት ታዲያ ሌሎች ምርቶችንም በማምረት ሊደገም ይገባል፡፡ በተለይ ወሳኝ የሆኑ እንደ ስኳር፣ ዘይት፣ ዱቄትና ሌሎችንም አላቂ የምግብ ሸቀጦችን በሀገር ውስጥ በስፋት ማምረት ሊለመድ ይገባል፡፡ ለዚህ ደግሞ መንግሥት በስንዴ ልማት ላይ የጀመረውን እንቅስቃሴ በነዚህ ሸቀጣሸቀጥ ምርቶች ላይ ማስቀጠል ይኖርበታል፡፡

ምንም እንኳን የኑሮ ወድነቱ ከአቅም በላይ ቢሆንም አንዳንድ ግዜ ወደራስ ተመልክቶ ለችግሩ መፍትሔ ማበጀት አንድ ነገር ነው፡፡ ኑሮ እያደረሰ ያለውን ጫና አምኖና ተቀብሎ መደቆስ ሕልውናን ማሳጣር ነው፡፡ እናም ለኑሮ ውድነት እጅ ሳይሰጡ ለመኖር በዜጎችም በኩል ትግል ማድረግ ይገባል፡፡

ስለዚህ በፍላጎት መናር የሚከሰተው የዋጋ ንረት የምርት እጥረትን ይፈጥራልና ነጋዴዎች የፍላጎትን መጨመር በበቂ ሁኔታ ለማስተናገድ ሲሳናቸው ዋጋ ይጨምራሉ፡፡ ይህ ደግሞ የኑሮ ውድነት እንዲከሰት ምክንያት ይሆናል፡፡ ከዚህ አንፃር መንግሥት በዚህ በኩል ለኑሮ ውድነት አስተዋፅዖ የሚያደርጉና በአንዳንድ ሕገወጥ ነጋዴዎች የሚደረጉ አላስፈላጊ የዋጋ ጭማሪዎችን በመከታተል እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

የነዳጅ ዋጋ መጨመር የዋጋ ንረትን በማስከተል ረገድ ከሚጠቀሱ ዋንኛ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ነው። ነጋዴዎች ዋጋ ቢጨምሩም ተገልጋይ ወይም ሸማች በቀላሉ ስለማይሸሽ አያሳስባቸውም፡፡ በተደጋጋሚ ዋጋ ይጨምራሉ፡፡ ይህን ችግር በተወሰነ መልኩ ለመቋቋም ሸማቹ የነዳጅ ዋጋን ታከው ከሚጨምሩ ምርቶች ለመራቅ የራሱን አማራጭ መውሰድ ይኖርበታል፡፡ ለምሳሌ ትራንስፖርት ዋጋ ከጨመረ የሕዝብ ትራንስፖርቶችን መጠቀም አልያም ደግሞ ግማሹን መንገድ በእግር በመሄድ ጤንነቱን ጠብቆ ገንዘቡን ማዳን ይችላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ለኑሮ እጅግ አስፈላጊ የሆኑ ምርቶችን ብቻ በመሸመት ከዚህ የኑሮ ውድነት ማምለጥ ይቻላል፡፡

# እንዲህም ይኖራል

**ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተሳምዶ ከመኖር ይልቅ ስመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውሳችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።**

## ያሳለፈ ትናንት ...

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

### እናትና ልጅ...

ብቸኛዋ ሴት ስለ መኖር ያልሆኑት የለም። ለዓመታት ትንሹን ልጅ ይዘው ተንከራተዋል። ያለ አባት የሚያድገው ሕጻን ከእናቱ ሌላ ዘመድ አያውቅም፡፡ በእሳቸው ጉያ በላባቸው ወዝ ያድራል፡፡ በሚከፍሉት የጉልበት ዋጋ እንደነገሩ ይኖራል፡፡ ለእሱ ሕይወትና ተስፋው፣ ዛሬና ትናንቱ ከእናቱ ተቆራኝቷል፡፡ ትንሹ ልጅ ዓባይነህ ሀብታሙ ፡፡

የዓባይነህ እናት ብርቱ ሴት ናቸው፡፡ ልጃቸውን ለማሳደግ በየቤቱ እንጀራ ይጋግራሉ፡፡ የሚታጠበው፣ የሚቆላ፣ የሚከካው፣ ከእሳቸው እጅ አያልፍም።፡ ለድካማቸው የሚያገኙት ምንዳ ደግሞ እዚህ ግባ አይሉትም፡፡ እንዲያም ሆኖ አዝነው፣ ተማረው አያውቁም፡፡ የያዙትን ይዘው ለልጃቸው ሆድ ይደርሳሉ።

ቤት ሲገቡ የጎን ማረፊያው አይመችም፡፡ ሁሌም የደባል ቤታቸው እንደሾህ ነው፡፡ እፎይታ ይሉት የለውም፡፡ በምቾት አልባ ዕንቅልፍ ሌቱ ይነጋል፡፡ ቀኑ በተለምዶ ድካም ያልፋል፡፡

### ትንሹ ዓባይነህ ...

ዓባይነህ የእናቱ ልጅ ነው፡፡ ችግር መከራ፣ ብርቁ አይደለም፡፡ ሁሌም የእሳቸው ሕይወት ሕይወቱ ነው፡፡ ፈተናቸውን ይጋራል፣ ኑሯቸውን ይካፈላል። የእናትና ልጅ የእንክርት ኑሮ አላበቃም፡፡ ስለመኖር በደባልነት የሚከፍሉት ዋጋ ቀጥሏል፡፡

ከቀናት በአንዱ የዓባይነህ እናት ከሰዎች መከሩ። ምክሩ ልባቸው ሲገባ አልዘገየም፡፡ በቅርብ የሚያውቋቸው አንዲት ሴት ዓባይነህን ይዘው ከቤታቸው እንዲኖሩ ፈቅደዋል፡፡ ይህ የምሥራች ለቤት አልባዋ ሴት ቀላል አልሆነም፡፡ እስከዛሬ በደባል ቤት ኑሮ ተንከራተዋል፡፡ ያላለፈ ድህነት ተጭኖ ፈትኗቸዋል፡፡

ዓባይነህ ከእናቱ ጋር ወደ ተባለው ቤት አመራ። ግቢው በቆሻሻ ክምር የተከበበ ነው፡፡ እነሱ ከወለል አንጥፈው እንዲተኙ ተፈቅዷል፡፡ በቤቱ መሐል የሚያልፈው የመፀዳጃ ፍሳሽ የእነ ዓባይነህን መኝታ ጎብኝቶት ያልፋል፡፡

ዕድሜያቸው የገፋው ሴት ራሳቸውን መግዛት ካቆሙ ሰንብተዋል፡፡ ካልጋ የዋሉት ባላቸው ሕመማቸው ከፍቷል፡፡ ሁለቱም የሌሎች ድጋፍ ያሻቸዋል፡፡ በዚህ እውነታ እናትና ልጅ ከእነሱ ጋር ኑሮን ጀመሩ፡፡ ቢከብድም ይህ እንዲሆን ግድ ሆነ፡፡

አዛውንቷ ውሎ አድሮ ባሕሪያቸው ተቀየረ። የዕድሜያቸው መግፋት እንደልጅ ያደርጋቸው ያዘ። ‹‹ካረጁ አይበጁ››ን የተረቱ በርካቶች በሚያዩት ድርጊት ሸሽተው ራቁ፡፡ እነ ሀብታሙ እሳቸውን ሊተዉ አልቻሉም፡፡ ሴትዬዋን ቀርበው መጠበቅ መንከባከብ ያዙ፡፡ ይህ አጋጣሚ የእናትና ልጅን ጤና ፈተነ፡፡ ሁለቱም በጉንፋን ተሰቃዩ፣ በደረቅ ሳል ተንተከተኩ፡፡

አሁንም የሰው ቤት ኑሮ አልሆነም፡፡ ስቃይ የሞላው ሕይወት ፈተና በዛበት፡፡ በዘመኑ ለቀበሌ ነዋሪዎች ኩፖን ይሰጥ ነበር፡፡ እነሀብታሙ የሌሎችን ዕድል ተጠቅመው ለቀበሌው ማመልከቻ አስገቡ፡፡ ፍላጎታቸው ቤት እንዲያገኙ ነበር፡፡

የታሰበው አልሆነም፡፡ ያለመፍትሔ የሰው ቤት እንክርቱ ቀጠለ፡፡ የሀብታሙ እናት ተስፋ ቆረጡ። እያደር ኑሮ ይመር ይከብዳቸው ጀመር። ይህ እውነት ልባቸውን ለመንገድ አነሳሳ፡፡ አንድ ቀን በድንገት ብድግ ብለው ሀገራቸው ጎጃም ገቡ፡፡

ሀብታሙ እናቱ ከሄዱ በኋላ የብቸኝነት ኑሮን ተጋፈጠ፡፡ አሁን ከጎኑ ማንም የለም፡፡ ዘመድ ወዳጅ ይሉትን አያውቀው ልጅ በግራ መጋባት ቀናትን ቆጠረ። ሰፈርተኛው እናት ልጃቸውን ጥለው ስለመጥፋታቸው እያነሳ አወራ፡፡ እንዲህ መሆኑ ለትንሹ ልጅ የፈየደው የለም፡፡

ሀብታሙ በችግር አለንጋ ተገረፈ፡፡ የእናት እጅ የለመደው ሆድ መራብ መጠማቱ አልቀረም፡፡ የጎረቤት እንጀራና ወጥ እየሸተተው አንገቱን ደፋ፡፡ ለአዳሩ ካንዱ ቤት አንዱ እያለ ጊዜያት አሳለፈ፡፡ እንደ ቀልድ ጊዜው ገፋ፡፡ ድፍን አንድ ዓመት ተቆጠረ፡፡

### ያልተሸነፈ ችግር ...

አንድ ቀን እናት ድንገት ካገር ቤት ተመለሱ፡፡ የትንሹ ልጅ ዕንባ ታበሰ፣ ከፊቱ ደስታው ተመለሰ፡፡ በናፍቆት የከረመው ሀብታሙ ውስጡ ሲያገግም ቀን አልፈጀም፡፡ የልጅነት ወዙ ተመልሶ ፈገግታው

... ወደ ገጽ 17 ዞሯል



**ከአማኑኤል የአእምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም**

## ወጣቱ ራሱን ስመጉዳት አደጋ ላይ እንደሚሆን ጠቋሚ ምልክቶች

በርካታ የአፍሪካ ሀገራት ካላቸው የሕዝብ ቁጥር አብዛኛውን የሚሸፍነው ወጣት ነው፡፡ ወጣቶች አምራች ኃይል እንደመሆናቸው መጠን ለሀገር ኢኮኖሚያዊ እድገት ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ዓለም ካለችበት የቴክኖሎጂ እድገት ጋር እኩል መራመድና ለውጥ ማምጣት የሚችሉትም ወጣቶች ናቸው፡፡ ይህንን አይነቱን ለውጥ የሚያመጣው ወጣቱ ትውልድ ምርታማ እንዲሆን የአዕምሮ ጤናው የተጠበቀ ሊሆን ይገባል፡፡ በመሆኑም ሀገራት ትኩረታቸውን ሕጻናትና ወጣቶች ላይ በማድረግ ለአዕምሮ ጤናቸው መጠበቅ የራሳቸውን ሚና ሊጫወቱ ይገባል፡፡

ከዛሬ አስርተ ዓመታት በፊት በተደረገ ጥናት በዓለም ላይ ካሉት ሕፃናትና ወጣቶች ውስጥ እስከ 20 በመቶ የሚሆኑ ልዩ ልዩ የባሕሪ ችግሮች ያላቸው መሆኑን ጥናቱ አመላክቷል፡፡ በጥናቱም እንደተገለጸው የባሕሪ ችግር ካለባቸው ሕጻናትና ወጣቶች ውስጥ ከሦስት እስከ አራት በመቶ የሚሆኑ ሕክምና የሚያስፈልጋቸው ናቸው፡፡ በሕፃናትና ወጣቶች ላይ ከ10 መሪ የጤና ቀውስ ከሚያስከትሉት ምክንያቶች አምስቱ የባሕሪይ እና የአዕምሮ ጤና ችግሮች መሆናቸውን ጥናቶች ያረጋግጣሉ።

ባሳለፍነው ሳምንት ትኩረት የሚሹ የወጣቶች ችግሮች በሚል ርዕስ ወጣቶችና ሕጻናት ለአዕምሮ ሕመም የሚያጋልጧቸውን ችግሮች በስፋት አስቃኝተናችኋል። የሕጻናትና ወጣቶች አዕምሮ በተለያዩ ሰው ሠራሽና ተፈጥሯዊ ችግሮች ሊናጋ ይችላል፡፡ ከዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ጦርነት፤ ረሃብ፤ ድህነት፤ የእናቶች አካላዊ፤ ሥነልቦናዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር፤ የሕፃናት ሰብዓዊ መብቶች የአለመረጋገጥ ወዘተ በሕፃናት ብሎም በወጣቶች ሥነ-ልቦናና አዕምሮ ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራሉ፡፡ ከጦርነት፤ ከመፈናቀል ወዘተ የሚመጡት



ከፍተኛ የሥነልቦና ቀውሶችና የአዕምሮ ሕመሞች ወጣቶች ለበሽታ መዳረግ ብቻ ሳይሆን ኅብረተሰቡንም ወደ ከፋ የማኅበረሰብ ቀውስ ሊከትቱት ይችላሉ፡፡

ራስን ማጥፋት በሦስተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ የወጣቶች ሞት መንስኤ ነው፡፡ ሌላው ወጣቶችን ለከፋ የአዕምሮ ችግር ከሚያጋልጡት አንዱ ለአደገኛ መድኃኒቶችና ሱስ አምጭ እፆች አለአግባብ መጠቀም መሆኑን እንዲሁ ጥናቶች ያትታሉ፡፡

በባለፈው እትማችን ካስቃኘናችሁ ፕሮፌሰር መስፍን አርአያ በ1996 ዓ.ም የሥነ አዕምሮ ጤና ቀንን ምክንያት በማድረግ በአቀረቡት ዓውደ ጥናት ላይ የተለየ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባ ዋና ዋና የወጣቶች የባሕሪና ጤና ችግሮች ውስጥ ከፍተኛ ጭንቀት(Anxiety disorder)፤ ድብርት (Depressive disorder)፤ የባሕሪ ቀውስ (Disruptive behavior disorder)፤ የመማር ቀውስ (Learning Disability)፤ የሱስ አምጭ ንጥረ ነገሮች አለአግባብ ተጠቃሚነት (Substance Abuse)፤ በወጣት ላይ የሚከሰት ራስ ማጥፋት (Teen Suicide) ተጠቃሽ ናቸው፡፡

በዛሬው እትማችንም ልናስቃኛችሁ የወደድነው ወጣቱ ራሱን ለመጉዳት አደጋ ላይ እንደሚሆን ጠቋሚ ምልክቶች የሚሆኑትንና ይህንን አይነቱን ችግር ለመከላከል መደረግ የሚገባቸው ቅድመ ጥንቃቄዎችን ፕሮፌሰር መስፍን አርአያ በ1996 ዓ.ም የሥነ አዕምሮ ጤና ቀንን ምክንያት በማድረግ በአቀረቡት ዓውደ ጥናት ያቀረቡትን ነው፡፡ ወጣቱ ራሱን ለመጉዳት አደጋ ላይ እንደሚሆን ጠቋሚ ምልክቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የአመጋገብና እንቅልፍ ሥርዓት መዛባት
- ቤተሰብ፤ ጓደኞችና የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ መገለል
- ከቤት መጥፋት ያልተለመደ ዓመፅኛ ጠባይ
- የአልኮልና ሱስ አምጭ ነገሮች ተጠቂ መሆን
- ባልተለመደ ሁኔታ ራስን መጣል
- ስልቹነት፤ አዕምሮን ማሰባሰብ አለመቻል
- የተለያዩ ምክንያት የለሽ አካላዊ ችግሮች ለምሳሌ ሆድ ሕመም፤ ራስ ሕመም፤ ድካም ወዘተ....
- ለምንም ነገር ስሜት አልባ መሆን፤ ወዘተ... ለአብነት የተጠቀሱ ከፍተኛ የአእምሮና የባህሪ ችግሮች ናቸው።

ወጣቱ ራሱን ለመጉዳት አደጋ ላይ ከመጋለጡ በፊት ለመከላከልና ሕፃናት ገና ከመወለዳቸው በፊት ጀምሮ ወላጆች እርግዝናውን በማቀድ ከዚያም ፅንሱ ተገቢውን እንክብካቤ ማለትም የእናቲቱን አካላዊና አዕምሯዊ ጤና የተሟላ ማድረግ በወሊድም ወቅት ተያያዥ ችግሮች እንዳይከሰቱ ጥንቃቄ ማድረግ ለሕፃኑ የተሟላ የአካልና የአዕምሮ ጤና ከፍተኛ አዎንታዊ አስተዋፅዖ አለው፡፡

በሕፃንነት የሚደረግ የተሟላ እንክብካቤ ወደ ወጣትነት የሚደረገው ሽግግር የተስተካከለ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ የተስተካከለ አመጋገብ የተረጋጋና የተሟላ ቤተሰብና አካባቢ ከተለያዩ ወረርሽኝና ቅፅበታዊ በሽታዎች መጠበቅ በአካል በተለይም በራስ ቅል ከሚደርሱ አደጋዎች ታዳጊውን መጠበቅ እንዲሁም አዎንታዊ የጤና አስተዋፅዖ ሲኖረው በየወቅቱ ቤተሰብና ማኅበረሰብ የወጣቱን የተናጠልና የድምር ፍላጎት በሚገባ በመመርመር ከጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በማራቅ ጠቃሚ ባሕላዊና ዘመናዊ እሴቶችን በማዳበር ተገቢውን እንክብካቤ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ በጥናቱ ተብራርቷል።

# ያሳስፈ...

ከ16ኛ ገጽ የዞረ

ደመቀ። እናት ከቆዩበት ሲመለሱ መልካም አልቆያቸውም። ቀድሞ ያስጠጓቸው ሰዎች ቤት እንዲፈልጉ ገፏቸው፡፡ እናትና ልጅ ከደባል ኑሮ ወጥተው ደባል ኑሮ ውስጥ ገቡ፡፡ የአምና ካቻምናው ዓለም አልተቀየረም፡፡ በነበረበት እንደነበረ ቀጠለ ፡፡

አድካሚው ኑሮ አሰልቺ እየሆነ ነው፡፡ በየሰበቡ

ከጎረቤቶች የሚጋጩት ሴት ኃይለኝነታቸውን ሀገር አውቆታል፡፡ አዲስ በገቡበት ቤት ሰላም አልተገኘም። አሁንም ልጃቸውን ይዘው እንዲወጡ ተፈረደባቸው፡፡ ሀብታሙ የእንክርት ኑሮ ውስጡን ሰበረው፡፡ ሕይወት ይሉት ጣጣ ከበደው፡፡ ከአንዱ ወደ አንዱ መመላስ ከችግር መከራ አላመደው ፡፡

1982 ዓ.ም፡፡ ይህ ጊዜ የመንግሥት ለውጥ ዋዜማ ነበር፡፡ ሀብታሙ ከወጣትነት ዕድሜ ደርሷል፡፡ እሱን ጨምሮ ሌሎች ሰዎች በወቅቱ ‹‹ኮርፖሬሽን›› ከሚባል ድርጅት ዳቦ እየገዙ ይሸጣሉ፡፡ እንዲህ መሆኑ ለኑሯቸው በጎ ሆነ። አጋጣሚው እሱን ከሰዎች አገናኘው፡፡ ከአንድ ጋራዥ እየተከፈለው መሥራት ጀመረ ፡፡

## ብርቱ እጆች ...

ሀብታሙ የጋራዥ ሥራ አበረታው፡፡ ሙያ እየለመደ፣ ጉልበቱን ፈተነ፡፡ ከጎሚስታ እየዋለ የአቅሙን ታገለ፡፡ ይህ ጥረቱ ለኪሱ አላሳጣውም። እንደሌሎች ወግ ደረሰው፡፡ ለእሱና ለእናቱ ጉሮሮ ይዞ መግባትን አወቀ፡፡

1996 ዓ.ም፡፡ ሀብታሙ ዛሬን እንደትናንቱ አይደለም። ያለፈውን ችግር በጉልበቱ ድካም፣ በላቡ ወዝ ቀይሮታል። አሁን ሠርቶ ይገባል፡፡ ያለበት ዕድሜ ብርታቱ ነው፡፡ ከራስ አልፎ ለእናቱ፣ ለቤቱ ጎዶሎ ሙላት ሆነ፡፡ አንድ ቀን ሥራ ላይ ሳለ ከአንድ ሰው ጋር ተጋጨ፡፡ አብሮት የቆየ ባልንጀራው ነው፡፡

የጠቡ ሰበብ የገንዘብ ጉዳይ ነበር፡፡ የሁለቱ ጭቅጭቅ ተካሮ አንገት ለአንገት ተያያዙ፡፡ ያገላገላቸው፣ ያስማማቸው አልተገኘም፡፡ በድንገት የአንደኛው ኃይል በረታ፡፡ ላለመውደቅ እጅ ለእጅ ተጣምረው ታገሉ። ባልንጀራው ኃይሉን ተጠቅሞ የኋሊት ገፈተረው። ሀብታሙ ተደናቅፎ በጀርባው ተዘረረ፡፡ አልተነሳም፡፡ ከመሬቱ ቀድሞ ያገኘው ትልቁ የመኪና ታኮ ከወገቡ አርፎ አቅሉን አሳጣው ፡፡

ሀብታሙ ዕለቱን ለሕክምና ደረሰ፡፡ ውሎ አድሮ ግን ችግሩ ከፋበት፡፡ አከርካሪውን ያገኘው ጉዳት ወደ ነርቩ ተሻግሮ መላ ሰውነቱ ተያዘ፡፡ አድካሚው የሆስፒታል ምልልስ ያለማቋረጥ ቀጠለ፡፡ ትናንት የሚያውቁት ዛሬን ጎኑ ቆመው የቻሉትን አገዙ፡፡ እንደትናንቱ ቆሞ መራመድ አልሆነለትም፡፡

## ክፉ ቀናት ...

ሀብታሙ ድኖ ለመቆም በብዙ ጥረት ለፋ። የውስጡን ሕመም ታግሎም ሊራመድ ታገለ፡፡ አሁንም እንዳሰበው አልሆነም ፡፡ እግሮቹ ከክራንች ድጋፍ አላለፉም፡፡ እንዲህ መሆኑ ሥራ አስፈትቶ ከቤት አዋለው፡፡ ይህ አጋጣሚ ለጆሮው ክፉ ቃላት እያቀበለ ሆድ ያስብሰው ያዘ፡፡ የሰዎች ጨዋታና ንግግር ሁሉ ትርጉሙ ተለየበት ፡፡

ከሁሉም አንድ ቀን አንዲት ጎረቤታቸው ‹‹ጉልቻ›› ብላ ሰድባኛለች የሚልበትን ክፉ ቃልና ቀን አይረሳውም። ሴትየዋ ንግግሬ ለሌላ ነው ብትልም እሱ ግን የሀሳቧ አቅጣጫ ስለራሱ መሆኑን አምኖ ዛሬ ድረስ በዕንባ ያወሳዋል፡፡ ይህን ሲናገር በጥልቅ የኃዘን ስሜት ተውጦ ነው፡፡

ከሀብታሙ ጉዳት በኋላ የኑሮ ሸክም መልሶ በእናቱ ትከሻ ወደቀ፡፡ ደግነቱ ለዓመታት ሲጠይቁት የቆዩትን የቀበሌ ቤት አግኝተዋል፡፡ ሀብታሙ አሁን መሥራት አይችልም እሳቸው ዕድሜያቸው እየገፋ፣ አቅማቸው እየደከመ ነው፡፡ ዛሬን እንደትናንቱ ልብስ አጥበው፣ እንጀራ ጋግረው አይገቡም ፡፡

የሚኖሩበት አካባቢ በርካታ ተግባር አለው። ሮጦ የሚገባው፣ ዘርፎ የሚሮጠው፣ ተቀምጦ የሚለምነው ሲተራመስበት ይውላል፡፡ በዚህ መንደር ሕይወታቸውን በሴትኛ አዳሪነት የሚመሩ በርካቶች ናቸው፡፡ ለነዚህ ሴቶች በዕለት ቤታቸውን የሚያከራዩ ነዋሪዎች የቀን ገቢ አላቸው፡፡ በእጃቸው በሚገባ ገንዘብ ቤታቸውን መርተው ልጆች ያሳድጋሉ ፡፡

የነ ሀብታሙ ቤት ዕጣ ፈንታ ከዚህ አላላፈም። ሴቶቹ ክፍሉን በፈለጉት ጊዜ አከራይተው ገንዘብ ይወስዳሉ፡፡ የእናትና ልጅ ሕይወት ለዓመታት በዚህ መንገድ ተጓዘ፡፡ በሴቶቹ የዕለት ገቢ ሕልውናቸው ቀጠለ፡፡ ሀብታሙ እግሮቹ ያለክራንች አይታገዙም። ያለሥራ መቀመጡ ሰውነቱን አግዝፎታል፡፡ አሁን አንዳንድ የቅርብ ሰዎች ሀብታሙ ትዳር ሊይዝ ይገባል እያሉ ነው ፡፡

## ድንገቴ በረከት ...

አንድ ቀን የሀብታሙ እናት ድንገት ተነስተው ሀገር ቤት ተጓዙ፡፡ ከቀናት በኋላ ሲመለሱ ብቻቸውን አልነበሩም፡፡ አንዲት የገጠር ልጅ አብራቸው መጥታለች። ይህች ጉብል ቀድሞ የተመከረባት፣ ለትዳር የታጨችው የሀብታሙ ሚስት ናት ፡፡

ያለአንዳች ትውውቅ በወላጆች ይሁንታ የቆመው ትዳር አራት ልጆች አፍርቶ ዓመታት ቆጠረ፡፡ ባለቤቱ ሚስትም እናትም ሆነችለት፡፡ ይህ እውነታ ግን ብቻውን በጎ አልሆነም፡፡ የኑሮ ሸክሙን ከእሷ ትከሻ አሳርፎ አንገዳገዳት፡፡ ሀብታሙ ራሱን ችሎ አለመሥራቱ ለድህነት ስር ሆኖ ቀጠለ ፡፡

## ያልተራመዱ እግሮች...

ዛሬ የሀብታሙ እግሮች ከክራንች አልፈው ከዊልቸር ከዋሉ አስራ አራት ዓመታት ተቆጥረዋል። የትናንቱ ብርቱ አሁን አቅሙ ደክሟል፣ ምላስ አንደበቱ ተይዟል፡፡ ጎልማሳው አባወራ ሁሌም ቤተሰቦቹን እያስቸገረ መሆኑ ይሰማዋል ፡፡ በሰው እጅ መውጣት መግባት፣ መታጠብና መጸዳዳት እጅጉን ይከብዳል፡፡ በሕመሙ ሳቢያ በሚስቱ ትከሻ ማደሩ ለእሱ የዘወትር ኃዘኑ ነው፡፡

ሀብታሙ ከበሩ ደጃፍ ተቀምጦ የሞባይል ካርድ ሲሸጥ ይውላል፡፡ ከእጁ የሚገባው የካርድ ሽያጭ ኑሮን የሚለውጥ አይደለም፡፡ ማንነቱን የሚያውቁ የሰፈሩ ሰዎች ችግሩን አይተው ይገዙታል ፡፡ አንዳንዶች ቀሪውን መልስ አይቀበሉም ፡፡

## ሥራን በምጽዋት...

አንዳንዴ ደግሞ ሀብታሙ ከእጁ ሲያጣ ምጽዋት ይጠይቃል፡፡ የሚያዩት የተዘረጋ እጁን አያልፉትም። የቻሉትን ይጥሉለታል፡፡ በምስጋና ተቀብሎ ለልጆቹ ዳቦ ይሰጣል፡፡ አሁን እንደቀድሞው ቤታቸው ለሴተኛ አዳሪዎች አይከራይም፡፡ ለልጆች የዕለት ጉሮሮ፣ ለአስፈላጊ ወጪዎች ገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ይህን የሚያውቀው ሀብታሙ የአቅሙን እየሞከረ ሕይወትን ይታገላል፡፡ በዚህ ብቻ የኑሮ ቀዳዳ አልተደፈነም፡፡ ችግር ከሰው ፊት አቁሞታል፡ ይሉኝታውን ሰርቆበታል፡፡ የትናንት ብርቱ እጆች ለልመና ሲዘረጉ አይተዋቸውም፡፡ የተሰጠውን አመስግኖ ይቀበላል ፡፡

ሀብታሙ በሰፈሩ ዓመታትን ቆጥሯል፡፡ አንጋፋ ነዋሪ ነውና እንደሌሎች የዕድር አባል ነው፡፡ እንደወጉ ግን ወርሐዊ ክፍያ ማሟላት ተስኖታል፡፡ ችግሩን የሚያውቁ፣ የአቅሙን ማነስ የሚረዱ ወር ሲመጣ አስበው ይከፍሉለታል ፡፡


ዓውደ ዓመት ሲመጣ፣ መልካም ልብ ያላቸው ዝም አይሉትም፡፡ ሁሌም ያስቡታል፡፡ ለልጆቹ፣ ፍላጎት ለእሱ ወግና ክብር የሚጨነቁ ሰላምታቸው ባዶ አይደለም፡፡ ትናንት ሠርተው ያደሩ እጆች ዛሬ ለልመና ተዘርግተዋል። ቀኑን ሙሉ ፀሐይ ከዝናብ ሲታገል የሚውለው አባወራ ነገ ልጆቹ ተምረው ታሪክ እንዲቀይሩ ይሻል፡፡

## ያሳስፈ ትናንት ...

ዛሬ በነሀብታሙ ቤት ችግሩ ብዙ ነው። አራት ልጆችን መግቦ አሮጊት እናትና ባልና ሚስት፣ማስተዳደር ቀላል አልሆነም፡፡ ይህ ሁሉ ሸክም በሚስት ጫንቃ መውደቁ ደግሞ ጫናውን አክብዷል፡፡ ዕንባና ኃዘን በማያጣው ጎጆ አንዳንዴ ጦም ውሎ ማደር ብርቅ አይደለም፡፡

ዛሬም እንደ ትናንት ያላለፈው ችግር መላው ቤተሰብን እየፈተነ ነው፡፡ ባዶውን የቀየረ እጅ፣ ረሀብ የፈተነው ሆድ፣ ተስፋ የለሽ ዓይኖች የሌሎችን እገዛ ይናፍቃሉ፡፡ የመልካም እጆች በረከት፣ የቅን ሰዎች ልቦና መፍትሔ ቢሆናቸው፡፡

# ስፖርት



# ገብረመድህን ኃይሌ የዋልያዎቹ አሰልጣኝ ሆነው ተሾሙ

**ብርሃን ፈይሳ**

አዲሱ የኢትዮጵያ ወንዶች ብሔራዊ ቡድን(ዋልያዎቹ) አሠልጣኝ በዓለም ዋንጫ ማጣሪያ ጨዋታ ሥራቸውን ይጀምራሉ፡፡ የዋልያዎቹ መሪ አሠልጣኝ ገብረመድህን ኃይሌ ለአንድ ዓመት የሚቆይ ውል ከኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ጋር በትናንትናው እለት አስረዋል፡፡

በኢትዮጵያ እግር ኳስ ከተጫዋችነት እስከ አሠልጣኝነት የዘለቁት አንጋፋው አሠልጣኝ ገብረመድህን ኃይሌ ለብሔራዊ ቡድን ዋና አሠልጣኝነት በኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን መሾማቸውን ተከትሎ፣ ሥራቸውን እአአ ለ2026ቱ ዓለም ዋንጫ የማጣሪያ ጨዋታ የሚጀምሩ ሲሆን፤ የብሔራዊ ቡድን ስብስባቸውንም አሳውቀዋል፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ኅዳር 5 እና ኅዳር 11/2016 ዓ.ም የዓለም ዋንጫ ጨዋታዎቹን ከሴራሊዮን እና ቡርኪናፋሶ አቻዎቹ ጋር በተከታታይ በሜዳው ያከናውናል፡፡ ይህንንም ተከትሎ አሠልጣኙ ዋልያዎቹን ከሴራሊዮን ጋር ለሚኖራቸው የመጀመሪያው ጨዋታ ከነገ ጀምሮ ወደ ዝግጅት በመግባት ሥራቸውን ይጀምራሉ፡፡ ለቀናት በሚኖራቸው የዝግጅት ጊዜም አንድ የወዳጅነት ጨዋታ በማድረግ ግጥሚያው ወደሚደረግበት ሞሮኮ እንደሚያቀኑም ነው ትናንት በተደረገው የፊርማ ሥነሥርዓት ያስታወቁት፡፡

በኢትዮጵያ ፕሪምየርሊግ ተፎካካሪ ቡድን የሆነው ኢትዮጵያ መድንን በማሠልጠን ላይ የሚገኙት አሠልጣኙ፤ ከክለቡ ጋር ለረጅም ጊዜ የሚያቆያቸው ውል አላቸው፡፡ ይህ በዚህ እንዳለም ከክለብ አገልግሎታቸው ጎን ለጎን ዋልያዎቹን ለአንድ ዓመት ለማሠልጠን መስማማታቸው ተጠቁሟል። በወር የተጣራ 250ሺ ብር እየተከፈላቸውም ዋሊያዎቹን የሚመሩ ይሆናል። በቀድመ አጠራሩ መከላከያ(መቻል)፣ ጅማ አባቡና፣ ጅማ አባጅፋር፣ መቐለ ከተማ፣ ሲዳማ




**አሠልጣኝ ገብረመድህን ኃይሌ ዋሊያዎቹን ለአንድ ዓመት የሚመሩ ይሆናል፤**

ቡና እና አሁኑን ኢትዮጵያ መድንን እያሠለጠኑ የሚገኙት ገብረመድህን በተጫዋችነት ዘመናቸው ከወጣት ቡድን አንስተው እስከ ዋና ብሔራዊ ቡድን አምበልነት የመሩ ድንቅ ተጫዋች እንደነበሩ የሚታወስ ሲሆን፣ በአሠልጣኝነትም ከ20 ዓመት በታች አንስቶ እስከ ዋናው ብሔራዊ ቡድን ማገልገል ችለዋል።

አሠልጣኝ ገብረመድህን በተለይም እአአ 2016 በሁለት የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ጨዋታዎች ዋልያዎቹን በጊዜያዊነት የመሩ ሲሆን ሌሴቶንና ሲሼልስን እንዳሸነፉ ይታወሳል። ከዚያም በፊት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን የአሠልጣኝ አሥራት ኃይሌ ረዳት በመሆን የሴካፋ ዋንጫን ማንሳታቸው ይታወቃል፡፡

ከስድስት ዓመታት በኋላ ወደ ብሔራዊ ቡድን አሠልጣኝነታቸው የተመለሱት አሠልጣኙ ‹‹በድጋሚ ወደ ብሔራዊ ቡድን ተመልሻለሁ፣ ከተጫዋችነት እስከ አሠልጣኝነት አዲስ አይደለሁም፡፡ ይሄ ኃላፊነት ሲሰጠኝ ክለቤንም ብሔራዊ ቡድኑንም እንዳሠለጥን ነው ስለዚህም ባለው ፕሮግራም መሠረት በዓለም ዋንጫ ማጣሪያ ዝግጅት በተጫዋቾች ምልመላ ወደ ሥራ እንገባለን፡፡ በአጭር ጊዜ በቡድኑ አዲስ ነገር መፍጠር ባንችልም በሂደት ተተኪ እና ሥነምግባር ያላቸው ተጫዋቾችን ወደ ቡድኑ ለማምጣት እንሠራለን›› ብለዋል፡፡ ከብሔራዊ ቡድኑ ጋር የሚኖራቸው ቆይታ በውሉ መሠረት አንድ ዓመት ቢባልም ሊራዘም እንደሚችልም ጠቁመዋል፡፡

ሁለት ቡድኖችን በአንዴ ከማሠልጠን ጋር በተያያዘ ስለሚኖረው አስቸጋሪ ሁኔታ ጥያቄ የቀረበላቸው አሠልጣኙ፤ ችግር ሊኖረው ቢችልም ሥራቸውን ትኩረት ሰጥተው በተገቢ ሁኔታ በመሥራት እንደሚያቻችሉትም ገልጸዋል፡፡ የፕሪምየር ሊግ ጨዋታ አንድ ቦታ የሚከናወን መሆኑ ሊኖር የሚችለውን አስቸጋሪ ሁኔታ በማቃለል ረገድም የጎላ ሚና አለው፡፡ ከዚህ ባለፈ ሁለት ቡድኖችን መያዝ የጥቅም ግጭት ሊያስከትል ይችላል የሚል ስጋት በስፖርት ቤተሰቡ ዘንድ መፈጠሩ አይቀርም፡፡ ይህንን በሚመለከትም አሠልጣኙ ቅድሚያ የሚሰጠው ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን እንደመሆኑ ቡድኑን የሚመጥን ተጫዋች ከየትኛውም ቡድን ሊመረጥ እንደሚችል አስረግጠዋል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ከአሰልጣኝ ውበቱ አባተ ስንብት በኋላ በፌዴሬሽኑ የቴክኒክ ዳይሬክተር ዳንኤል ገብረማርያም ጊዜያዊ አሠልጣኝነት ሁለት የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ጨዋታዎችን ማከናወኑ ይታወሳል፡፡ ይህንን ተከትሎም አዲስ አሠልጣኝ የሾመው ፌዴሬሽኑ፤ አሠልጣኙን በዋናነት ለዓለም ዋንጫ እና አፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ጨዋታዎችን እንዲመሩ የቀጠራቸው መሆኑን አስታውቋል፡፡ በስምምነት ሥነሥርዓቱላይ መግለጫውን የሰጡት የፌዴሬሽኑ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ባሕሩ ጥላሁን፤ ሥራ አሥፈጻሚው አሠልጣኝ ገብረመድህን ኃይሌን ለመቅጠር ከስምምነት ላይ የደረሰው ከአምስት ወራት በፊት እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡ ነገር ግን አሠልጣኙ ከክለባቸው ጋር ውል ያላቸው እንደመሆኑ ንግግር በማድረግ ከስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ ከዚህ ቀደም አንድ አሠልጣኝ ከክለብ ጋር ውል እያለው ብሔራዊ ቡድኑን ማሠልጠን አይችልም የሚል ሕግ በፌዴሬሽኑ ሲተገበር የቆየ ቢሆንም፤ ሥራ አሥፈጻሚው ለፌዴሬሽኑ ጥቅም ሲባል ሕጉን አሻሽሏል፡፡ በመሆኑም ለአንድ ዓመት በሚኖረው ቆይታ የብሔራዊ ቡድን ጨዋታዎች ሲኖሩ ፕሪምየር ሊጉ የሚቋረጥ በመሆኑ አሠልጣኙ ዋሊያዎቹን በማዘጋጀት በጨዋታዎች ላይ የሚሳተፉ እንደሆነም አብራርተዋል፡፡